መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም ባንበላም ምንም አይጐድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም። ዳሩ ግን ይህ መብታችሁ ለደካሞች እንቅፋት እንዳይሆንባቸው ተጠንቀቁ። አንተ እውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ አንድ ሰው ቢያይህ ደካማ ሰው ቢሆን ለጣዖት የተሠዋውን ለመብላት ሀሊናው አይታነጽበትምን? በአንተ እውቀትም ይህ ደካማ ይጠፋል፤ እርሱም ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው። እንዲህም ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ። ስለዚህም መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ወነድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።

1 ቆሮንቶስ 8÷8-13

የማሰናከያ ዐለት

እኔና ሬይ ቀያ ለጉብኝት ሄደን ድንኳናችን ሥር ቆመን ሳለ ድንገት በጣም የሚያስፈራ ጩኸት ምንጣፍ ከወደሚሠራበት ቤት በኩል ሰማን። በፍርሀት ተሞልተን ምክኒያቱም ለማወቅ ጓጓን።

በመዝሊያው በር በኩል ሰናይ እረብሻ ተከሥቶ አየን። አስቻለው የተባለው አንዱ የምንጣፍ ሥራ ተማሪያችን ዱላ አንሥቶ ሰውን ሁሉ ያስፈራራውና ያስጮኸው እሱ ነበር። በዚህ ጊዜ አስቻለው አንዱን የምንጣፍ ሠራተኛ ጓደኛውን መትቶ በወለል ላይ ገፍትሮ ጥሎት ነበር። ነገር ግን እኛን ሲያይ መደብደቡን አቆመ። ሆኖም አሁንም በቁጣ ተሞልቶ ነበር። እንደገናም ሊመታው ያስብ ነበር። ነገሩን ቀረብ ብሎ ያየ ሰው እንደ ነገረን የተደበደበው አያሌው የተባለው የምንጣፍ ሠራተኛ ጓደኛው ነበር። በሰውነቱ ላይ ሰንበርና ምልክት ቢታይም፣ የተጐዳ የአካል ክፍል አልነበረም። ስለ ተፈጸመበት ድብደባ በጠየቅነው ጊዜ፣ መቀስ ይዞ ስለ ነበር በአጋጣሚ የአስቻለውን ሸሚዝ እንደ ቀደደና ድርጊቱንም ሆን ብሎ እንዳላደረገው እያለቀሰ ነገረን።

የተመታው ሸሮለት ወደ ምንጣፍ ሥራው ለመመለስ አንድ ሳምንት ፈጀበት። አያሌው ተመልሶ ከመጣ በኋላ በአስቻለው ጉን ባለው ወንበር ላይ ሆኖ ነበር የሚሠራው። ከዚህ የተነሣ የሁለቱ አብሮ መሥራት ችግር ነበረበት። ከቀናት በኋላ ግን ሁኔታው እየተረጋጋ ሄደ። ከዚያም በኋላ አያሌው በመቀሱ ሲጠቀም ይጠነቀቅ ነበር። አስቻለው ግልፍተኛነቱን እንዴት ማስወገድ እንዳለበት ትምህርትና ምክር ሊሰጠው እንደሚያስፈለግ ዐሰብን።

በመንዝ ዙሪያ ሰዎች ሁሉ የአድባር ዛፎች ተብለው የሚጠሩና ክፉ መንፈስ እንደሚያድርባቸው የሚታመኑ የቄዩና ያማሩ ዛፎች መኖራቸውን ያውቃሉ። እነዚህ ዛፎች በትልቅ ፍራቻ ይመለካሉ። ማንኛውም ሰው ዛፉ ላይ ለመውጣት፣ ለመቁረጥ፣ ከሥሩ ሆኖ ለመጫወት ወይም አጠገቡ ለመሥራት አይደፍርም። እነዚህ

ዛፎች ተቁርጠው ስለማያውቁ፣ በአካባቢው ካሉት ዛፎች ሁሉ ያረጁና የሚበልጡ ናቸው።

በዓመት ውስጥ ሁሉም ሰው በታዘዘበት ጊዜ ልመናውን ለማቅረብ ስጦታ ይዞ ወደ አድባር ዛፎቹ ይሄዳል። እነዚህ ስጦታዎች ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳት ማለት ዶሮዎች፣ በጎች ወይም ፍየሎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ወይም ምግብ ማለት ቅቤና ማር መሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ዛፉ ላይ ልብስ ይንጠለጠላል፤ ወይም የዶሮ ላባ እንደ ጌጥ ይቀመጥበታል። ምንም ይሰጥ ፍላጎቱ ያው ነው። የስጦታው ዐላማም በዚያ ለሚያድረው ጎይል ለውለታው ምላሽ ክብር ለመስጠት ነው።

አንድ ቀን አንድ አሳፋሪ ዜና ደረሰን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ዎቻችን መካከል አንዱ የአድባር ዛፉን መጠጋት ብቻ አይደለም ሌላ ሰው በዛፉ ላይ አስቀምጦት የሄደውን ስጦታ እንደ ወሰደ ሰማን። በመንዝ በጣም ውድ የሆነውንና የሚፈለገውን አንድ ማሰሮ ቅቤ ነበር የወሰደው። ከዚህም ዐልፎ ቅቤውን የተጠቀመበት የደረቀና የተሰነጣጠቀ እግሩን ለማለስለስ ነው።

ይህን ጥፋት የፈጸመው ማን እንደ ሆነ ያወቅነው በመጀመሪያው ግምታችን ነበር። አስቻለው ነበር። ስለ ጉዳዩ ስናናግረው በሞኛ ሞኝነት ድርጊቱን እንደ ፈጸመ አመነ። ዛፉን ማምለክ ለእርሱ ስሜት ስለማይሰጠው በጊዜው ሐሳቡ ምንም መስሎ አልታየውም ነበር። ጥሩውን ቅቤ እንደዚያ ማድረግ ማባከን ሆኖ ታየው። ነገር ግን ቀጣ እንደሚያስነሣ አላስተዋለም። ምናልባትም ነገሩ ጥሩ ሐሳብ እንዳልነበር ሳይገነዘብ የቀረ አይመስልም።

ይህ ችግር ተከሥቶ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሌላ ችግር ተፈጠረ ። በዚህን ጊዜ ደግሞ የዚህ ክሥተት ምክንያቶች ሁለት ተማሪዎች ነበሩ። የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ እንደሚጸሙ ይታወቃል፤ በጾም ጊዜ የሚበሉት ተራ ምግብ ማለት ጥራጥሬና ጥቂት ቅጠላ ቅጠል ነውና በጣም አሰልቺ ይሆናል።

በድጋሚ አስቻለው ካገኘው ዐዲስ ነጻነት የተነሣ ከዚያ በኋላ የጾም ሕግጋትን መከተል እንደማያስፈልገው ወሰነ። እምነቱን ለማሳየት በጾም ቀን ዶሮ ዐርዶ ጓደኛውን ዲያቆን ግርማን ወደ እርሱ እንዲመጣ ጠራው። አስቻለው ይህን ያደረገው አንድ ነገር ለማሳየት ፈልጎ ነበር። ሁሉም ሰዎች እያዩ የተዘጋጀውን የፍስክ ምግብ ተመገቡ።

ለዚህ ድርጊት የተሰጠው የአፀፋ ምላሽ ፈጣን ነበር። ሰዎቹ ተናደዱ። ሁኔታው ልክ እንደ ጠረጠሩት ሆኖ አገኙት። ዐዲሱ የመጤ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሰዎችን ሕግ እንዲጥሱ አድርጓል። እግዚአብሔርን መቃወም ነበር። እንዲህ ዐይነት ነገሮች የዐዲሱ ትምህርት ውጤት ከሆኑ፣ ሰዎች መንም ነገር ማድረግ አይፈልጉም።

በዚህ ምክንያት አስቻለውና ግርማ እንዲሁም ሌሎች ጓደኞቻቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳያገለግሉ ተከለከሉ።

ወደ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ለመመለስ ለስድስት ወራት ሲጠብቁ ቈይተው በዚህ ጊዜ ግን በድንገት እዚያ የመገኘት መብታቸውን ዐጡ። ሁሉም ሰው ሕግን የሚጥስ ሰውን አስተያየት መስማት አይፈልግም። አስቻለው ችኩል ባሕርዩ ካስከተለበት ችግር የተነሣ በጣም ተናደደ። ስለሚከተለው ዐዲስ እምነት ለሁሉም ሰው መንገር ወስኖ ነበር። ሆም እንደ ሰማው ጮኾ ለመናገርም እንኳ ፈልጎ ላለ፣ ከችግሩ የተነሣ ለማንም የመንገር ዕድሉን ባጠቃላይ አበላሸው።

አስቻለው በብዙ መንገዶች ጴጥሮስን ያስታውሰን ነበር። ዐዲስ ሐሳብ ሲያገኝ ወዳያውኑ መሞክር ይፈልጋል። አንድ ነገር ስሕተት እንደ ሆነ ከተሰማው ደግሞ በተቻለ ፍጥነት ነገሩን ለማስተካከል ይሞክራል። አስቻለው ትዕግሥት የሌለው፣ የሚሰማውን ወዲያውኑ አፉ እንደ አመጣለት የሚናገር ሰው ነበር። በዚህ ምክንያት ጌታ በሕይወቱ እንዲሠራና እንዲያለሳልሰው እንጸልይ ነበር።

ቀጥሎም የጾም ጕዳይ ቡድኑ ውስጥ ባሉት ሰዎች ሁሉ ተነሣ። ጕዳዩ መነሣቱ ዐዲስ ችግር እንዳልሆነ እናውቅ ነበር። ጳውሎስ ልክ እንደዚህ ዐይነት ችግር በጥንት ክርስቲያኖች ዘንድ ሊጋጥሞት ነበር። ሥጋ ሁሉ ጥሩ እንደ ሆነና እንድንመገበው በእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ነግሯቸዋል። ነገር ግን ሥጋ መብላቱ ለወንድሙ ዕንቅፋት ሆኖ የሚታየው ከሆነ፣ የአይሁድን ሕግ መከተል እንደሚቀጥል ተናገረ። አስፈላጊ ከሆነ ጳውሎስ በኖረበት ጊዜ ሁሉ ሥጋ ሳይመገብ ለመኖር ፈቃደኛ ነበር።

ጊዜው ስለ ሕግና ስለ ጸጋ የምንማርበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የምናደርግበት ጊዜ መሆኑን አስተዋልን። ሰዎቹ ደኅንነትን አስካገኙ ድረስ ሕጉን ለመጠበቅ ሙከራ ያደርጉ የነበረው፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ብቁ እንደሚደርጋቸው በማሰብ ነበር። ከዳኑ በኋላ ግን ሁሉ ነጻ ናቸው። በራሳቸው ሥራ ፈጽሞ እዚህ ሊደርሱ እንደማይችሉ ዐውቀዋል። በጥፋተኝነት ተፈርደባቸው ነበር ነገር ግን ኢየሱስ ቅጣታችንን ከፍሏል። ከእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ የተነሣ የሚገባቸውን አልተቀበሉም። ይቅርታ ተደርጎላቸዋል።

ይህ ማለት ከዚህ በኋላ ሕጉን መጠበቅ የለባቸውም ማለት ነው? እያንዳንዳቸው እምነታቸውን ለጓደኞቻቸውና ለዘመዶቻቸው ማካፈል ይፈልጉ ነበር። ሕጉን ቢያሞጋግሱ፣ ማንም አያዳምጣቸውም። ስለ ሌሎች ከልባቸው ከተጠነቀቁ፣ ራሳቸውን ዕንቅፋት ከመሆን ይጠብቁ ነበር። ሕጉን በመጣስ የሰዎችን ትኩረት ከኢየሱስ ወደ ራሳቸው እንዲመጣ ያደርጋሉ።

ጳውሎስ በግማሽ አይሁዳዊ የነበረውን ጢሞቴዎስን ለአይሁድ ለመመስከር ሲሄድ አብሮት እንዲወጣ ገረዘው። ከጥቂት ጊዜ አስቀድሞ አማኝ ሆኖ ስለ ነበር፣ መገረዙ ለደኅንነቱ አስፈላጊ አልነበረም።

የተገረዘው ከሕጉ ወጥቶ ለአይሁድ መሰናክል እንደይሆንባቸው ነበር። ጳውሎስ ያንን ያደረገው ጢሞቴዎስ ሕግን ስሚጠብቁ አይሁድ እንዲመስክር ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ እኛም ሰዎቹን ሕጉን ማክበር እንዲቀጥሉ አበረታታናቸው። ይህ የተለየና ዐዲስ ዐላማ ነበረው። ሕግን መጠበቅ ደኅንነትን እንደማያስገኝ ያውቃሉ። ነገር ግን ለወንድማቸው ካላቸው ፍቅር የተነሣ ሕጉን መጠበቅ ነበረባቸው። ከዚያም በኋላ ከሸክምነት ለኢየሱስና በዙሪያቸው ላሉ ፍቅራቸውን በልዩ ሁኔታ ወደሚያሳዩበት መንገድ ተለወጡ።

በኢትዮጵያ ባሳለፍናቸው ጊዜያት በተደጋጋሚ የራሳችንን ሁኔታ ከአርቶዶክስ የምግብ ሕግጋት አንጻር እንመረምር ነበር። በርግጥ መጀመሪያ ላይ በዚህ ረገድ የምናውቀው ትንሽ ነገር ብቻ ነበር። ነገር ግን በመንዝ እየቈየን በሄድን ቊጥር ብዙ ተማርን። እንደ ጥሩ አርቶዶክስ ክርስቲያን ዕሮብና ዐርብ እንዲሁም ከፋሲካ በፊት አርባ ቀን ሥጋን ወይም የእንስላት ተዋፅኦን ማለት ወተትን፣ ዐይብን፣ ቅቤንና ዕንቊላልን ከመመገብ መቈጠብ ነበረብን። በተጨማሪም በአጠቃላይ የዐሣማ ሥጋን በምንም ዐይነት መንገድ መመገብ አቆምን፤ ጥንቸል፣ ዳክዬና ዝይም እንዳይበሉ የተከለከሉ መሆናቸው ይታወቃል።

በቤታቸው ስንሆን የሚበሉትን መብላት ሲጸሙ መጸም ቀላል ነበር። ነገር ግን እንግዳ ተቀባዮች ስለ ሆኑ ትርፍ ካላቸው በጾም ጊዜ በተደጋጋሚ ወተት ያቀርቡልናል። እንደ እነርሱ ያለ የጾም ሕግጋት እንደሌለንና ያልተጣራ የገብስ ቢራቸውን እንደማንወድ ያውቁ ነበር። ካልጠጣን ያበሳጫቸዋል ስለዚህ የተሰጠንን እንጠጣና ከሳምባ ነቀርሳ ወይም ከሌላ በሽታ እግዚአብሔር እንዲጠብቀን በጸጥታ እንጸልያለን።

ስለ አመጋገብ ሕግጋት ብዙ እየተማርን ስንሄድ፣ በዚህ ምክንያት ሌላ ችግር እንዳይከሠት ጥረት እናደርግ ነበር። በተለይ ደግሞ ሰዎቹ እኛ ቤት መጥተው ሻይ ሲጠጡ ወይም ምግብ ሲመገቡ በጣም እንጠነቀቅ ነበር። ዐሰፎ ዐልፎ እንሳሳትና ማድረግ የሌለብንን ነገር እናዘጋጃለን። ምን እንደ ሆነ በማስተዋል ሲነግሩን ግን ወዲያውኑ ያንን ምግብ እናስወግደዋለን።

ቀጥሎ ፊታችን ላይ የተጋረጠብን ጥያቄ በመንዝ ስድስት ዓመት ከኖርንና የአመጋገብ ሕጉን በአብዛኛው ካወቅን በኋላ ሕጉን ልንከተል ይገባልን? የሚል ነበር። ጥያቄውን በዐዲስ ኪዳን ጳውሎስ ስለ ሕግ አጠባበቅ በሰጠው ትምህርት ላይ ተመርኵዘን አጠናነው። መልስም አገኘን። አሕዛብ ክርስቲያን ሲሆኑ ተገርዘው አይሁድ መሆን አልነበረባቸውም። ከአይሁድ ጋር ምግብ እንዲመገቡ ጥቂት የአይሁድ የምግብ ሕግጋትን እንዲጠብቁ ብቻ ነበር የማኦከሩት። ደኅንነታቸው በጸጋ እንደ መጣና የሕጉን ሸክምም በላያቸው መጫን እንደማያስፈልግ ርግጠኞች ነበሩ።

ያ ሁኔታና እኛ የነበርንበት ሁኔታ በብዙ መልኩ ይመሳሰል ነበር። ኦርቶዶክስ አልነበርንም። ደኅንነታችንን በጸጋ ያገኘነው የኦርቶዶክስን ሕግጋት ከማወቃችን በፊት ነው። ቁይቶ ሕግጋቱን መጨመር በርግጥ ሕጉን ለመጠበቅ ፈቃደኛ መሆን ነው።

ሰጕዳዩ ትልቅ ትኵረት ለመስጠት ሞከርን። የአመጋገብ ልምዳችን ዕንቅፋት ሆኖ የተገኘበትን ቦታ አግኝተንም አናውቅም። የውጭ አገር ሰዎችን አጋንንት የማይዟቸው የዐሣማ ሥጋ ስለሚበሉ ነው ብለው የመንዝ ሰዎች ማሰባቸው አስገራሚ ነበር። በተወሰነ መንገድ ከእነርሱ እንደምንለይ ተረድተዋል ነገር ግን ትክክለኛውን ምክንያት አያውቁም ነበር።

ዐዲሶቹ አማኞች በቤተ ክርስቲያናቸው ያለውን ልማድ በጥንቃቄ ለመመልከት ተገደው ነበር። ሁልጊዜ በፀደይ ወቅት ታቦቱ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ በሰልፍ ሲሄድ፣ ትልቅ የበዓል አከባበር አለ። ከሥርዐቱ ፍጻሜ በኋላ በሬ ይታረድና ሕዝቡ ጥሬ ሥጋ ይመገባል።

ከእነዚህ በዓላት መካከል በአንዱ ላይ እንድንገኝ ተጋብዘን ነበርና ተገኝተን እንደ ተለመደው የሚደረገውን በሙሉ በጥንቃቄ ተመለከትን። ከሥርዐቱ በፊት ሰዎቹ ከእንስሳው ዋጋ ድርሻቸውን እንዲከፍሉ ለማድረግ ትልቅ ክርክር ተደርጓል። ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በሕጉ መሠረት እንስሳው ተባረከ። ቁሱ ይህን የሚያደርገው ደማቁን የበዓል ካባ በመልበስና መስቀሉን በመያዝ ነው።

የእንስሳው መታረድ ዓላማ ምን እንደ ሆነ ስንጠይቅ፣ ለሰይጣን መሥዋዕት የሚቀርብ እንደ ሆነ ተረዳን። ለመጪው ዓመት ሳይጉዳ እንዲተዋቸው እንደ ስጦታ በሬ ይታረድለታል። ይህን በማድረግ መጥፎ የአየር ንብረትን፣ በሽታን፣ አደጋዎችን፣ መሬቱ ፍሬ እንዳያፈራ የሚያደርገውን፣ ዝናብ የሚያጠፋውንና እንዲሁም ሌሎች ከሰይጣን ጋር የሚያያዙ ነገሮችን ሁሉ ለመከላከል ይሞክራሉ።

ጓደኞቻችን ኢየሱስን ከማወቃቸው የተነሣ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ልማድ ተቃወሙት፤ መሳተፍም እንደሌለባቸው ወሰኑ። እንዲህ ዐይነቱ ሥጋ ብዙ ጊዜ አይዘጋጅም ነበር፤ ነገር ግን ምእመናኑ ለሰይጣን ምንም ዐይነት ክብር ለመስጠት አልፈለጉም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሰይጣንን እንዳሸነፈው ተረድተዋልና እነርሱ ማድረግ የሚገባቸው በኢየሱስ ስም ድል ማወጅን ብቻ ነበር።

ስለ ጣዖት አምልኮም ደግሞ ማሰብ ጀመሩ። የአድባሩን ዛፍ ማምለክ ስሕተት እንደ ሆነ ለማየት ቀላል ነበር። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ በማስተዋል ሊመለከቱ በውስጡ ያሉ ጥቂት ነገሮች ጣዖታት እንደ ሆኑ ተገነዘቡ።

ሁልጊዜ እሑድ ጠዋት ላይ ቅዳሴው ሲያልቅ፣ ቄሱ መስቀል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ እየዞረ እያንዳንዱን ሰው ይባርካል። ጥቂቶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እንዳለ ወይም መስቀሉ ምንን

እንደሚወክል ያውቃሉ፤ ሆኖም ብዙዎቹ የቅዱሱን ዕቃ በረከት ለመቀበል ይጓጓሉ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባት በፊት የቤተ ክርስቲያኑን በር፣ መሬቱን ወይም መጽሐፍ ቅዱሱን መሳም በራሱ መጥፎ አይደለም። ነገር ግን ለብዙዎቹ ያ ማለት የማይታየውን እግዚአብሔርን ማየትና ማምለክ እንዲሁም በረከትን መቀበል የሚችሉበትን የመቀየር ሙከራ ማድረግ ማለት ነው።

ጓደኞቻችን እግዚአብሔርን በመንፈስ ማምለክ ተማሩ። በልዩ ቅዱስ ቦታ እግዚአብሔርን ለማምለክ ሁሉንም ትክክለኛ አልባሳትና መጐናጸፊያ መልበስ ለእነርሱ ከዚያ በኋላ አስፈላጊ አልነበረም። እግዚአብሔር በየቦታው እንጂ በአንድ ሕንጻ ተወስኖ ሊቀመጥ እንደማይችል አስተዋሉ። ያ ማለት ደግሞ በየትኛውም ሰዓትና ቦታ መጸለይ እግዚአብሔርን ማምለክ ይቻላል ማለት ነው።

በዐዲሱ ነጻነታቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመሄድ አልተ ቈጠቡም። እግዚአብሔርን ለማምለክ ጥሩ ቦታ ነበር። ሃይማኖታዊ ግዴታቸውንም መፈጸም አላቋረጡም። ነገር ግን ስለሚናገሩትና ስለሚያደርጉት ነገር ሁሉ በልምድ ዝም ብሎ ከመፈጸም ይልቅ ማሰብና ማስተዋል ጀመሩ። አገልግሎት ላይ መጽሐፍ ቅዱስን በግእዝ ቋንቋ በማንበብ ፈንታ በአማርኛ ማንበብ ጀመሩ። በቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸው ዐዲስ ትርጉም ያለው ነገር ለማየት በቁ።

በዚህ ጊዜ በይሁዳ፣ በገሊላና በሰማርያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን በሰላም መኖር ጀመረች፤ ተጠናከረችም። ደግሞም እግዚአብሔርን በመፍራት እየተመላለሰችና በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች በቍጥር እየበዛች ሄደች።

የሐዋርያት ሥራ 9፡31

መብዛት

በ1968 መጀመሪያ ላይ በቀያ የሽመና ትምህርት የምናስተምራቸው ተማሪዎች ስለ ተመረቁ ድንኳናችንን ይዘን ወደ ቤታችን ተመለስን። በፀሐይ ሲና የእጅ ሥራ ትምህርት ቤት እንደ ተማሩት ሽማኔዎች በየቤታቸው የሽመና ዕቃ ሠርተው ራሳቸውን ችለው የሽመና ሥራ በግል ጀመሩ። ከእነርሱ ጋር በየቀኑ መገናኘት አቆምን ነገር ግን እነርሱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንድንሄድ ከዚያም በኋላ ይፈልጉ ነበር።

ስለዚህ የክትትል ትምህርት መርሐ ግብር ነድፈን ጀመርን። ለዚያ የክትትል ትምህርት የሚያገለግሉት የመማሪያ መጻሕፍት በአማርኛ የተጻፉና ለሳምንቱ ቀናት የሚሆኑ ዐጫጫር ትምህርቶችና በቤት ሥራ መልክ የሚሠሩ ጥያቄዎችን የያዙ ነበሩ። ሁልጊዜ ረቡዕ ረቡዕ እንገናኝና በሳምንቱ ትምህርት ላይ ዐጭር ፈተና ይሰጣቸዋል፤ ከዚያም የቤት ሥራ መልሶቻቸውን እንከልሣለን። የሆነው ሆኖ ብዙውን ጊዜ የምንፈጀው የተማሩትን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው እንዴት እንደሚተገብሩት በመወያየት ነው።

ሁሉም ሙሉ በሙሉ በነጻ የሚሰጥ ስለ ነበር ከጅምሩ እያንዳንዱ ተማሪ ለሚወስደው መጽሐፍ አንድ ብር እንዲያስይዝ አደረግን። ተማሪዎቹ የቤት ሥራውን መልሶች በሌላ ማስተወሻ ደብተር ላይ ይጽፉ ነበር። ከዚያም ትምህርቱ ዐልቆ መጽሐፉን ሲመልሱ ብራቸው ይመለስላቸዋል።

በመጀመሪያው ኮርስ ላይ ዐሥራ ሦስት ዲያቆናት ተመዝግበው ለትምህርቱ በየጊዜው ወደ ቀያ ይመጡ ነበር። ምንም እንኳ ቁስ ግርማ በአዲስ አበባ የካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ውስጥ እየተማረ የነበረ ቢሆንም፤ ከተማሪዎቹ ጋር እንገናኝ የነበረው በእርሱ ቤት ውስጥ ነው። ግቢው ውስጥ ሁለት ቤት ነበረው። እርሱ ሲሄድም ቤተ ሰቡ ይጠቀም የነበረው በአንዱ ቤት ብቻ ነበር። በሌላው ቤት ውስጥ ተማሪዎችን እንድናስተምር ባለቤቱ በደስታ ፈቀደችልን።

በመጀመሪያ የተጠናው መጽሐፍ ስለ ጸሎት የሚያስተምር መጽሐፍ ነበር። ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጸሎት ምን እንደሚያስተምር ሲያውቁ የማስተዋል ችሎታቸው እያደገ መሄድ ጀመረ። እያንዳንዱ የትምህርት ጊዜ በጸሎት ይዘጋ ነበር። ብዙዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ጸሎት እንዴት እንደሚጸለይ የተማሩት በነዚያ የትምህርት ጊዜያት ነው።

ከፀሓይ ሲና እየመጡ ሊማሩ የሚፈልጉ ረቡዕ ረቡዕ ይመጡ ነበር። ከሁለት ወር በኋላ እነርሱም ተመሳሳይ የትምህርት መርሐ ግብር በቤታቸው አቅራቢያ እንድንጀምር ጠየቁን። ብዙ ጓደኞቻቸው እንደሚመጡም ርግጠኞች ነበሩ። እኛም ትምህርቱ ለመጀመር እንደምንሞክር ተስማማን።

ይህን ሐሳብ በማቅረባቸው ትክክል ነበሩ። በፀሓይ ሲናም ለክትትል ትምህርት ተመሳሳይ ፍላጎት ነበር። በጠቅላላ የተመዘገቡት ሃያ አራት ሰዎች ሲሆኑ፣ ከእነርሱ ውስጥ ስድስቱ ቄሶች ነበሩ። ከዚህ ቡድን ጋር የነበረው ውይይት ብዙ ቄሶችና ትልልቅ ተማሪዎች ስለ ነበሩበት በቀያ ከነበረው ይልቅ የደመቀና አነሣሽ ነበር። በነበራቸው ሥልጣን ስለሚተማመኑ፣ ነገሮችን ለመፈተሽና ሐሳቦችን ለመመርመር አይፈሩም ነበር።

ሚያዝያ ወር ላይ ሁለተኛውን ኮርስ በቀያ ጀመርን። በዚህ ጊዜ አንድን ቄስ ጨምሮ ዐሥራ ዘጠኝ ተማሪዎች ተመዘገቡ። ስለ ምስክርነትና ስለ ዮሐንስ ወንጌል ሐሳብ በሚያስተምሩ ሁለት መጻሕፍት ተጠቀምን። አንድ ቀን የዕለቱ ትምህርት ካለቀ በኃላ፣ ሁለት ወጣት ወንዶች እንደ መኮ፣ እንደ ንጉሤና እንደ ሚስዮናውያን መስበክ እንዲችሉ እናስተምራቸው ዘንድ ሊጠይቁን ወደ ኋላ ቀሩ።

ያቀረቡት ሐሳብ ጥሩ ሐሳብ ነበር። ጊዜውም ትክክለኛው ጊዜ ነበር። ከመደበኛ ትምህርቱ በተጨማሪ በሳምንት ሁለት ተማሪ ሰባኪዎችን ለማስተማር ወሰንን። እንደ አስፈላጊነቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያዎችንና ልዩ ልዩ ሐሳቦችን እናቀርብላቸው ነበር። ከእያንዳንዱ የትምህርት ጊዜ በኋላ በግል እናነጋግራቸውና በጥሩ ጉናቸው እንዲገፋ አበረታተን ደካማ ጉናቸው ላይ ደግሞ እንረዳቸዋለን።

ይህንን ሐሳብ ይዘው በመጀመሪያ ወደ እኛ የመጡት ታጠቅና ግርማ ስለ ነበሩ፣ ለውይይቱ የመጀመሪያዎቹ እንደ ሆኑ እነርሱን ጠየቅናቸው። ታጠቅ ብዙ አያወራም ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱ ላይ በጣም ጉበዝ ነበር። ግርማ ደግሞ የቄስ ግርማ ጓደኛ ም፣ ተማሪም ነው። ቄስ ግርማ በሌለበት ጊዜ ሌሎቹ ግርማን የሚመለከቱት እንደ ተጠሪያቸው ነው። ግርማ ከሁሉም ሰዎች ረጅም ቁመና ያለው ሲሆን፣ ይህም ከመልከ መልካምነቱና ከፈጣን አአምሮው ጋር ተዳምሮ ትክክለኛ መሪ ያደርገዋል።

በቀጣዩ ሳምንት በጓደኞቻቸው ፊት ቆመው ለመናገር ተራቸውን ሲጠብቁ ሁለቱም ፈርተው ነበር። መናገር ሲጀምሩ ከንፈራቸው ተንቀጠቀጠ፤ ድምፃቸውም ደካማ ነበር። ወደ ርእሳቸው ሲገቡ ግን ዐይን አፋርነታቸው በመጠኑ ለቀቃቸው ሐሳባቸውን ለመግለጽ በጣም ጉጉዎች ነበሩ።

ንግግሩን ስናዳምጣቸው የራሳችን ልጆች የሆኑ ያህል በጣም ኩራንባቸው። በርግጥ ምንም ዐይነት ሥራ ቢሠሩ እንደሰት ነበር። ነገር ግን እያንዳንዳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ጋር በማገናዘብ ሲያብራሩና በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ሲተገብሩት ስናይ ልባችን ይነቃቃ ነበር።

እኛ እንደ ነበረን የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ወይም በሕዝብ ፊት ቆሞ የመናገር ትምህርት ልምምድ አልነበራቸውም። ነገር ግን እነርሱ ሲናገሩ እንድ በጣም ውብ ነገር አስተዋልን። የአማርኛ ቋንቋን ያለምንም ሰዋሰዋዊ ስሕተት ነበር የሚናገሩት። ለማስታወስ የሚያስቸግር ቃልን በመፈለግ ወይም ትክክለኛውን ግስ በማሰብ ረገድ አላመነቱም። ትክክለኛውን የቃላት አነጋገርና ግልጽ ቃላትን ነበረ የተጠቀሙት። ሲናገሩ መስማት ማራኪ ነበር። በተጨማሪም አድማጮቻቸው ምን ዐይነት ችግር እንዳለባቸው ስለሚያውቁ የተጠቀሙባቸው ምሳሌዎች በዋናው የንግግር ነጥብ ላይ የሚያተኩሩ ነበሩ። የመጀመሪያ ስብከታቸው እኛ ልናደርገው ከምንችለው በላይ በጣም ጥሩ ነበር።

በተከታታይ ሳምንታት ሁሉም ሰው የመስበክ ዕድል አገኘ። እየተለማመዱ በሄዱ ቁጥርም በራስ መተማመናቸው እያደገ መጣ። ጥቂቶች በቤተ ክርስቲያኖቻቸው ውስጥ እሑድ ጠዋት መስበክ ጀመሩ። ከአቃፊ የመጡት ከሌሎች ሁሉ ደፋሮች ነበሩ። ታጠቅና ግርማ ደግሞ በፍጥነት ቋሚ ሰባኪዎች ሆኑ።

ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታችን ጋር የማጎበረ ሰብ ልማት ፕሮጀክቶችንም አቀናጅተን ቀጠልን። በጣም የማያስበን ነገር የግብርና ዘዴአቸው ኋላቀርነት ነበር። በዚህም ላይ ጥቂት ነገሮች ማለት ለም ያልሆነ ዐፈር፣ መጥፎ የአየር ሁኔታ፣ የዝናብ ዕጥረትና የማያቋርጥ ንፋስ መኖር ሊለወጡ የማይችሉ የሁልጊዜ ችግሮች ናቸው። እነዚህ ምክንያቶች ተባብረው በመንዝ ውስጥ የግብርናን ሥራ በጣም አስቸጋሪ አድርገውታል። ይሁን እንጂ ሊሻሻሉ የሚችሉ ጥቂት ነገሮች ነበሩ።

በመንዝ ያሉ ሜዳዎች በሙሉ ማለት ይቻላል በድንጋይ የተሸፈኑ ናቸው። አንዳንዶቹ ላይ እንዲያውም ትልልቅ ድንጋዮች ነበሩ። በጥንት ጊዜ ሜዳውን የሚያጸዱት ባሪያዎች ነበሩ። ነገር ግን ባርነት ስለ ተወገደ አሁን ያንን ሥራ ማንም አይሠራውም። ስለዚህ በድንጋዩ ዙሪያ ምናልባት ባያበቅል በማለት የሚዘራው በቀጭኑ ነበር። ገበሬዎቹ ሁሉንም እህላቸውን ከማጣት ሥጋት ማምለጥ አይችሉም። ከዚህም የተነሣ ሁልጊዜ አዝመራቸው ዘርዘር ብሎ የበቀለ ነው።

አንድ የሙከራ ፕሮጀክት ለመሥራት ከአንድ ሜዳ ላይ ድንጋዮችን የማንሣት ሐሳብ አቀረብን። ወጣት አባትና ዲያቆን የነበረው አቢ ይህንን ለመሞከር ፈቃደኛ ነበር። ከእርሱና ከሌሎች ከእኛ ሸማኔዎች ጋር በመተባበር በእርሱ ማሳ ላይ ለሁሉም ቀናት

ሠራን። ሁለት የአቢ ልጆችም ከእኛ ጋር እኩል ሠሩ። የእጅ ጋሪ በድንጋያማ መልክአ ምድር ላይ በቀላሉ የሚሰበርና አነርሱም መግዛት የሚችሉት ዕቃ ስላልነበር፣ ዕንጨት ላይ በምስማር በተመታ ቆርቆሮ ማለት ቃሬዛ በሚመስል ባሬላ ላይ አድርገን ነበር ድንጋዮቹን እናነሣ የነበረው። ሥራው ጀርባ የሚሰብር፣ እድገቱም አዝጋሚ ነበር፣ ቢሆንም በዚህ መንገድ ሠርተን ጨረስን።

ሬይ ለአቢ ከተለመደው አሠራር ዕጥፍ አድርጎ እንዲዘራ ሐሳብ አቀረበለት። አቢም በቀረበለት ሐሳብ በመተማመን እንደ ተባለው አደረገ። ከዚያም እህሉ አደገ። በእውነትም ማራኪ ነበር። የትም ቦታ ከነበረው እህል ሁሉ ይበልጥ ነበር። አዝመራው በመንገዱ ዳር አጠገብ ስለ ነበርም በዚያ የሚያልፍ ሰው ሁሉ ይመለከተው ነበር።

ቁስ ግርማ አዲስ አበባ በካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ገብቶ ለመማር ለአንድ ዓመት ሥልጠና ሲሄድ በጣም አስጨንቆት ከነበረው ነገር ውስጥ አንዱ ባለቤቱንና ልጆቹን ለረጅም ጊዜ ጥሎ መሄዱ ነበር። አማኞች ቤተ ሰቡን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እንደሚረዱ ቃል ከገቡለት በኋላ ግን ተረጋግቶአል። እህል የሚዘራበት ጊዜ ሰደርስ ምእመናኑ የቁስ ግርማን በሬዎች በመጥመድ መሬቱን ዐርሰው ካዘጋጁ በኋላ እህል ዘሩበት። በተባበሩ ብዙ እጆች ሥራው በፍጥነት ዐለቀ።

አንድ ቀን ቡድኑ በሳምንቱ መጀመሪያ ላይ ያጨደውን እህል በመከመር ለመርዳት ሄድን። የቁስ ግርማ ባለቤት እንደ አስተማሪ ሆና የሚያማምሩ ክምሮችን እንዳይደረመሱና ነፋስ እንዳይወስዳቸው እንዴት ተደርገው እንደሚከመሩ አስተማረችን። በሌላ ቀን ደግሞ ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ጋር በመሆን አተር በመሰብሰብ ረዳናት። አተሩ ብቻ ሳይሆን አዝመራው ሁሉ ተሰበሰበ። ማሳው ላይ እንዳለን አንድ ሰውየ በፈረስ ላይ ሆኖ በፀሓይ አጐንብሰን ስንሠራ ተመለከተን። የውጭ አገር ዜጎች በማሳ ላይ እየሠሩ በማየቱ ማመን አቃተው። ሴትየዋ ስንት እንደምትከፍለን በአቅራቢያው ያሉትን ጠየቃቸው። ለረጅም ጊዜ ዐፍነን የያዝነው ሣቅ ፈንዳ።

ማሳው ከጸዳ በኋላ ተክሉን በትልልቅ ቋጠሮ በማሰሪያ ካሰሩ በኋላ ጭንቅላታቸው ላይ አስተካክለው ተሸክመው አንድ ማይል ያህል ወደሚርቀው ወደ መኖሪያ ቤቱ ተመለስን። እኔ የትንሹን ዮሐንስንና የሁሉንም ጃኬት ተሸከምሁ። ሁሉንም ካወረድን በኋላ ሁላችንም እየተዝናናንና እያወራን ቅዝቃዜና ጨለማ በሰፈነባት ቤታ ውስጥ ተቀመጥን። በዚያ ቤት ውስጥ በብዙ ፍቅርና ሣቅ ቀለል ያለ ምግብ እንመገብ ነበር።

ከጥቂት ሳምንት በኋላ የቁስ ግርማ ሚስት ችግር ገጥሟት ወደ እኛ መጣች። ቁስ ግርማ ባለፈው ዓመት ለበሬዎቹ የሰበሰበው ጭድ ዐልቆበት ነበርና በአቅራቢያዋ ያሉትን ሁሉ ጠይቃ የሚሸጥላት አላገኘችም።

በመንዝ ከቤተ ሰብ የተወረሰው መሬት በየዓመቱ ካልታረሰ መሬቱ ወደ ቀድሞው ቤተ ሰብ ይመለሳል። የቁስ ግርማ እናት ትኖር የነበረው ከነቁስ ግርማ አጠገብ ባለው ግቢ ውስጥ ነበር። በምስጢርም የልጇ ሚስት መሬቱን ለማረስ ዐቅም እንዳይኖራት ትመኝ ነበር። ከዚያም መሬቱን መልሳ ትወስደዋለች። ዕቅዷን ለመተግበርም ወደ የጎረቤቶቿ ቤት እየሄደች ለቁስ ግርማ ባለቤት ምንም ዐይነት ርዳታ እንዳይሰጧት አስጠነቀቀቻቸው።

አማኞቹ የመከልከሏን ወሬ እንደ ሰሙ ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት ጊዜ አልፈጀባቸውም ነበር። ጭድ ሊሸጥ የሚችል ሰው እንዳለ ያውቁ ነበር። የጭድ ሻጩ ሰውዬ መኖሪያ ጥቂት ማይሎች ቢርቅም፣ ያ ትልቅ ችግር አልነበረም። ወዲያውኑ ለጭዱ ገንዘብ አዋጥተው የሚጫንበትን ቀን ወሰኑ።

እኛም መኪናችንንና ተሳቢያችንን ይዘን ወጣን። ልንሄድ የምንችለው በወንዙ ሸለቆ እስከ ድንጋዩ ጫፍ ነበር። ቀጥ ባለው ተራራ ላይ ተራ በተራ ጭዱን ተሸክመው ጫፍ ላይ ቆሞ ወደ ነበረው ላንድ ሮቨር መኪናችን ያመጡ ነበር። ጭዱን በመኪናው ለመጫንና በግቢዋ ለመከመር ሁሉም ተባብሮ ሲሠራ ማየት ጥሩ ኅብረት ነበረን። ችግሩ በዚህ ዐይነት ተወግዶ የቁስ ግርማ ሚስት ከብቶች የሚበሉት ጭድ አገኙ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነው ዲያቆን ታዬም ተመሳሳይ ችግር አጋጥሞት ነበር። አንድ ቀን ከዕርሻ ወደ ቤት ሲመለስ ባለቤቱና ልጆቹ የሉም። ከዶሮዎቹ የተወሰኑት ታርደው፣ ደማቸውም በቤትና በግቢው ውስጥ ተረጭቶ ታየ። እህሉ ተሰርቋል፤ ቤቱም በድንጋይ ተመቶ ነበር። ከዚህም የተነሣ ዲያቆን ታዬ በጣም ዐዘነ።

ጌታ በችግሩ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ጸለይንለት። ዘመዶቹ ንብረቱን ሁሉ ትቶ ከቀያ እንዲወጣና ተስፋ እንዲቈርጥ እንደሚፈልጉ ነገረን። ነገር ግን ጌታ ትዕግሥትን ሰጠውና ከሳምንት በኋላ ባለቤቱ ተመልሳ ወደ ቤት መጣች። ከዚያ በኋላ ዘመዶቹ እርሱን ለማስወጣት የሚደርጉትን ሙከራ አቆሙ።

ዐዲሶቹ አማኞች በሕይወታቸው ችግር ሲያጋጥማቸው፣ ጌታ ለችግራቸው በቂ መፍትሔ እንደ ሆነ ተረዱ። በሳምንቱ ስላገኙት የጸሎት መልስ ይወያያሉ። ጌታ በሕይወታቸው እንዴት እየሠራ እንደ ሆነ ሐሳብ ለሐሳብ ይለዋወጣሉ። ሌሎቹ ሰዎች የእነርሱን ምስክርነት ሲያዳምጡ ይበረታቱ ነበር።

አንድ ቀን በአየር ማረፊያው ቦታ ላይ ትልቅ ሥራ ሠራን። በጥንቃቄ ሁሉንም ዐረም ፈቃደኛ ከሆኑ ሽማኔዎች ጋር በመተባበር ዐረምን። እጃችን ብዙ ቦታ ውሣ ቋጠረ ነገር ግን ዐብረን በመሥራታችን ተደሰትን፤ አየር ማረፊያውንም እንደገና አገልግሎት እንዲሰጥ አደረግን። አገልግሎት ሳይሰጥ በሚያላዝን ሁኔታ የቈየው ግን ሰዐጭር ጊዜ ብቻ ነበር።

ነገር ግን መንገዱ አሁንም አለ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መንገዝ ስንመጣ ከአዲስ አበባ ከግማሽ በላይ የሚሆነው መንገድ አልተነጠፈም ነበር። ከዚያም ውስጥ በዓመት ለበርካታ ወራት ፈጽሞ የማያስኬድ ክፍል አለው። ቀስ በቀስ እየተሻሻለ የካናታ ቤተ ሰብ ከሚኖርበት እስከ መሐል ሜዳ ድረስ ለሁሉም የአየር ጠባይ የሚስማማ መንገድ ተሠራ። ያ ማለት ከመንዝ በዓመት ውስጥ በየትኛውም ጊዜ የቱንም ያህል ጭቃ ቢሆን በመኪና መሄድ እንችላለን ማለት ነበር።

የመንገዱ የመጨረሻው ክፍል ማለት ከመሐል ሜዳ እስከ እኛ መኖሪያ ቤት ድረስ ያለው ግን የተበላሸ ነበር። ትንሽ ዝናብ ሲዘንብ መንገዱ የበለጠ አስቸጋሪ ይሆናል። ሰው ሲንጓዝበትና ሲጨቀይ ተስፋ አስቈራጭ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የዝናቡን ወቅት ስንመለከት፣ በዚያ መንገድ ወንዙን ለማቋረጥ ሲሞክሩ ዐሥራ ሰባት ሰዎች በውሃ በመወሰዳቸው ድልድይ ሠራን። ይህም ማለት ከፀሓይ ሲና መውጣት የምንችለው በእግር ብቻ ነው ማለት ነው። ከዚያ ወዲህ በእኛ በኩል ባለው የወንዝ ክፍል ከዝናብ የተነሣ ችግር አጋጥሞን አያውቅም።

ለፋሲካ ዕረፍት ልጆቻችን አንድ ሳምንት ለመቈየት በአውሮፕላን ወደ እኛ መጡ። የፀሓይ ሲናው አየር ማረፊያ ስለ ተዘጋ እነርሱን ለማግኘት ወደ መሐል ሜዳ በመከራ ሄድን። እኛ ወደ አየር ማረፊያው ለመድረስ የሚፈጅብን ሰዓት አውሮፕላኑ ከአዲስ አበባ ሊመጣ ከሚፈጅበት አርባ አምስት ደቂቃ ስለሚበልጥ በጠዋት ሄድን።

ድልድዩ አጠገብ ስንደርስ ችግር እንደ ተፈጠረ ተረዳን። ሰው ተሰብስቦአል፤ በአየሩ ላይም ጢስ ይታይ ነበር። ተጠግተን ስንመለከት ብዙ የለፋንበት ድልድይ ጣውላ ብዙ ቦታ ላይ ተከፋፍሎ ሊጨስ አየን። ወደ ገቢያ የሚሄዱ ሰዎች ከወንዙ ሠላሳ ጫማ ወደ ታች እሳቱን ለማጥፋት ቡድን ፈጥረው ቆመዋል። የውሃ መቅጃ እንስራዎችን፣ ባርኔጣዎችን፣ ቦርሳዎችንና በቅርብ የተገኙ ሌሎች ነገሮችን ተጠቅመው ነበር።

ድካማቸው ከንቱ እንደ ሆነ ለእኛ ግልጽ ነበር። ድልድዩ ብዙ ተጐድቶ ነበር፤ ተጠግተን ስንመለከት ጣውላዎቹ ላይ ዘይት ፈሶ ነበር። ስለዚህ ለሊቱንም ሲነድ ነበር ያደረው ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ለማቆም መሞከር ምንም ጥቅም አልነበረውም። ልጆቻችንን ማምጣት ስለ ነበረብን ለርዳታቸው አመስግነን ወደ ገቢያ መሄድ እንደሚችሉ ነገርናቸው። ጉልበት ያለው መኪና ስላለን እየተደሰትን ወንዙን በላንድ ሮቨር መኪናችን አቋርጠን በተቃራኒው ወገን ያለውን ዳገታማ መንገድ ዐልፈን ሄድን።

ልጆቻችን በሰዓታቸው ደረሱ። በመኪናችን እነርሱንና ዕቃቸውን ይዘን ወደ ቤት ተመለስን። ወደ ወንዙ ሸለቆ ስንገባ በመንገዱ መሀል የጦር ሰራዊት መኪና ቆሞ አገኘን። የጦር መሣርያ የያዙ ወታደሮች ዙሪውን ከበውት ነበር። ወደ ላይ ፊታቸውን አዙረው ድልድዩን በማፍረስ የሚዋጉአቸውን ዐማፅያን በንቃት ይጠብቃሉ።

መኪናችንን ከኋላቸው አቆምን፤ ወዲያውኑም መኪናችንን አዙረን እንድንመለስ አዘዙን። ይህን ትእዛዝ ሰጥተውን መመለስ እንደ ጀመርን ተኩስ ጀመሩ። ሁለት ጊዜ መጠየቅ አላስፈለገንም። ከጠመንጃው ተኩስ የተቈራረጠ ድምፅ በኋላ ኩረብታውን ተመልሰን በመውጣት ከሸለቆው ወጥተን ሄድን። ወዲያውኑ ወደ መሐል ሜዳ መመለስ እንችል ነበር፤ ነገር ግን ልጆቻችን ሰብዙ ወራት ከቤት ርቀው ቈይተው ስለ ነበር ወደ ቤት ለመሄድ በጣም ጓጉ።

ከዚያም ከወንዙ ትይዩ በነበረ አሮጌ መንገድ ላይ መጓዝ ጀመርን። መንገድ ላይ ጥቂት ገበሬዎች ረድተውን በቤታችን አቅራቢያ ያለውን ወንዝ በማቋረጥ የዋናውን መንገድ አቅጣጫ ተከትለን መሄድ ቻልን። ድልድዩ ከቤታችን ስድስት ማይል ነው የሚርቀው። በዚያ ሳምንት ወታደሮቹ ወደ እኛ ገና አልተጠጉም ነበር። ጌታን አመሰገንን።

ድልድዩ በተቃጠለ ማግስት በርቀት በሚገኘው ጉዋሳ በሚባል የግጦሽ ስፍራ ላይ አንድ አውቶቡስ ወደ አዲስ አበባ ረጅሙን ጉዞ ከጀመረ አንድ ሰዓት ተኩል በኋላ ጥቃት እንደ ደረሰበት ወሬ ደረሰን። ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ቦታ ዐማፅያን ሁለት ጊዜ መንገዱን መዝጋት ችለው ነበር። በእነዚያ ሁለት ጊዜያት አውቶቡሱ ወደ መጣበት ነበር ዞሮ የተመለሰው፤ በዚያ ቀን ጠዋት ግን አጋጣሚው ጥሩ አልነበረም።

አድፍጠው የሚጠብቁ ሰዎች አውቶቡሱን በጠመንጃ አሳድደው አስቁመው ሹፌሩንና ፖሊሱን ገደሏቸው፤ ብዙዎችን ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ አቁሰሏቸው ንብረታቸውን ዘርፈው ከጨረሱ በኋላም ተሳፋሪ ዎችን ሰቀቋቸው። በዚያ ቀን ከሰዓት ላይ በጣም የተጐዱትን ተሣፋሪ ዎች ቍስል ሳም ሲሰፋ ነበር። ከዚያ ሁኔታ በኋላ የአውቶቡስ ድርጅቱ ወደ መንዝ እየሄደ ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት አቆመ።

በተጨማሪም ዐማፅያኑ በመሐል ሜዳ ያለውን ስልክ የሚያገናኙ የስልክ መሥመሮችን ቈረጡ፤ ጥቂት ምሰሶዎችንም ነቀሉ። በመንዝ በየቦታው ያለ ማቋረጥ ጥቃት ቀጠለ። የመንግሥት ወታደሮችም ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ መሯሯጥ ቀጠሉ። የሚሰነዝሩት ጥቃት ፈጣንና ውጤታማ ነበር። ዐማፅያንን በቤታቸው በማስቀመጥ የሚጠረጠሩትንና የማይታመኑትን ሰዎች ቤትና አዝመራ አቃጠሉ።

በመንዝ በየቦታው ነገሮች ስላልተረጋጉ ዐዲሶቹ አማኞች መገለል አልደረሰባቸውም ነበር። የሰላም ጊዜ ነበራቸው። ሰዎች ስለ እነርሱ ከመጨነቅ ይልቅ ብዙ በግል የሚያሳስቧቸው ነገሮች ነበሩ። በመጨረሻ ለመማርና ለማደግ ነጻ ስለ ነበሩ በዚህ ተጠቀሙ።

ጴጥሮስም እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፤ «እግዚአብሔር ለማንም አንደማያዳላ በርግጥ ተረድቻለሁ፤ ነገር ግን እርሱን የሚፈልጉትንና ጻድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላቸዋል።

የሐዋርያት ሥራ 10÷34-35

ማኅበራዊ መገለል

እስካሁን ድረስ አንዳንድ ጊዜ ስለ ውኽይ እናስባለን። ለማስተማር ያደረግናቸው የመጀመሪያ ሙከራዎች ያመጡት ውጤት የተቀደደ ድንኳንን ማስገኘት ብቻ ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ጥቂት ዲያቆናትና አንድ ቄስ ከውኽይ እየመጡ በታማኝነት ቋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ሆነው ነበር። እነዚህ ሰዎች ስለውኽይ ሁለተኛ ዕድል እንድንሰጥ ይለምኑን ነበር።

በተለይ ደግሞ አውላቸው በጣም ይጨቀጭቀን ነበር። ስለዚህ መጨረሻ ላይ በሐሳቡ ተስማማን። በቀጣዩ ትልቅ በዓል ላይ የእርሱን ቤተ ክርስቲያን እንድንገበኝ ሁኔታዎችን አመቻቸልን። በዚያን ቀን ስንደርስ ሰዎቹ ሞቅ ባለ ሁኔታ ተቀበሉን። እንዲያውም በቅዳሴ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንድንገባ ጋበዙን። ከዚያ በኋላ ሬይን በግቢ ውስጥ ይሰብክ ዘንድ ጠየቁት። እንደ ተለመደው ያገኘውን ምቹ ጊዜ በመጠቀም ስለ ኢየሱስ ነገራቸው።

ከስብከቱ በኋላ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ባሉ ብዙ ትናንሽ ጎጆ ቤቶች ውስጥ ሰዎች በቡድን ተከፋፈሉ። ይህም ማኅበር የሚባለው ነው። እያንዳንዱ ቡድን በአንድ ቅዱስ ስም ይሰየምና አባሎቹን ይመርጣል። በየትኛውም ቡድን ያልተመረጡት ውጭ ይቆማሉ። በቡድኑ ውስጥ አባሎቹ ያዘጋጁት ብዙ ዳቦና ጠላ አለ። ልዩ ልዩ ሥርዐት ከተፈጸመ በኋላ ይባረክና መብላትና መጐበኛኘት ይጀምራሉ። የሚተርፍ ምግብ ካለ በውጪ ለሚጠብቁ ድኾች ይሰጣል።

የዚያን ቀን ከመሄዳችን በፊት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ እኛ መጡና የምንጣፍ ሽመና ወይም ሌላ የእጅ ሥራ ትምህርት ወደ ውኽይ መጥተን እንድናስተምር ጠየቁን። በመጨረሻ ላይ ጥሩ መስተንግዶ አድርገውልን ነበር። እኛም በጉዳዩ ላይ እንደምናስብበት ቃል ገባንላቸውና በቀጣዩ ወር በዓል ላይ ተመልሰን እንደምንሄድ ነገርናቸው።

ከብዙ ወራት በፊት ከሰዓት በኋላ ባለው ጊዜ ወደ ቤታችን በመኪና እየሄድን ሳለ አትኩሮታችን መንገድ ዳር ላይ ቆሞ በነበረ አንድ ልጅ ላይ ዐረፈ። መኪናችንን እንድናቆም እጁን እያውለበለበ ነበር። ባለፉት ጥቂት ወራት ልጁን ብዙ ቦታዎች ላይ አይተነዋልና ፊቱ ዐዲስ አልሆነብንም። ቀኝ እግሩ ከጕልበቱ በታች

የሰለለ ስለ ነበር የሚራመደው በዱላ እየተደገፈ በግራ እግሩ ብቻ ነበር።

ስሙ ወልደ ጻድቅ እንደ ሆነ ነገረንና የእጅ ሥራ እንድናስተምረው ጠየቀን። ስድስተኛ ክፍል ድረስ የደረሰ ቢሆንም፤ ትምህርቱን ለመቀጠል ከቤተ ሰቡ ርቆ መሄድ ነበረበት። ቤተ ሰቦቹ እርሱ መሐል ሜዳ ሄዶ በዚያ እየኖረ እንዲማር ለማድረግ ዐቅሙ አልነበራቸውም። ወልደ ጻድቅ አካል ጕዳተኛ ከመሆኑ የተነሣ አነርሱን ብዙ ለመርዳት አልቻለም።

በዚያን ጊዜ ሬይ የምንጣፍ ሽመና ያስተምር ነበር ነገር ግን አንድ ሽማኔ ቀኑን ሙሉ በመቆም ለሥልጠናው ሁለት እጆቹን መጠቀም አለበት። ለወልደ ጻድቅ የምንጣፍ ሽመና ትምህርት አይስማማውም። ወዲያውኑ ምንም ዐይነት የዕጅ ሥራ እርሱን ልናስተምረው አልቻልንም። ነገር ግን ወደ ፀሓይ ሲናው የክትትል ትምህርትና የእሑድ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲመጣ ጋበዝነው።

በዚያ አካባቢ በሚሰጡት ትምህርቶች ሁሉ ላይ ወልደ ጻድቅ በታማኝነት ይገኝ ነበር። ትምህርት ቤት ገብቶ ስለ ነበር ማንበብ ይችላል፤ ፍጥነትም ነበረው። አካል ጕዳተኛ ቢሆንም ሁልጊዜ ፊቱ ላይ ፈገግታ አይጠፋም፤ ወዲያውኑም ብዙ ጓደኞች አገኘ። ወደ ቀያ ልናስተምር ስንሄድ ወልደ ጻዲቅ ዐብሮን ይገኝ ነበር። በቀላሉም በዚያ የነበረው ቡድን አባልና ብዙም ሳይቈይ ዳግም የተወለደ አማኝ ሆነ።

አንድ ቀን ትምህርት ካለቀ በኋላ ወልደ ጻድቅ እኛን ሊያናግረን ወደ ኋላ ቀረ። በጣም ያልተለመደ ታሪክ ሊነግረን ጀመረ። ከጥቂት ወራት በፊት በአቅራቢያው አንድ ፈረስ ሞቶ ነበር። ነገሩ ከተከሠተ በኋላ ጎረቤቶቹ ስብሰባ አድርገው የወልደ ጻድቅ ቤተ ሰብ ጥፋት እንደ ሆነ ወሰኑ። በውሳኔውም መሠረት ሰሞተው እንስሳ ቤተ ሰቦቹ ሃያ ሦስት ብር እንዲከፍሉ ታዘዙ።

የወልደ ጻጽቅ ቤተ ሰቦች የተጠየቁትን ከመክፈል ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። ስለዚህ ገንዘቡን ለማሰባሰብ እንቅስቃሴ ጀመሩ። ያን ያህል ብር በእጃቸው ስላልነበረ፤ ጥቂት ነገሮችን መሸጥና ከዘመዶቻቸው መበደር ነበረባቸው። ይህ ውሳኔ በእነርሱ ላይ ትልቅ ችግር ፈጠረባቸው። በመጨረሻ ላይ ገንዘቡን ሲያገኙ ለፈረሱ ባለቤት ከፈሉ። ከሳምንት በኋላ የሰውየው ትንሽ ልጅ ሞተ። ሐዘን ተሰምቶት ስለ ነበር ሃያ ሦስቱን ብር አምጥቶ በንዴት ወረወረባቸው። እርሱንና ቤተ ሰቡን የማይተናኰሉና ድጋሚ የማይረብሹ ከሆነ ብሩን መውሰድ እንደሚችሉ ነገራቸው።

ታሪኩ ለእኛ ምንም ዐይነት ትርጕም አልሰጠንም። የተከፈለውን ሊያመጣጥን የሚችል ምክንያት በግልጽ አልታየም። ያልገባን ነገር እንደ ነበር ግልጽ ነው። ስለዚህ እንደገና እንዲነግረን ወልደ ጻድቅን ጠየቅነው። እርሱ ወይም ቤተ ሰቡ እንስሳውን ነክተው

ወይም የሆነ ነገር አብልተውት ይሆን? ጥያቄውን አልተቀበለውም። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ እንደሚሆነው ስለ ሁኔታው ምንም ሳይገባን ተስፋ ቁርጠን ተውነው። ለዚህ ሕዝብ ባህል በትክክል እንግዶች እንደ ሆንን አስተዋልን።

ታሪኩን ነግሮን ከጨረሰ በኋላ ወልደ ጻድቅ የሚጠይቀው ሌላ ነገር ነበር። እግዚአብሔር ከሰይጣን የበለጠ ጎይለኛ እንደ ሆነ ስናስተምር ቈይተናል። ላለፉት ጥቂት ሳምንታት እናቱ ትንቀጠቀጥና ድግምትም ትደግም ነበር። በዲያብሎስ እየተሠቃዮች እንደ ሆነ ተሰማው። ሄደን እንድንጸልይላት ዐሰበ ይሆን?

ከወንዙ ባሻገር ወዝይ እንደሚኖር ነገረን። በቀጣዩ ማክሰኞ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተመልሰን ለመሄድ ቀጠሮ ነበረን። ሁለቱን ጉዞዎች ማቀላቀል እንችላለን። ለመሄድና ችግሩን ለጌታ ለመስጠት ተስማማን። በሁለቱም ቦታዎች ምን እንደሚጠብቀን ስለ ማናውቅ ብቸኛው ጎይላችን ጸሎት ነበር። ከዚህም የተነሣ በዚያ ሳምንት ብዙ ጸለይን።

በዚያ ቀን መኮ ዐብሮን እንዲሄድ ጠየቅነው። ቤተ ክርስቲያን ስንደርስ ብዙ ሕዝብ ውጪ ተሰብስቦአል። ቅዳሴም ተጀምሮአል። ቅጥር ግቢው ውስጥ ስንገባ ማንም አልተቀበለንም ወይም እንድንሳተፍ አልጋበዘንም። ስለዚህ ቁጭ ብለን መጠበቅ ጀመርን። መጨረሻ ላይ ቅዳሴው ዐለቀና ሰው ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ግቢ ወጣ። ከዚያም አንድ ሽማግሌ ቄስ ለየት ያለ ረጅም ምንባብ በግእዝ ቋንቋ ከድርሳነ ሚካኤል አነበበ። እኛን እንደማንታይ ያህል ነበር ችላ ያሉን።

በመቀጠልም ዐብረውን ለመብላት ወደ ትናንሽ ጎጆ ቤቶች ገባን። በዚያ ጊዜ ከአንደኛው ቡድን ጋር እንድንቀላቀል አጥብቀው ጠየቁን። በተቻለ መጠን ባህላቸውን ለመከተል ስለምንሞክር አልተቃወሙም። ጎጆ ቤት ውስጥ ከሰዎቹ መካከል አንዱ በጀርባው ላይ ብዙ ዳቦ ተሸክሞ በእጁ በመደገፍ ተንበረከከ። ሰውየው ሲንበረከክ ቂሱ በእርሱ ላይ እጁን ዘርግቶ ጥቂት ቃላትን ተናገረ።

ከዚያም ምግብ በአንድነት ከተመገቡ በኋላ መወያየት ጀመሩ። በአካባቢያችን ምን እየተካሄደ እንደ ነበረ ለመረዳት እየሞከርን ሳለ ሦስታችንም ስለ ሁኔታው ተመሳሳይ ግንዛቤ ነበረን። በዚያ ክፍል ወይም እየተፈጸመ በነበረው ሥርዐት እግዚአብሔርን የሚያከብር አንዳች ነገር የለም። ከዚያ የበለጠ እዚያው መቈየት እንደሌለብን ተሰማን። በጥድፊያ ሰዎቹን ተሰናብተናቸው ወደ መኪናችን ተመልሰን ሄድን። እኛን በዚያ ለማቈየት የሞከረ ሰው አልነበረም። እግዚአብሔር በውኽይ ሥራ እንዳንጀምር በድጋሚ በሩን ዘጋው።

የወልደ ጻድቅ መኖሪያ ቤት ሁለት ማይል ይርቅ ነበረ። እዚያ ስንደርስ እርሱ መንገድ ላይ ሆኖ ይጠብቀን ነበር። ከመኪናው ፊት ለፊት ቀደም ቀደም ለማለት እየሞከረ በቅርቡ ወደሚገኘው

ቤቱ መራን። ቤታቸው ደርሰን ከግቢው ፊት ለፊት መኪናችንን ስናቆም የተለየ ነገር ተመለከትን። በግቢው ውስጥ የተሰባበሩ ሽክላዎች በቦታው ተጥለው ይታዩ ነበር፤ ዘመዶቹ ሽክላ ሠሪዎች እንደ ሆኑ ተረዳን። እስከምናውቀው ድረስ ሽክላ ሠሪዎች በጎብረተ ሰቡ የተገለሉ ሰዎች ናቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ርግጠኛ ለመሆን ያህል መኮን ጠየቅነው። መኮ ስለ ባህሉ እኛ ከምናውቀው የተለየ ብዙ ነገር አያውቅም ነበር፤ እርሱም ተመሰሳይ አስተሳሰብ ነበረው። ጓደኞቻችን ከጎብረተ ሰቡ የተገለሉ ሰዎች ናቸው ማለት ነው።

የተገለሉ የሚለው ቃል ለአንደበታችን እንግዳ ሆነብን። ይህን ሐሳብ የምናያያዘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ጋር እንጂ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ጋር አይደለም። ነገር ግን ወደ መንዝ ስንሄድ የተገለሉ ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ እንዳሉና እንደ ቀድሞው ዘመን እንደሚፈሩና በጥሩ ነገር እንደማይታወቁ ተረዳን።

በመንዝ ከአያንዳንዱ ዐምስት ወይም ዐሥር ማይል በኋላ የሸክላ ሠሪዎች ግቢ ይገኛል። እንደነዚህ ዐይነት ሰዎች በጎብረተ ሰቡ ውስጥ ይህን የመሰለውን ስም የሚያገኙት ከተገለሉ ወላጆቻቸው በተወለዱ ጊዜ ነው። ይህን የሚቀይሩበት ምንም ዐይነት መንገድ የለም። ሁልጊዜ ጋብቻ መመሥረት የሚችሉት በተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ካሉት ጋር ብቻ ነው። ስለዚህ ይህ ሁኔታ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚቀጥል ነው።

የተገለሉ ሰዎች የዕርሻ መሬት እንዲኖራቸው አይፈቀድም፤ ነገር ግን ማንም ለመሥራት በማይፈልግበት ኰረብታማ መሬት ላይ እንዲያደርሱ ይደረጋል። ስለዚህ ለግብርና ሥራ የሚሆነውን ትክክለኛ መሬት ለማግኘት መወሰን ስለማይችሉ ለገቢ ምንጭነት የእጅ ሥራ እየሠሩ ለመኖር ይገደዳሉ። እንደ እጅ ሙያ ሰዎች በመንዝ ብቸኛ የብረታ ብረት ነጋዴዎች ወይም ሠራተኞች እነርሱ ናቸው። እያንዳንዱ ገበሬ ለሥራው የሚጠቀምበትን ማረሻና ማጭድ ቀጥቅጠው ያበጃሉ። በመጀመሪያ የብረት መሣሪያቹን ይቀጠቅጣሉ ከዚያም እንደ ተፈለገው ይስሏቸዋል።

በተጨማሪም የሸክላ ሥራ ይሠራሉ። ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ጊዜ በፈጣ የሸክላ ሠራተኞች ይባላሉ። በዚህ ሙያ በጣም የተካኑ ስለ ሆኑ የሚያማምሩ የሸክላ የወጥ ቤት ዕቃዎችን ይሠራሉ። ለሚሠሯቸው ዕቃዎች ሰዎች ለመክፈል የሚፈቅዱት ገንዘብ ላይ ጥገኛ ስለ ሆኑ፤ ገቢ ለማግኘት ጠንክረው መሥራት አለባቸው።

በመንዝ ማንም ብረታ ብረት ለመቀጥቀጥ ወይም ሸክላ ለመሥራት አያስብም። እንዲያውም ገበያ ላይ እንደዚህ ዐይነት ዕቃ መሸጥ ከአነርሱ መካከል እንደ ሆነ ያስቄጥራል። የተገለሉት ሰዎች በተጨማሪም ልብስ ይሸምናሉ፤ ሌሎች የእጅ ሥራዎችንም ይሠራሉ። ነገር ግን እነዚህ የእጅ ሙያዎች ለተቀሩት ሰዎች የተለመዱ ነበሩ። በቤተ ክርስቲያን እነዚህ ሰዎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ነው

የሚታዩት። ዲያቆን ወይም ቄስ ለመሆን ወይም በየትኛውንም መንገድ የሃይማኖት መሪ ለመሆን ደረጃውን ማሻሻል አትችሉም። በቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ውስጥም ተቀባይነት ያገኙ የሚመስሉት እንዲሁ ዳር ቆመው ስለሚሳተፉ ነው።

የተገለሉ ሰዎች በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ፈላሻ ተብለው ስለሚጠሩ የአይሁድ ዘር ነን ይላሉ። እስካሁን ድረስ የብሉይ ኪዳን የአይሁድ ሕግጋትን በጥብቅ ሲከተሉ ይታያል። በመንዝ ይህን ቅርስ ባጠቃላይ የረሱት ይመስላሉ። ጥቂቶቹ ሲያረጁ ወደ መጡበት ይመለሱና እስኪሞቱ ድረስ ከዚያ ይቀመጣሉ።

ማኅበራዊ መገለል የደረሰበት ሰው ሆኖ መገኘት ከሚያመጣቸው ችግሮች ውስጥ ሰዎች ቡዳ እንደ ሆኑ ማመናቸው መጥፎውና ከዚህ ሁሉ የከፋ ነው። የቀረው ሕዝብ በእነዚህ የተረገሙ ሰዎችና እነርሱ ሊያስከትሉት በሚችሉት ጉዳት በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ ይኖራል። የሕዝቡ ፍርሃት በተለይ ሲጨልም ይልቁንም ሊነጋጋ ሲል ባሉት ሰዓት ይጨምራል። ብዙዎች የተገለሉት ሰዎች ሲመሽ ወደ ቀበሮነት ተለውጠው መቃብር እንደሚዘርፉ ይታመናል፤ ብዙዎች ደግሞ በሽታን ወይም ሞትን የሚያመጣ ርግማን እንደሚያወርዱ ያምናሉ።

ከዚህም የተነሣ በገበያ ቀን የሸክላና የብረታ ብረት ሥራዎቻቸውን ለመሸጥ በተለየ ቦታ ላይ እንዲቀመጡ ይገደዳሉ። ሰዎች ከእይታቸው ይሸሻሉ፤ መንገድ ላይም ሲያገኟቸው ዘወር ብለው ያሳልፏቸዋል። ከእነርሱ ጋር መብላትም ሆነ በአንድ ክፍል ውስጥ መተኛት የሚታሰብ አይደለም።

በመንዝ ያሉ ትንንሽ ልጆች ሁለት ለየት ያለ የፀጉር አቈራረጥ ነው ያላቸው። ሁሉም ፀጉራቸው ይላጭና ፊት ላይ ብቻ ትንሽ ፀጉር (ቋንጮ) ይቀራል። ወላጆች ይህ ዐይነቱ የፀጉር አቈራረጥ ቡዳው በዐይኑ ተመልክቶ እንዳይጎዳው ያደርጋል ብለው ያስባሉ። በተጨማሪም ወላጆች ይህንን አስፈሪ ነገር ለመከላከል ለልጃቸው ክታብ ያደርጉለታል።

ከቤቱ ውጪ ያለውን የሸክላ ስብርባሪ ስንመለከት ይህ ሁሉ በአእምሯችን መጣ። በተጨማሪም የሞተው ፈረስ ታሪክ ትዝ አለን። በመጨረሻ ላይ ትርጉም ሰጠን። የአካባቢው ሰዎች የወለደ ጻድቅ ቤተ ሰብ በቡዳ ዐይናቸው ፈረሱን እንደ ገደሉት ዐሰቡ።

ከጅምሩ በመንዝ የተገለሉ ሰዎች እንዳሉ እናውቅ ነበር ነገር ግን ከመንዝ ሕዝብ በመቶ ሦስት እጅ ፐርሰንት ብቻ ነበሩ። ከሚበዙት ኦርቶዶክሰውያን ጋር ሲሳካልን ከእነርሱ ጋር ለመሥራት ዐሰበን ነበር። ጥቂት የተገለሉ ሰዎችን አግኝተን ነበር በጣም ጥሩ ሰዎችም እንደ ሆኑ እናውቅ ነበር ነገር ግን የሚሆነው እኛ እስከምናውቀው ድረስ ነበር።

ወደፊት ምን እንደምናገኝ ለማወቅ በጣም እየጓጓን ከመኪናው ወጣን። ወልደ ጻድቅ እናቱን ሰይጣን እያሠቃያት ነው ብቻ ሳይሆን፣

ርኩስ መንፈስም ሊኖርባት ይችላል ነበር ያለው። ነገር ግን የተገለሉ ነበሩ። የሆነው ሆኖ ቤተ ሰቡ ሞቅ ባለ ሁኔታ ተቀበሉን፤ ወደ ውስጥም እንድንገባ አጥብቀው ለመኑን። ቤቱ ተጠርጎ ንጹሕ ሆኖ ነበረ እነርሱም የክት ልብሳቸውን ለብሰው ነበር። የመንዝ ሰዎች እንደሚያደርጉት ለእኛ የሚበላና የሚጠጣ በማዘጋጀት ራሳቸውን በሥራ በመወጠር ፈንታ ከእነርሱ ጋር ተቀምጠን እንድንነጋገር ጠየቁን።

የወልደ ጻድቅ እናት ለመናገር የጓጓችበት ነገር ነበራት። ልጇ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ መገኘት ከጀመረ ጊዜ አንሥቶ ያልተለመዱ ነገሮችን ማስተዋል እንደ ጀመረች ነገረችን። ሁልጊዜ ትምህርት ወይም ስብከት ሰምቶ ሲመጣ በቀጥታ ወደ ቤት ይመጣና የተማረውን ሁሉ ይነግራቸዋል። የመማር ዕድል በማግኘታቸው ሁሉም ደስተኞች ነበሩ።

እናቱ አንድ ነገር መሥራት እንዳለባት ማለት ወደ አንድ ቦታ ለመሄድ ወይም ጓደኛ ለመጠየቅ ስታስብ፣ ትንሽ ቡና አፍልታ ሲኒ የማየት ልምድ እንዳላት ነገረችን። ጀበናውና ዐብሮ የሚቀርበው ደመቅ ያለ ቀለም ያለው ጨርቅ የመጣው ከጠንቋይ ዘንድ ነው። የተለያዩ ሥርዐቶችን በማማለያ ዕንጨት እጁታ ከፈጸመች በኋላ ጢሱን በመመልከት መልሱን ታገኛለች። ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነገሮች እየተበላሹባት መጡ። ሁልጊዜ ይህን ማድረግ ስትጀምር ትንቀጠቀጥና መሬት ላይ ወድቃ ትንከባለላለች።

ስለ ችግሯ ከወልደ ጻድቅ ትምህርት ጋር በማነጻጸር ስታስብ የምታደርገው ነገር ስሕተት እንደ ሆነ ተረዳች። በእግዚአብሔር ፈንታ ሰይጣንን እያመለከች ነበር። ሌሎች ጥቂት ክታቦችም ነበሯት። ታሪኳን እየነገረችንም ሳለ፣ ከጠንቋዩ ያመጣቻቸውን ዕቃዎች በሙሉ አምጥታ እግራችን ሥር ደረደረቻቸው። ወዲያውኑም «ይህን ሁሉ አቃጥሉት፤ ድጋሚ ይህን ማየት አልፈልግም። ይህንን መያዝ ትክክል እንዳልሆነ ዐውቄአለሁ። ከአሁን ጀምሮ እምነቴ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው» አለች።

በጣም ደነገጥን። ሴት ነበረች ይህን የምትናገረው። እኔ ለዐምስት ዓመት ሴቶችን አስተምሬአለሁ። ስለ ሆነ ነገር ምን እንደሚያስቡ ስጠይቃቸው ሥቀው፤ «እኛ ምንም አናውቅም። ሴቶች ነን» በማለት መለሱልኝ።

ሴቶች መማር እንዳለባቸው ለማሳመን ከፍተኛ ጥረት አድርጌ ነበር። ነገር ግን ጥረቴ ምንም ዐይነት ውጤት አላመጣም። ለአንድ ቀን እንኳ ትምህርት ቤት ሄደው አያውቁም። ከቤት ሥራቸው በስተቀር ሌላ አስተያየት እንዳላቸው ማንም ሰው ጠይቋቸው አያውቅም። በተደጋገሚ ምንም እንደማያውቁ ተነግሯቸዋል። ስለዚህ ማመናቸው አስገራሚ አይደለም።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የተናገራትና የሰማችውም አንዲት ሴት ነበረች። ያች ሴትዮ በነጻነት የተሰማትን ለእኛ ገለጸችልን። ከዚያም መናገር ያለባት ለእግዚአብሔር እንደ ሆነ ነገርናት። ጎጢአት የሠራችው በእግዚአብሔር ላይ ስለ ነበር ይቅር ሊላት የሚችለው እርሱ ብቻ ነበር። ለጎጢአቷ መቀጣት የለባትም ኢየሱስ ዋጋ ከፍሏልና።

በዚህን ጊዜ በመንዝ ከእግዚአብሔር ጋር በምኞት የሚነጋገሩት ጥቂት ቀሳውስትና ዲያቆናት ብቻ ነበሩ። ሴት መጸለይዋ የማይታወቅ ነገር ነበር። ለመምራት ወሰንን፤ አንድ አረፍተ ነገር ስንናገር እርሷ ከእኛ ኋላ ትደግመዋለች። የጸሎት ሐሳብ ገብቷት ሐሳቧን በዚያ እንድትገልጽ መጠበቅ ከእርሷ ዐቅም በላይ ብዙ መጠየቅ ነው።

ራሳችንን ዝቅ አደረግንና መከ በመጀመሪያ ጸለየ። ከዚያም ሴትዮዋን ለመምራት ሲዘጋጅ በራሷ መጸለይ ጀመረች። ጸሎቷ ቀላልና ግልጽ ነበር፤ «እግዚአብሔር ሆይ ሕይወቴን በሙሉ ታውቃለህ ከቤተ ሰቤ ሰው ሲታመም ወይም አንዳች ነገር ስፈልግ ወደ ጠንቋይ እሄድ ነበር። የሰይጣን ፍራቻ በሕይወቴ ትልቅ ስፍራ ይዞ ስለ ነበር፣ እርሱን ለማክበር ብዙ ነገር ሠርቻለሁ። አሁን ያ ሁሉ ስሕተት እንደ ሆነ ተረድቻለሁ፤ ይቅርታ አድርግልኝ ማለትም እፈልጋለሁ ድጋሚ ያንን ማድረግ አልፈልግም። ከአሁን ጊዜ ጀምሮ በኢየሱስ ብቻ ማመን እፈልጋለሁ አሜን» አለች ጸሎት ምን ማለት እንደ ሆነ እንደ ተረዳችና በዚያን ጊዜ መላእክት በመንግሥተ ሰማያት እየተደሰቱ እንደ ነበር ምንም ጥርጣሬ አልነበረንም።

እርሷ ጸልያ እንደ ጨረሰች ወዲያውኑ ትልቋ ሴት ልጇ በበኩሏ መጸለይ ጀመረች። ከባሏ ተፋትታ የመጣች ወጣት ሴት ነበረች። አንድ ልጇ ሞቶባት ነበር። እርሷም ልቧን ለጌታ አፈሰሰችና ሕይወቷን እንዲረከብ ኢየሱስን ጠየቀችው። ከዚያም ሌላዋ ሴት ልጇ ጸለየች። የወልደ ጻድቅ ተራ ሲደርስ ደስታውን መቋጣጠር አቃተው። በተጨማሪም ሁለት ወንድሞቹና የወንድሙ ሚስት በዚያ ስለ ነበሩ፣ ይባል ነበረውን ነገር በሙሉ በጥንቃቄ አደመጡ። ይሁን እንጂ በዚያ ቀን አልተቀላቀሉም።

ከመሄዳችን በፊት በሌላ ጊዜ ተመልሰን መጥተን በቤታቸው ፊልም እንድናሳይ ጠየቁን። በዚያን ቀን ሌላ ሰው የሚመጣ ስለ መሆኑ በመጠራጠር አመነታን። ሐሳባችንን አነበቡና፣ «ጎረቤቶቻችን ሁሉ ይመጣሉ ብለን እናስባለን። እኛን ከመፍራታቸው በላይ ሲኒማ ይወዳሉ። በተጨማሪም በምሽት ወቅት ከእኛ ጋር መሆንን እንደ መጥፎ ነገር አይመለከቱትም» በማለት በፍጥነት ጥርጣሬያችንን አስወገዱልን።

ስለዚህ በዚያ ቦታ ፊልም ማሳየት ጀመርን። ወልደ ጻድቅና አንድ ጓደኞችን በአቅራቢያው ወዳሉት ቤቶች ሁሉ እየሄዱ የእኛን መምጣት ተናገሩ። ስንደርስ በሰው የታሞላ ቤት አገኘን። በአንድ ክፍል

ውስጥ ሰባ ሰው ለማስቀመጥ ቻለ። የጠነከረ ጎብረት ነበረን። ከፊልሙ በኋላ ወልደ ጻድቅ ሰበከ። በጣም ጥሩ ነበር። ሰዎቹም ስብከቱን ከመውደዳቸው የተነሣ ሲያልቅ መሄዳቸውን እንኳ አልወደዱትም በሚቀጥለው ሳምንትም እንድንመጣ ቃል አስገቡን።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ቀያ ለማስተማር ስንሄድ፣ የወልደ ጻድቅን ስም ሳንጠቅስ ታሪኩን በሙሉ ነገርናቸው። እኛ እንደ ተሰማን ሁሉም በታሪኩ ተደንቀውና ተደስተው ነበር። በመጨረሻ ላይ ባለ ታሪኩ ወጣት ልጅ ጓደኛቸው እንደ ሆነ ገለጽንላቸው። ወዲያውኑ ወጣቱ ልጅ ማን ሊሆን እንደሚችል መገመት ጀመሩ። መጨረሻ ላይ ማንነቱን የግድ መናገር ነበረብን። ለማመን ተቸገሩ። ወልደ ጻድቅ በጣም ጥሩ ሰው ነበር። ማኅበራዊ መገለል የደረሰበት ሰው ከዚህ በፊት ጥሩ ጓደኛ መሆን እንደሚችል ዐስበው አያውቁም። ስለ እርሱ ብዙ ዐሰቡ። በዚያን ጊዜ እርሱን መጥላት እንደማይችሉ በግልጽ የሚታይ ስሜት ነበራቸው። እግዚአብሔር ሁሉንም እንደሚወድ በማሳየት ለወልደ ጻድቅ የሚገልጹትን ፍቅር ለያንዳንዳቸው ሰጣቸው።

ማኅበራዊ መገለል የደረሰባቸው ሰዎች ስለ ነበሩ፣ የወልደ ጻድቅ ቤተ ሰብ አባላት በሕይወታቸው ሁሉ ስደት ነበረባቸው። ወልደ ጻድቅ የአህያ ሥጋ በልተዋል ተብለው በተከሰሱት ሰዎች ላይ የደረሰባቸውን ያውቅ ነበር። ይሁን እንጂ ከዚያ ሁሉ በላይ በሕወታቸው የጌታ ደስታ እንደ ነበራቸው ተመለከተ። ጥቂቶቹ ወደ ቤቱ መጥተው እምነታቸውን ለቤተ ሰቡ እንዲያካፍሉና እንዲጸልዩ ጠየቁ። ታጠቅና ግርማ ጥያቄውን በደስታ ተቀበሉት። እነርሱን ወደ ውኽይ ወሰድናቸውና ልምዳቸውን ሲያካፍሉና በአንድነት ሲጸልዩ በግልጽ የሚታይ አንድ የመሆን መንፈስ ነበራቸው። በሚቀጥለው ጊዜ በዚያ ፊልም ስናሳይ ግርማ ዐብሮን ሄዶ ፊልሙ ታይቶ ሲያልቅ ሰበከ።

በውኽይ ጌታ በር እንዲከፍትልን ጸልየን ነበር። ነገር ግን የጠበቅነውን በር እግዚአብሔር አልከፈተም። በዚያ ፈንታ መሽሎኪያ በር ከፍቶ አስደነቀን። ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፣ በትክክለኛው ጊዜ በትክክለኛው ቦታ ተገኝተን በበሩ ለመግባት በመቻላችን እግዚአብሔርን አመሰገንን። እግዚአብሔር በውኽይ ምስክር ብቻ አይደለም ያስቀመጠው፤ በዘመኑ ሊቀረፍ ያልቻላቸውን ችግር ጭምር ነው መስበር የጀመረው።

እነርሱም ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው በሚያልፉበት ጊዜ፣ ሐዋርያትና ሽማግሌ ዎች በኢየሩሳሌም ያሳለፉትን ውሳኔ ተቀብለው እንዲጠብቁ ለምእመናኑ ይሰጡ ነበር። አብያተ ክርስቲያናትም በእምነት እየበረቱና ዕለት ዕለትም በቍጥር እየጨመሩ ይሄዱ ነበር።

የሐዋርያት ሥራ 16÷4-5

በበለጠ መጠንከር

የመጨረሻውን የመነቃቃት ስብሰባ ካደረግን ስድስት ወር ዐልፎ ነበር። ጊዜው ሌላ ስብሰባ ለማድረግ ምቹ ነበር። መሐል ሜዳ ያደረግነው ትልቅ ስብሰባ ልክ ዓመቱ ነበር ያን ጊዜም ብዙ ነገር ተከሥቶአል። ጆን ቤይንና ንጉሤን በድጋሚ፣ በተጨማሪም ዐዲሱን ሚስዮናዊ ጓደኞችንን ጂሚ ማኒን ጋበዝናቸው።

ከስብሰባው አንድ ሳምንት በፊት ንጉሤ ለስብሰባው መምጣት እንደማይችል ሰማን። በጣም ዐዘንን ነገር ግን አሁንም መኮን ሰባኪና አስተርጓሚ አድርገን መቀጠል እንችላለን። ቄይቶም በሬዲዮ ጂሚ ማኒ በጣም ታሞ ሆስፒታል እንደ ተኛ ተነገረን። ጆኒ ብቻ ቀረ። አንድ ቀን ቀደም ብሎ ሲመጣ ጎይለኛ ትኩሳት አሞት ነበር። በአፍሪካ የተለመደው የወባ በሽታ ይዞት ነበር። መድኃኒት ያድነው ነበር። ነገር ግን ለስብሰባችን አይደርስም። ከስብሰባው ለመሰረዝና ይህነኑ ዜና ለሁሉም ለማድረስ በጣም ዘገየ፤ ስለዚህ ያለ ምንም ተጋባዥ ሰባኪ በራሳችን ለመቀጠል ወሰንን። ከመኮ ርዳታ ጋር የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ቁርጠን ተነሣን።

መኮ በደቡብ ኢትዮጵያ በወላሞ አካባቢ ነበር ያደገው። ሚሲዮናውያን ሁሉ በ1923-1933 በነበረው የጣልያን ወረራ ሲባረሩ በዚያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ታድግ ነበር። ይህ አሰደናቂ ታሪክ ሬይሞንድ ዴቪስ በጻፈው «ፋየር አን ዘ ማውንት» ላይ ይገኛል።

መኮ እስከ ዐሥረኛ ክፍል የተማረው በሕዝብ ትምህርት ቤት ነው። በጣም ጉበዝ ተማሪና በቤተ ክርስቲያኒቱ ንቁ ተሳታፊ ነበር። በጥቂት የሱዳን ሚሲዮናውያን ርዳታ ወደ ረዳት ሐኪሞች ትምህርት ቤት ገብቶ በነበረበት ሠለጠነ። ከተመረቀ በኋላ ከሳም ጋር እስኪገናኙ ድረስ በአንድ ሆስፒታል ውስጥ ይሠራ ነበር።

በመንዝ ገና የሚሸን ሥራችንን እየጀመርን ነበር። ሳም በተንቀሳቃሽ ጤና ጣቢያውና በፀሐይ ሲናው ጤና ጣቢያ የሚረዳውን ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ይፈልግ ነበር። ሕክምና ዕቃውን የሚያስቀምጠውና ጎሙስ ጎሙስ የሚያክመው በፀሓይ ሲና ጤና

ጣቢያ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜ በዚያ ቦታ ሕክምና የሚሰጥ ሰው ይፈልግ ነበር።

መኮ ወደ መንዝ የመሄዱ ሐሳብ ቢያስደስተውም ቦታው መጥፎ ዝናብ ስለ ነበረ ፈርቶት ነበር። ነገር ግን የጌታ ምሪት መሆኑን ተረድቶ ለመሞከር ተስማማ። በአቅራቢያው ቤታችንን ሠርተን እንደ ጨረስን እርሱም ወደ ክሊኒኩ አንድ ክፍል ገባ። አንድ ላይ መንዝን እየለመድነው ሄድን።

ለእኛም እንደ ሆነው ሁሉ አማርኛ ለመኮም ሁለተኛ ቋንቋው ነበር። ወደ መንዝም የመጣው እኛ በመጣንበት ጊዜ ነው። ነገር ግን ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቅ፣ ነገሮችንም በከፍተኛ ፍላጎት ለማስተዋል ይጥር ነበር። ብዙም ሳይቈይ በአካባቢያችን ምን እየተካሄደ እንዳለና ምን እንደሚባል ለማወቅ በእርሱ ላይ መደገፍ ጀመርን። በተጨማሪም በጣም ልዩ የሆነ የጨዋታ ለዛ እንዳለው ተረዳን። የሰውን አኳኋን ቀድቶ በማሳየት ረገድ እርሱን የሚችለው የለም። መኮ አጠገባችን ካለ በርግጠኝነት ደስተኞች ነበርን።

የሕክምና ሥራውን በትንሹ ነበር የጀመረው፤ መጀመሪያ ላይ በሽተኞቹ የሚመጡት ምርጫ ሲያጡና በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ ነበር። ነገር ግን መኮ የማረጋጋት ጠባይ ስላለው በሽተኞቹ የሕክምና ርዳታን በከፍተኛ ጥንቃቄ ያገኙ ነበር። ስለ እርሱ ለጓደኞቹና ለጎረቤቶቻቸው መንገር ጀመሩ፤ ከዚያም ብዙ በሽተኞች ከመምጣታቸው የተነሣ ፀሓይ የጀመረ ምሽት ዐልፎ ሌሊት እስኪተካ ድረስ ይቀጥላል። አንድ ሰው ለመንቀሳቀስ እስኪችግረው ከታመመና መኮ ካለ፣ በቅሎም ባይገኝ በእግር ቤቱ ድረስ ሄዶ ሕክምና ይሰጣል።

አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ አደጋ ይደርሳል። የተጐጂው ዘመዶች እየጮኹ ርዳታ ፍለጋ ይመጣሉ። መኮ አልችልም ለማለት ስለሚከብደው፤ ብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ይሄዳል። ምንም እንኳ የመኮ ትምህርት የተወሰነ ቢሆንም በየቀኑ የተለያየ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ሲያይና የማያውቀው ነገር ሲያገኝ የሕክምና መጻሕፍቱን ይመለከታል፤ ዶ/ር ካናታን ይጠይቃል ወይም በቀላሉ ጌታ ተገቢውን አቅጣጫ እንዲያሳየው በእርሱ ላይ እምነቱን ይጥላል።

ሳም በጤና ጣቢያው የሕክምና መሣሪያዎቹ እስኪቀቀሉ ድረስ የሕክምና ሥራውን በስብከት የመጀመር ባህል ነበረው። ብዙ ጊዜ መኮን እንዲሰብክ ይጠይቀዋል። መኮ በጣም ቸልተኛ የሆነን በሽተኛ ትኵረት እስኪያገኝ ድረስ ደስተኛ አልነበረም። ከዚያም ብዙ ሳይቈይ ጥሩ ዶክተር እንደ ሆነ ሁሉ ጥሩም ሰባኪ እየሆነ አደገ።

መኮ በጤና ጣቢያው ሥራ እንደሚበዛበት እናውቅ ነበር። የሆነው ሆኖ በሦስት ቀኑ ስብሰባ ላይ በሚችለው መንገድ ሁሉ ሊረዳን ተስማማ። እነዚህን ስብሰባዎች ሁሉም የሚወዳቸውን ያህል

ይወዳቸው ነበር። በመንዝ በጊዜው ከነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት የተነሣ በማኅበረ ሰቡ አዳራሽ የሕዝብ ስብሰባ ማድረግ ጥሩ እንዳልሆነ ዐሰብን። ጊዜው ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልግበት ነበር።

በቤታችን ውስጥ በተደጋጋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እናደርግ ነበር። ሳሎኑና የምግብ ቤቱም በመጠኑ ትልቅ ነበር። ብዙዎቹን የቤት ዕቃዎች በማውጣትና ሰዎቹን መሬት ላይ በማስቀመጥ ስልሳ ሰዎች ሊይዝ ይችላል። አመቺ የስብሰባ ቦታ ነበር ምክንያቱም መኮ በተፈለገ ጊዜ ወደ ክሊኒክ መሄድና ተመልሶም መምጣት ይችላል። ተጨማሪው ጥቅም ደግሞ ውሀና መብራት ሌሊቱን ሙሉ ማግኘት መቻላችን ነው።

ስብሰባውን እሑድ ከሰዓት በኋላ ስንጀምር ከመሐል ሜዳ የመንግሥት ተማሪዎች በቡድን መጡ። የእኛ የኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በጣም ዐፈሩ። ከተማሩ የከተማ ተማሪዎች ጐን ሲቀመጡ የማይረቡ የገጠር ሰዎች እንደ ሆኑ ተሰማቸው። አንዳች ነገር ቢናገሩ እንደ መሀይም የሚቈጠሩ መስሏቸው ስለ ፈሩ ጸጥ ረጭ አሉ። እስከ ምሽቱ ድረስ አስተማርን፤ ነገር ግን ከተሳታፊዎች የጠበቅነውን ተገቢ ተሳትፎና ምላሽ አላገኘንም ነበር።

በማግስቱ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ተመለሱ። ከዚያም ሌሎቹ መሳተፍ ጀመሩ። በስብሰባው ላይ ትልቁ ፍላጎታቸው የነበረው በመንዝ ባላቸው የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ወንጌልን ተግባራዊ ማድረግ ነበር። ለበዓሉ ትክክለኛው ሰባኪ መኮ ነበር። የነገሮች ድምዳሜ ምን እንደ ሆነ በግልጽ በሚያሳይ መልኩ በሥዕላዊ ሁኔታ የማስረዳት የተፈጥሮ ችሎታ ነበረው። ሐሳቡን ለመረዳት ሲቻል ዐዲስ ትልቅ ግኝት እንደ ተገኘ ይቈጠራል።

በመንዝ ሕጋዊ ያልሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ትልቁ ችግር ነበር። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝሙት ከሕግ ውጪ እንደ ሆነ ሥርዐት ሳይሆን፣ እንደ ልማድ ነው የሚታየው። የምሽቱ ጊዜያት ቀዝቃዛ ናቸው። ዐልጋና ብርድ ልብስም ብርቅ ናቸው። በዚያ ዐይነት የአየር ጠባይ ለብቻ መተኛት የማይታሰብ ነገር ነው። ሁልጊዜ አንድ እንግዳ ተቀባይ ለእንግዳው መስተንግዶ የምታሞቀውን ሴት ጨምሮ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማዘጋጀት አለበት።

በመንዝ ትዳር የሚያረገርግ ጕዳይ ነው። የትዳር ግንኙነት በተደጋጋሚ ይቋረጣል ሊያውያም በማይረቡ ነገሮች። ሴቶች በድጋሚ ሲያገቡ ወዲያውኑ ልጆቻቸው የእንጀራ ልጆች ይሆናሉ፤ ከዚህም የተነሣ ልጆች ብዙ ጊዜ በመጥፎ ሁኔታ ነው የሚያዙት። በእኛ መረዳት በመንዝ ካሉ ልጆች መካከል አንድ ሦስተኛ ያህል የሚሆኑት ያለ ጋብቻ የተወለዱ ሲሆን፣ ሌላው አንድ ሦስተኛ ደግሞ እንጀራ ልጆች ናቸው።

ጣቢያ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜ በዚያ ቦታ ሕክምና የሚሰጥ ሰው ይፈልግ ነበር።

መኮ ወደ መንዝ የመሄዱ ሐሳብ ቢያስደስተውም ቦታው መጥፎ ዝናብ ስለ ነበረ ፈርቶት ነበር። ነገር ግን የጌታ ምሪት መሆኑን ተረድቶ ለመሞከር ተስማማ። በአቅራቢያው ቤታችንን ሠርተን እንደ ጨረስን እርሱም ወደ ክሊኒኩ አንድ ክፍል ገባ። አንድ ላይ መንዝን እየለመድነው ሄድን።

ለእኛም እንደ ሆነው ሁሉ አማርኛ ለመኮም ሁለተኛ ቋንቋው ነበር። ወደ መንዝም የመጣው እኛ በመጣንበት ጊዜ ነው። ነገር ግን ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቅ፣ ነገሮችንም በከፍተኛ ፍላጎት ለማስተዋል ይጥር ነበር። ብዙም ሳይቈይ በአካባቢያችን ምን እየተካሄደ እንዳለና ምን እንደሚባል ለማወቅ በእርሱ ላይ መደገፍ ጀመርን። በተጨማሪም በጣም ልዩ የሆነ የጨዋታ ስዛ እንዳለው ተረዳን። የሰውን አኳኋን ቀድቶ በማሳየት ረገድ እርሱን የሚችለው የለም። መኮ አጠገባችን ካለ በርግጠኛነት ደስተኞች ነበርን።

የሕክምና ሥራውን በትንሹ ነበር የጀመረው፤ መጀመሪያ ላይ በሽተኞቹ የሚመጡት ምርጫ ሲያጡና በፍርሀትና በመንቀጥቀጥ ነበር። ነገር ግን መኮ የማረጋጋት ጠባይ ስላለው በሽተኞቹ የሕክምና ርዳታን በከፍተኛ ጥንቃቄ ያገኙ ነበር። ስለ እርሱ ለጓደኞቹና ለጎረቤቶቻቸው መንገር ጀመሩ፤ ከዚያም ብዙ በሽተኞች ከመምጣታቸው የተነሣ ፀሓይ የጀመረ ምሽት ዐልፎ ሌሊት እስኪተካ ድረስ ይቀጥላል። አንድ ሰው ለመንቀሳቀስ እስኪቸግረው ከታመመና መኮ ካለ፣ በቅሎም ባይገኝ በእግር ቤቱ ድረስ ሄዶ ሕክምና ይሰጣል።

አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ አደጋ ይደርሳል። የተጐጂው ዘመዶች እየጮኹ ርዳታ ፍለጋ ይመጣሉ። መኮ አልችልም ለማለት ስለሚከብደው፤ ብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ይሄዳል። ምንም እንኳ የመኮ ትምህርት የተወሰነ ቢሆንም በየቀኑ የተለያየ በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ሲያይና የማያውቀው ነገር ሲያገኝ የሕክምና መጻሕፍቱን ይመለከታል፤ ዶ/ር ካናታን ይጠይቃል ወይም በቀላሉ ጌታ ተገቢውን አቅጣጫ እንዲያሳየው በእርሱ ላይ እምነቱን ይጥላል።

ሳም በጤና ጣቢያው የሕክምና መሣሪያዎቹ እስኪቀቀሉ ድረስ የሕክምና ሥራውን በስብከት የመጀመር ባህል ነበረው። ብዙ ጊዜ መኮን እንዲሰብክ ይጠይቀዋል። መኮ በጣም ቸልተኛ የሆነን በሽተኛ ትኵረት እስኪያገኝ ድረስ ደስተኛ አልነበረም። ከዚያም ብዙ ሳይቈይ ጥሩ ዶክተር እንደ ሆነ ሁሉ ጥሩም ሰባኪ እየሆነ አደገ።

መኮ በጤና ጣቢያው ሥራ እንደሚበዛበት እናውቅ ነበር። የሆነው ሆኖ በሦስት ቀኑ ስብሰባ ላይ በሚችለው መንገድ ሁሉ ሊረዳን ተስማማ። እነዚህን ስብሰባዎች ሁሉም የሚወዳቸውን ያህል

ይወዳቸው ነበር። በመንዝ በጊዜው ከነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት የተነሣ በማኅበረ ሰቡ አዳራሽ የሕዝብ ስብሰባ ማድረግ ጥሩ እንዳልሆነ ዐሰብን። ጊዜው ጥንቃቄ ማድረግ የሚያስፈልግበት ነበር።

በቤታችን ውስጥ በተደጋጋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እናደርግ ነበር። ሳሎኑና የምግብ ቤቱም በመጠኑ ትልቅ ነበር። ብዙ ሰዎችን የቤት ዕቃዎች በማውጣትና ሰዎቹን መሬት ላይ በማስቀመጥ ስልሳ ሰዎች ሊይዝ ይችላል። አመቺ የስብሰባ ቦታ ነበር ምክንያቱም መኮ በተፈለገ ጊዜ ወደ ክሊኒክ መሄድና ተመልሶም መምጣት ይችላል። ተጨማሪው ጥቅም ደግሞ ውሀና መብራት ሌሊቱን ሙሉ ማግኘት መቻላችን ነው።

ስብሰባውን እሑድ ከሰዓት በኋላ ስንጀምር ከመሐል ሜዳ የመንግሥት ተማሪዎች በቡድን መጡ። የእኛ የኦርቶዶክስ መጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በጣም ዐፈሩ። ከተማሩ የክተማ ተማሪዎች ጐን ሲቀመጡ የማይረቡ የገጠር ሰዎች እንደ ሆኑ ተሰማቸው። አንዳች ነገር ቢናገሩ እንደ መሀይም የሚቈጠሩ መስሏቸው ስለ ፈሩ ጸጥ ረጭ አሉ። እስከ ምሽቱ ድረስ አስተማርን፤ ነገር ግን ከተሳታፊዎች የጠበቅነውን ተገቢ ተሳትፎና ምላሽ አላገኘንም ነበር።

በማግስቱ ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ተመለሱ። ከዚያም ሌሎቹ መሳተፍ ጀመሩ። በስብሰባው ላይ ትልቁ ፍላጎታቸው የነበረው በመንዝ ባላቸው የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ወንጌልን ተግባራዊ ማድረግ ነበር። ለበዓሉ ትክክለኛው ለባኪ መኮ ነበር። የነገሮች ድምዳሜ ምን እንደ ሆነ በግልጽ በሚያሳይ መልኩ በሥዕላዊ ሁኔታ የማስረዳት የተፈጥሮ ችሎታ ነበረው። ሐሳቡን ለመረዳት ሲቻል ዐዲስ ትልቅ ግኝት እንደ ተገኘ ይቈጠራል።

በመንዝ ሕጋዊ ያልሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ትልቁ ችግር ነበር። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝሙት ከሕግ ውጪ እንደ ሆነ ሥርዐት ሳይሆን፣ እንደ ልማድ ነው የሚታየው። የምሽቱ ጊዜያት ቀዝቃዛ ናቸው። ዐልጋና ብርድ ልብስም ብርቅ ናቸው። በዚያ ዐይነት የአየር ጠባይ ለብቻ መተኛት የማይታሰብ ነገር ነው። ሁልጊዜ አንድ እንግዳ ተቀባይ ለእንግዳው መስተንግዶ የምታሞቀውን ሴት ጨምሮ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማዘጋጀት አለበት።

በመንዝ ትዳር የሚያረገርግ ጉዳይ ነው። የትዳር ግንኙነት በተደጋጋሚ ይቋረጣል ሊያውያም በማይረቡ ነገሮች። ሴቶች በድጋሚ ሲያገቡ ወዲያውኑ ልጆቻቸው የእንጀራ ልጆች ይሆናሉ፤ ከዚህም የተነሣ ልጆች ብዙ ጊዜ በመጥፎ ሁኔታ ነው የሚያዙት። በእኛ መረዳት በመንዝ ካሉ ልጆች መካከል አንድ ሦስተኛ ያህል የሚሆኑት ያለ ጋብቻ የተወለዱ ሲሆን፤ ሌላው አንድ ሦስተኛ ደግሞ እንጀራ ልጆች ናቸው።

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ከሰሙ እንደሚያምኑ ርግጠኛና ትክክልም ነበር። በዚያ ውጤት አልተደነቀም። ልክ እንደ ጠበቀው ነበር የሆነው።

የዝናብ ወቅት ልክ በጊዜው በሰኔ ጀመረ። የተቃጠለውን ድልድይ እንደገና በትክክል መሥራት ጀመርን። በመጀመሪያ ድልድዩ ሲሠራ ሕዝቡ ሳይሳተፍ ሚሽኑ ነበር ሥራውን ሁሉ ያከናወነው፤ ዕቃዎቹንም ያቀረበው። በዚያ ጊዜ ሕዝቡ በድልድዩ መጠቀም ለምዶአል። በተቃጠለ ጊዜ በጣም ዐዝኖ ነበር፤ ስለዚህ ድጋሚ ሲሠራ ድጋፍ ለማድረግ ፈለገ እንደ ጣውላ እንዲያገለግል የባሕር ዛፍ ዕንጨት ከየቦታው አመጣ።

ዛፎቹ ከሥር ተቈርጠው በመዶሻ በቦታቸው ተመቱ። ከዚያም በኮረት ተሸፈኑ። ለሁለተኛ ጊዜ ድልድዩ በቀላሉ እንዳይቃጠል በደንብ ተሠራ። ጎይለኛ ዝናብ ጀምሮ ወንዙን ለመሻገር ከማስቸገሩ በፊት ተሠርቶ ዐለቀ። ድጋሚ በተሠራው ድልድይ ላይ ኰርተን ነበር የምንሻገረው። ምንም ወጪ አላስወጣንም። በጣም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው ደግሞ የኅብረተ ሰቡን መተባበር የሚጠይቅ ሥራ መሆኑ ነበር።

መንገዱ ጭቃ ሲሆን የትም ቦታ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሄድ አቆምንና ቁጭ ብለን በየቀኑ በሚዘንበው ጎይለኛ ዝናብ መደነቅ ጀመርን። ልጆቻችን ለዕረፍት ወደ ቤት መጥተው ስለ ነበር ቤተ ሰብ አንድ ላይ ጥሩ ጊዜ ለማሳለፍ ቻልን።

ዝናቡ በአካባቢያችን ይካሄድ የነበረውን ጦርነትም ባለበት እንዲቆም አደረገ። የመንግሥት ወታደር የተጫነባቸው የጭነት መኪናዎች በሚዳልጡት መንገዶች ላይ መሄድ አልቻሉም። በእግር መሄድ በጣም አደገኛ ነበር ምክንያቱም ወንዞች በፍጥነት ስለሚሞሉ ጥንቃቄ ከጐደለ በተሳሳተ አቅጣጫ ተሸክርካሪ ገብቶ ሊያዝና ሊቀር ይችላል። ዝናቡ በነበረበት ጊዜ ጦርነቱ የቆመው ከዚህ የተነሣ ነው።

የዝናቡ መምጣት የክረምት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መከፈቻ ጊዜ እንደ ደረሰ አመላከተ። ባለፈው ዓመት አዲስ አበባ ከነበረው የኦርቶዶክስ ሚስዮን ጋር በተደጋጋሚ እንገናኝ ነበር። የእነርሱ የሬዲዮ ፕሮግራም ዘማሪ ዋቂት የመዝሙር ካሴቶችን ሠርቶልናል። እዚያ የሚሠራው ቂስ መክብብ ከመንዝ ነው የሄደው። እርሱ ብዙ ጊዜ ከሳም ጋር በመሄድ በጤና ጣቢያችንና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፕሮግራሞች ላይ ሰብኳል።

በየዓመቱ ከክረምቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ጀርባ ነገሮችን የሚያፋጥንልን አቶ ገብረ ሕይወት ነበር። አስተማሪዎችን ያገኘና በመንዝ ለሚኖራቸው ቈይታ ነገሮችን ያዘጋጃል። ነገር ግን በዚህ ጊዜ እርሱ ወህኒ ቤት ታስሮ ነበር። በመንዝ ያሉ ሰዎች ተስፋ ቈርጠው ነበር። በዚያ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንደማይኖር ርግጦች ነበሩ።

ወደ አርቶዶክስ ሚስዮን ሄደን ባደረግናቸው ጉብኝቶች አዲስ አበባ ባሉት የአርቶዶክስ መሪዎችና በመንዝ ባሉት ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲከፈት በሚፈልጉት መካከል እኛ አገናኝ ድልድይ ሆንን። በዚህ ዓመት ትምህርት ቤት የሚኖር ከሆነ፣ ጌታ ራሱ ዝርዝር ነገሮችን እንዲያዘጋጅ ለወራት ጸለይን። ከዚህ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ላይ ፍላጎት ያደረባቸው ሰዎች በኋላ በክርስቶስ እምነታቸውን ለመመሥላት በጥልቀት የተከታተሉ ነበሩ።

ሁሉም ይወዱት የነበረው የቀድሞ አስተማሪያቸው ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ተዛውሮ ነበር። የእርሱን ቦታ የሚተካ ሰው ለመፈለግ ከባድ አይሆንም ነገር ግን ጌታ ወደ ኢሳይያስ መራን። የብሉይ ኪዳኑን ነቢይ የኢሳይያስን ስም የወሰደው ኢሰይያስ ኑሮውን ይመራ የነበረው ልክ እንደ ስሙ ነው። በቢሲኤም ኤስ (ባይብል ቸርች ሜንሰ ሚሽነሪ ሶሳይቲ) ቋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥበት ትምህርት ቤት ውስጥ ስለ ተማረ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ያውቅ ነበር። በአርቶዶክስ የሬዲዮ ፕሮግራም ላይ በተደጋጋሚ ይሰብክ፣ ኢየሱስንም ያውቅና ይወድ ነበር። እግዚአብሔር ላቀረብነው ጸሎታችን በድጋሚ ከጠበቅነው በላይ መልስ ሰጠን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ የትምህርት ሳምንት ጂሚ ማሮኒ ስለ ስብከት አዘገጃጀትና አቀራረብ ዘዴ አስተማረ። ብዙዎቹ ተማሪዎች በዚህ ትምህርት በጣም መመሰጥ ጀምረው ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ እስከ ቄየበት ጊዜ ድረስ በቀን ሁለት ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻቸው ይሰብኩ ነበር። ብዙ የትምህርት ክፈለ ጊዜያትን ስንከታተል ይህ የመጀመሪያችን ነበር። በርግጥ ተማሪዎቻችን ሲሰብኩ መስማት ፈልገናል ነገር ግን በተጨማሪ የኢሳይያስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች በጣም ያስደስቱን ነበር። ኢሳይያስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ሕይወት ለመስጠት ይችል ነበር። ሁልጊዜ እሑድ በፀሐይ ሲና ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይሰብካል፤ ከዚያም በኋላ የእኛን ቋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያስተምራል።

የምርቃቱ ቀን ከሌላው ጊዜ የተለየ ነበር። በማኅበረ ሰቡ አዳራሽ ውስጥ ስንሰበሰብ ዝናቡ በስሱ ጣሪያ ላይ ድምፅ እየፈጠረ ይንጠባጠብ ነበር። አንድ መቶ ሃያ ተማሪዎች ከዘመዶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በዚያ ነበሩ። ወሩን ሙሉ ልምምድ ሲያደርጉባቸው ከነበሩት መዝሙሮች ጥቂቶቹን በመዘመር ጀመሩ። ከዚያም ወደሚያስደስተው የፕሮግራሙ ክፍል ተደረሰ። የገንዘብ አባካኙን ልጅ ታሪክ በድራማ መልክ አቀረቡ። ድራማውን የሠሩት በወቅታዊው መንዝ ውስጥ ሆነው ስለ ነበር፣ ትክክለኛ መስሎአል። በጣም በሚያሳምን መንገድም ነው ያቀረቡት።

በዚያን ጊዜ ጥቂት ወንድ ልጆች በቡናማ የሱፍ ብርድ ልብስ ተሸፍነው በደረታቸው እየተሳቡ መጡ። መድረኩ ላይ በእጃቸውና በጉልበታቸው እየሄዱ ያልተለመደ ጩኸት አሰሙ። ቄይተን ጉዳዩ ግልጽ ሆነልን፤ ዐሣማ ሆነው ለመታየት ነበር እንዲዚያ ያደረጉት። በመንዝ ማንም እንደዚያ ያሉትን እንስሳት ያየ የለም። ስለዚህ ተጠቀመቡት በዐይነ ኅሊናቸው የሣሉትን ነው። ውጤቱ የተለየና በጣም አስደሳች ነበርና ትልቅ ስኬት ታየበት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ብዙ ዐዳዲስ ጓደኞችን አፈራን። ባለፈው ጊዜ በእያንዳንዱ ዓመት እንዳደረግነውም የምርቃት ቀን ሽልማቶችን ሰጠን። መጽሐፍ ቅዱስ ላላቸው ተማሪዎች የመዝሙር መጻሕፍትንና የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን ሸለምን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ከተለመደው ስድስት ሳምንት በላይ በአንድ ወር ተራዝሞ ነበር፤ ይሁን እንጂ በሌላ ጊዜ ከነበረው እንደሚበልጥ ተሰማን። ነገሮች በጊዜው ሁሉ እየተሻሻሉ ይታዩ ነበር። ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል ዐሰብን። ያንም ለማወቅ ብዙ መቄየት አልነበረብንም።

ጌታም ሴሊት በራእይ ጳውሎስን እንዲህ አለው፤ «አትፍራ፤ ተናገር፣ ዝምም አትበል፤ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና ማንም በአንተ ላይ ተነሥቶ ሊጐዳህ አይችልም፤ በዚች ከተማ ብዙ ሰዎች አሉኝና።» ስለዚህ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማራቸው አንድ ዓመት ተኩል አብሮአቸው ተቀመጠ።

የሐዋርያት ሥራ 18÷9-10

ጥበቃ

በኢትዮጵያ የነበረው የፖለቲካ ለውጥ ውጤት ይሰማን ጀመረ። በየቦታው ጋዝ በራሽን መልክ የሚሰጥ ሆነ። በተመረጡ ጋዝ ማደያዎች በራሽን ኩፖን በሳምንት አራት ጋሎን ብቻ ነበር የሚፈቀደው። ያለንን ጋዝ በሙሉ በበርሜል ወደ መንዝ አምጥተን በጋራዥ አስቀምጠን በተፈለገ ጊዜ በጎማ እንቀዳ ነበር። አንድ ሙሉ በርሜል ጋዝ ለመግዛት ፈቃድ ማግኘት የማይቻል ነገር ነበር። ከዚህ የተነሣ መኪና የምንነዳው በጣም ካስፈለገ ብቻ ነበር።

ገበያ ላይ ያለው የሸቀጥ አቅርቦት ዕጥረት እየታየበት ሄደ። ጨውና ስኳር ብርቅ ሸቀጦች ሆኑ። ዱቄት ብዙ ጊዜ አይገኝም ነበር። በመንዝ ሕዝብ ለሚገለገልባቸው ቀላል ፋኑሶች እንደ ነዳጅ የሚያገለግሉት ነጭ ጋዝና ናፍጣ ሊገኙ አልቻሉም። ሕጋዊ ያልሆኑ ነጋዴዎች የማይገኙትን ሸቀጦች ዋጋ የሚተምኑት እንደ ፈለጉ ነበር።

የስልክና የአውቶቡስ መሥመሮች በተደጋጋሚ ከአገልግሎት ውጪ በመሆናቸውና ክፍያዎችም ብዙ ውዝፍ ዕዳ ስለሚያስከትሉ፣ በዚያ ያለው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክህነት በዚህ ምክንያት ተዘጋ። በተጨማሪም ከመዘጋቱ ጋር ቁስ ግርማ የመንዝ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ባለ ሥልጣን የመሆን ዕድሉ ቀረ። መስከረም ላይ ከመላው ኢትዮጵያ ከተሰበሰቡት መቶ ዐሥራ ሁለት ተማሪዎች መካከል በመጨረሻው ፈተና አንደኛ በመሆን ተመርቆ ነበር። ወደ መንዝ ሲመለስ ያ እድል እንደሌለ ዐወቀ።

ዝናቡ ጋብ ሲል በመንዝ የነበረው ጦርነት በድጋሚ ቀጠለ። በዚህን ጊዜ ሁለቱም አየር ማረፊያዎች በመንግሥት ትእዛዝ ተዘጉ። ልጆቻችን ወደ ዐዳሪ ትምህርት ቤቱ እንደ ተመለሱ ዐማፅያኑ ወደ አዲስ አበባ የሚወስደውን ዋና መንገድ ዘጉት። በዚያ የሚያልፍ ማንኛውም ሰው በጥይት እንደሚመታ አስታወቁ። በዚያን ጊዜ በመንዝ

ያለነው ሚስዮናውያን እኔና ሬይ ብቻ ስለ ነበርን ለጊዜው ባለንበት መቈየት እንደሚሻል ወሰንን።

የመንግሥት ወታደሮች አልጨብጥ ያሉትን የሽፍቶችን ዱካ ለማግኘት ገጠር ውስጥ በመግባት ከፍተኛ ዐሠሣ አካሄዱ። በመንገዳቸው ላይ የነበረውን ነገር ሁሉ አጠፉ። በሰማይ አድማስ ላይ ከሣር ክዳን ጣሪያዎች የሚወጣ ጥቍር ጢስን ማየት የተለመደ ሆነ።

ሕዝቡ ከወታደሮቹ ፊት ሲሸሹ በቤታችን ያልፉ ነበር። በፍጥነት ለመሄድ የሚያስቸግራቸውን ሸክም ሁሉ ጥለው የሚችሉትን ያህል ብቻ በጥንቃቄ ተሸክመው ነበር የሚሄዱት። የጭነት መኪናዎችን መቅደም መቻል አለባቸው። ብዙዎቹ ዕቃዎቻቸውን በእጅ ሥራ ትምህርት ቤት ውስጥ እንድናስቀምጥላቸው ወደ እኛ ይዘው መጡ። ሬይ እያንዳንዱን እስር ወይም ትልቅ ሻንጣ በጥንቃቄ ምልክት እያደረገ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ከመረው። ከብዙ ቀናት በኋላ አንድ ትልቅ ክፍል ከመሬት እስከ ኮርኒሱ ድረስ በዕቃ ተሞልቶ ባለመብቃቱ፣ በተጨማሪም አንድ ትንሽ መጋዘን ለዚህ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ ዕቃ ሞላው።

እንዲያውም በአቅራቢችን ቤተ ክርስቲያን ያሉ ቄሶች ታቦቱን ሳይቀር እንድናስቀምጥና እንድንጠብቅ እንዲሁም ጥቂት ቅዱሳት መጻሕፍትንና በትልቅ ሣጥን ውስጥ የተቀመጡ ቅርሶችን በዐደራ እንድናኖር ወደ እኛ ይዘው መጡ ከስድስት ወር በፊት እኛ ታቦት በመስረቅ ተወንጅለን ነበር። አሁን ደግሞ ታቦት እንድንጠብቅ ተጠየቅን!

የዐማፂው ቡድን የተመሠረተው በአገሩ ተወላጅ ሰዎች ሲሆን፣ የሚመራው በቅርቡ ትልቅ የክብት ዕርባታና ሌሎች የመሬት ይዞታዎች በመንግሥት በተወረሱባቸው ሁለት ወንድማማቾች ነበር። እነዚህ ሰዎች ዐዲሱን መንግሥት በግልጽ በመቃወም የትግል እንቅስቃሴ በማድረግ ወደ መንዝ የሄዱ ናቸው። ዐማፅያኑ ከተቀሩት ሌሎች ሰዎች ምንም ስለማይለዩ እነርሱን ለመያዝ አይቻልም ነበር። ነገር ግን በዚያ እንደ ነበሩ ግልጽ ነበረ ምክንያቱም በመንግሥት ላይ ጥቃት ያደርሱ ነበር።

ለጦርነቱ ጀቶች እየበረሩ መጡ። በመጀመሪያ ገጠሩን ለማሠሥ ሄሊኮፕተሮች ዝቅ ብለው መብረር ጀመሩ። ሰዎች የሄሊኮፕተሮቹን የሚሽከረከር ድምፅ ሲሰሙ ፍተሻውን ተሸፍነው ለማምለጥ ቦታ ይፈልጋሉ። ቀጥሎ ጀሮ በሚበጥስ ጩኸት ታግዘው ጀቶች መጡ። ሰዎቹ በጣም ፈሩ። ለመደበቅ ሞከሩ ነገር ግን ድምፁን ማምለጥ አልቻሉም። ጀቶቹ ዐማፅያኑ ይደበቁባቸዋል ተብለው በሚጠረጠሩ ቤቶች ላይ መትረየስ በመተኩስና ቦምብ በማውረድ በተደጋጋሚ ይመላለሱ ነበር። ከነቃቱ በኋላ የመንግሥት ወታደሮች

በፍጥነት ወደ ውስጥ ይገባሉ። በፍጥነት የሚሮጥ ሰው ብቻ ነበር ከዚያ ሁኔታ ሁሉ የሚያመልጠው።

ቤታችን ጦርነቱን ለመመልከት አመቺ ቦታ ላይ ነበር። ለመንግሥት ወታደሮች ወይም ለዐማፅያኑ ደጎንነት በጣም እናስብ ነበር። እነርሱም በጦርነቱ መካከል እኛን ጣልቃ ላለማስገባት በጣም ይጠነቀቁ ነበር። በየትኛውም ጊዜ ሁለቱም ወገኖች የእኛ በዚያ መገኘት ቅር የሚያሰኛቸው መስሎ አይሰማንም ነበር።

ለእነዚያ ሁለት ወራት ከቀሪው ዓለም ጋር የሚያገናኘን ብቸኛ መንገድ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ላይ የምናደርገው የዐጭር ሞገድ የሬድዮ ግንኙነታችን ነው። በአዲስ አበባ ስለ ጦርነቱ ይሰማ የነበረው ወሬ የተጋነነ ስለ ነበር ሁሉም ሰው ደኅንነታችን አሳስቦት፣ ሕይወታችንም አደጋ ላይ የወደቀ መስሎት ነበር። እግዚአብሔር ነገሮችን እየተቈጣጠረ እንደ ነበረ የሰጠንን ማረጋገጫ ለማስረዳት ከፍተኛ ጥረት አደረግን።

እግዚአብሔር በሚፈልገው ቦታ ላይ እንዳለንና እኛን የመጠበቁ ተግባርም የእርሱ ኀላፊነት እንደ ሆነ ይሰማን ነበር። ከሁሉ የበለጠ ደኅና ቦታ ላይ መገኘት ማለት በእግዘአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆን እንደ ሆነ ማመን ከጀመርን ረጅም ጊዜ ሆናል። በዚያ ጊዜ እምነታችንን የምንፈትንበት ዕድል አያገኘን ነበር። በወቅቱ ግቢያችንን ለቀን ወጥተን ወይም ስብሰባ ጠርተን አናውቅም ነበር፤ ነገር ግን ብዙ ሰዎች እኛን ሊጠይቁ ይመጡ ነበር። ብዙዎቹ ለመወያየትና መጽናናትን ለማግኘት ነበር የሚመጡት። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እምነታችንን ለሰዎች ለማካፈል ወሰን የሌለው ዕድል አገኘን።

የመንግሥት ትምህርት ቤት አስተማሪዎችና ሠራተኞች ከወራት በፊት የአውቶቡስ አደጋ በደረሰበት ጊዜ ለቀው እንደ ሄዱ አልተመለሱም ነበር። በመንዝ የቀረን የውጪ ሰዎች እኛ ብቻ ነበርን ለማለት ይቻላል። ሰዎች እኛን ለመጠየቅ ሲመጡ መቄየት ባለስፈለገ ጊዜም በመንዝ እንቄይ እንደ ሆነ ይጠይቁን ነበር። ከወራት በፊት መሄድ እንችል ነበር። በምርጫችን እንደ ቄየን አስተዋሉ። ይህንንም እንደ ወደዱት በተደጋጋሚ ይነግሩን ነበር። በሰላም ጊዜ ለሰባት ዓመት በዚያ ስንኖር ያላገኘነውን ነገር በጦርነት ጊዜ አብረናቸው ስንቄይ ከእነርሱ መካከል እንደ አንዱ በመቍጠር ተቀበሉን።

በየቀኑ ቤት ማቃጠሉ ቀጠለ ነገር ግን ሁልጊዜ ከእኛ ትንሽ ይርቅ ነበር። በመጨረሻ አንድ ቀን የእኛ ተራ የደረሰ መሰለን። የሩቅን አቅርቦ በሚያሳይ መነፅር ወደ እኛ አቅጣጫ ያለማቋረጥ የሚመጣ የሚንቦገቦግ እሳት ተመለከትን። ከሰዓት በኋላ በሙሉ አመጣጡን ስንመለከት ቄየን። ልክ ፀሓይ ስትጠልቅ፣ ጢሱ ከእኛ ግማሽ ማይል ርቀት ላይ ደረሰ። ቤቱ በሚያለቅሱ ሰዎች ተሞልቶና በኋላችንም ብዙ

ሰዎች ተወሽቀው ባለንበት ሁኔታ ፀሓይ ስትወጣ ወታደሮቹ መንገዱን አቋርጠው ወደ እኛ ቤት ሲመጡ ተመለከትን።

የግቢው ሴቶች በሙሉ ወደ እኛ ቤት ሸሽተው መጡ፤ ወንዶቹ ደግሞ በዕርሻ ውስጥ ተደብቀው ነበርና ከተደበቁበት እንዲወጡ ወታደሮቹ አዘዟቸው። ከዚያም ሴቶቹን ወደ ቤት እንዲመለሱ አዘዟቸው። ለቀኑ የሚበቃቸውን ያህል ሠርተዋል አሁን የሚተኙበትና ትኩስ ምግብ የሚያገኙበትን ቦታ ነው የሚፈልጉት። ከዚህ የተነሣ ያ ግቢ ከችግር አመለጠ።

በማግስቱ ወደ ቀያ ተንቀሳቀሱ። በዚያ አቅጣጫ ጥቊር የጢስ ደመና ስንመለከት በዚያ ስለ ነበሩት ብዙ ጓደኞቻችን ዐሰብን። ምን እንደ ሆነ ዜና እስኪደርሰን እየጠበቅን ጸለይንላቸው። በኋላ ታሪኩን ስንሰማ በእግዚአብሔር ስሕተት አልቦ ዕቅድና የራሱ በሆኑት ላይ ባለው አስደናቂ ጥበቃ በድጋሚ ተደሰትን።

ወታደሮቹ ቀያ እንደ ደረሱ ቀጥታ ወደ ቄስ ግርማ ቤት ሄዱ። ብዙዎቹ አዲስ አበባ ከቀሳውስት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቱ ጐን ባለው ወታደራዊ ማሠልጠኛ ሲሠለጥኑ ቄስ ግርማን አግኝተውት ነበር። ቀደም ሲል ጥቂት የማይባሉ ወታደሮች በእርሱ አገልግሎት ኢየሱስን ዐውቀዋል። ምናልባት ወደ መንዝ ከመጡ እንዲጠይቁት ጋብዟቸው ሳይሆን አልቀረምና ለጥቂት ጊዜ ካወሩ በኋላ ቤቱን ለቀው ወደ ሥራቸው ሄዱ። በቀያ ሁለት ሰዎች የትግል እንቅስቃሴ ውን በመምራት ይጠረጠሩ ነበር። ወታደሮቹ ወደ ሁለቱ ሰዎች ግቢ ሄደው ቤቱን አቃጠሉ። የሆነው ሆኖ በሚያስደንቅ መልኩ በሌላ ቦታ እንዳደረጉት በመንገዳቸው ላይ ምንም ነገር አልነኩም ወይም ጉዳት አላደረሱም። ስለዚህ ቀያ ከአደጋ ተረፈ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎቻችን መካከል አንዱ የዐማፅያን መሪ በመሆን ከሚጠረጠር ሰውየ ግቢ አጠገብ ይኖር ነበር። ወታደሮቹ በሰማይ አድማስ ከላይ ብቅ ሲሉ ከጉልቴ በስተቀር ሁሉም ሰው ሸሸ። ቤቱን እንዳያቃጥሉት ለመንገር ፈለገ። ከዐማፅያኑና ከጦርነቱ ጋር የሚገናኝ ምንም ነገር አላደረገም ነበር። ጉልቴ ይህንን ማወቅ እንዳለባቸው በማሰብ እየቀረቡ ሲመጡ ማስረዳት ጀመረ። የሆነው ሆኖ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ተናግሮ ሳይጨርስ ከወታደሮቹ አንዱ በጀርባው ባዘለው የዐጭር ሞገድ ሬዲዮ ወደ ጠቅላይ መምሪያ መልእክት አስተላለፈ። የሚገኝበትን ቦታ በመጠቈም ለሚቀጥለው ተልእኮ ፈቃድ ጠየቀ።

ጉልቴ በደንብ ለመስማት ወደ ፊት ተጠጋ። ያለ ምንም ርኅራኄ በዚያ ያገኙትን ሁሉንም ነገርና ሁሉንም ሰው እንዲያጠፉ ታዘዙ። ጉልቴ የተቀረውን ንግግር ለመስማት በዚያ አልቈየም። የሚበቃውን ያህል ሰምቷልና። ወዲያውኑ ከግቢው ውስጥ ሮጠ ወጣና በቅርቡ ወደ አለው ሣር በቀጥታ ሄደ። በዚያ ቀን ጌታ ጉልቴን ከዚያ አደጋ አዳነው። ለጥቂት ያመለጠበትን ሁኔታ ጉልቴ ሲያስብ ዐላማ እንደ ነበረው ርግጠኛ ሆኖአል።

ባለፈው ፀደይ ወታደሮቹ ቤት ሲያቃጥሉ ሰዎቹ ወዲያውኑ ዐዲስ ሣር ገዝተው ዝናብ ከመጀመሩ በፊት እንደገና ሌላ ቤት ሠሩ። አሁን ከስድስት ወር በኋላ በድጋሚ ተቃጠለባቸው። በዚህን ጊዜ ሰዎቹ ድጋሚ ቤት ለመሥራት አልተቻኮሉም። ምንም ተስፋ አልነበረውም። ቤቶቹ ጣሪያ ሳይለራላቸውና እንደ ተቃጠሉ ሆነው ሊኖሩባቸው የግድ ሆኖአል።

ጥቅምት ወር ላይ ከባድ ጦርነት ከተካሄደ በኋላ የመንግሥት ወታደሮች ዐማፅያኑን በሸለቆ ውስጥ እንደ ከበቧቸው ወሬ ሰማን። በጭነት መኪኖች በመንገዝ፣ በተዋጊ ሄሊኮፕተሮቻቸውም በመታገዝ ወታደሮቹ በደከሙትና ተስፋ በቁረጡት እግረኞች ላይ ዘመቱባቸው። መጨረሻ ላይ በአቋማቸው ጸንተው ከዚያ ሳይነቃነቁ ለመዋጋት ቁረጡ። ከብዙ ተኩስ በኋላ ዐማፅያኑን ከበቧቸው መጨረሻ ላይም ለመያዝ ሲያስችግሯቸው በነበሩበት ዋሻ ለመጀመሪያ ጊዜ ተመለከቷቸው።

ሁለቱ የዐማፅያን መሪዎች ሞተው ነበር። በሕይወት እንዳሉ ከመማረክ ለመዳን ራሳቸውን በጥይት ገድለው ተገኙ። ስለ አሟሟታቸው የነበሩትን ጥርጣሬዎች ለማስወገድ ጭንቅላታቸው በመሃል ሜዳ ገበያ ላይ ዞሮ ታየ። በአዲስ አበባም በቴሌቭዥን ቀረበ። በአሁኑ ጊዜ ታሪካቸው አፈ ታሪክ ወደ መሆን የተጠጋው የራስ ብሩ ልጆች በመጨረሻ ላይ በውጊያው ተሸንፈው እንደ ነበር ማረጋገጫ ዎች ተገኝተዋል።

የመንግሥት ወታደሮች ተቃዋሚዎችን በመደገፍ የሚጠረጠሩ ቦታዎችን ለመበቀል ተጨማሪ ጥቂት ሳምንታት ቈዩ፤ ይሁን እንጂ ሰጊዜውም ቢሆን መጨረሻ ላይ ጦርነቱ ተጠናቀቀ። መንገዱ በድጋሚ ተከፈተ፤ ወደ ከተማም ለመሄድ ቻልን። በጉዟችን ሁሉ በእነዚያ አስቸጋሪ ቀናት ስለ ጠበቀን ብቻ ሳይሆን፣ ከፍርሀት ነጻ የመሆንን ልምድ ስላገኘንም ጭምር እግዚአብሔርን አመሰገንን።

በዚህ ሁኔታ መንገዱ ከተከፈተ በኋላ ወልደ ጻድቅን በአዲስ አበባ ወደ ሚገኘው የሥጋ ደዌ ሆስፒታል ወሰድነው። በሆስፒታሉ የሚሠራ አንድ ሚስዮናዊ ጓደኛችን ሊረዱት እንደሚችሉ ነግረውናል። እግሩን ከመረመሩ በኋላ ጉልበቱ ላይ እንዲቈረጥ አዘዙ። ሰው ሠራሽ እግር እንደሚዘጋጅለት ተናገሩ። ለመዳን አንድ ወር ያህል እንደሚፈጅበት ከገለጹልን በኋላ፣ መጨረሻ ላይ ሰው ሠራሽ እግር ይገጠምለታል አሉን።

ወልደ ጻድቅ ቀዶ ጥገና ከተደረገለት ከአንድ ወር በኋላ ልንጠይቀው ሄድን። ቊስሉ እንዳመረቀዘ ስንሰማ በጣም ዐዘንን። እግሩ ዶክተሮቹ እንደ ገመቱት በፍጥነት እየዳነ አልነበረም። በአሰርት ሆስፒታል ለጥቂት ጊዜ መቈየት ነበረበት። የካሴት ማጫወቻና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍትን ወሰድንለት። ወልደ ጻድቅ በመላላክ ተከታታይ ትምህርት ይሰጥበት በነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ

ጥናት ኮርስ የተመደቡትን ሰባት መጻሕፍት አስቀድሞ አጥንቶ ጨርሶ ነበር።

ወልደ ጻድቅ ከውሽይ ስለ ሄደ ፊልም ለማሳየት ወደ ዚያ ተመልሰን አልሄድንም ነበር። እንደ ተመሰሰ ፊልም የማሳየቱን ተግባር እንደገና ለመጀመር ዐቅደን ነበር። ነገር ግን ሁል ጊዜ ልንጠይቀው ሄደን ስንመለስት፣ ወደ ቤቱ ለመመለስ የጨንነቱ ሁኔታ ከወር በፊት ከነበረው እምብዛም የሚሻል አልነበረም። ጌታ ይህ እንዲሆን ለምን እንደ ፈቀደ ዐሰብን።

ከዚያም ያልተለመደ ነገርን ማስተዋል ጀመርን። የሆስፒታሉ ሠራተኞች ባዶ ዐልጋ በተገኘ ቁጥር ወልደ ጻድቅን ከክፍል ወደ ክፍል ያዘዋውሩታል። ሁልጊዜ ልንጠይቀው ስንሄድ ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውሮ ይገኛል። ለመጨረሻ ጊዜ እርሱን የጉበኘንበትን ክፍል መፈለግ እንጀምራለን፤ ከዚያም የክፍሉ ሕሙማን ሁልጊዜ የሚገኝበትን ዐዲሱን ክፍል ማሳየት ይችሉ ነበር። ሁሉም ሰው እርሱን ያውቀውና ይወደው ነበር። መጨረሻ ላይ ስናገኘው ክፍሉ ዐዲስ ይሆናል ነገር ግን ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ ይዞና ዐልጋ ላይ ተቀምጦ በሽተኛ ያነጋግራል።

ወደ ታወቀው የሥጋ ደዌ ሆስፒታል ሰዎች ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ይመጣሉ። የሚመጡት ብዙዎቹ ኦርቶዶክስ ክርስቲያች ናቸው። ወልደ ጻድቅ ከእነርሱ ጋር በልዩ ሁኔታ እንደ ተዛመደ ተሰማው። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥም ያገኛቸውን አስደናቂ ነገሮች ለእያንዳንዳቸው ለማስተዋወቅ ብዙ ጊዜ አልወሰደበትም። ጥቂቶቹ ባካፈላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ተማርከው ነበር። ስለዚህም ከክፍል ወደ ክፍል ሲዘዋወር በሄደበት ቦታ ሁሉ ይመሰክር ነበር። እግሩ አልዳነም ነበር፤ ሆኖም ጌታ እየተጠቀመበት የነበረው እግር እንዳለው ሰው ነው።

በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ ወደ መንዝ ተመልሰን ስንሄድ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በድጋሚ ጀመርን። በቀያ በጣም ታማኝ የነበሩት አማኞች አንድ ሐሳብ ይዘው ወደ እኛ መጡ። በሙሉ ጊዜያቸው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመግባት ፈለጉ።

ቁስ ግርማ እርሱ በተማረበት ትምህርት ቤት የሚፈልጉትን እንደማያገኙ ተናገረ። ብዙው ትምህርት ከቤተ ክርስቲያን ታሪክና ባህል እንዲሁም በኦርቶዶክስ ፍልስፍና ላይ ያተኮረ ነበር። እነርሱ መማር የፈለጉት መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ነበር። ጥቂቶቹ ያገቡና ቤተ ሰብ ያላቸው ነበሩ፤ ሁሉም ደግሞ የሚያርሱት መሬትና የሚረዷቸው ዘመዶች ነበሯቸው። አንዳቸውም ያጠራቀሙት ብር የላቸውም። በመንዝ መቈየት የተሻለ መፍትሔ ይመስል ነበር። እንደዚህ ከሆነ ቤተ ሰቦቻቸውን መንከባከብና በአካባቢያቸው ላሉት መመስከር ይችላሉ።

ከሌሎች ጋር ሲነጻጸሩ መሣይም እንዳይባሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በተጨማሪ በሕዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚማሩትን

በጥቂቱ የመማር ፍላጎት ዐደረባቸው። ተማሪዎች በተደጋጋሚ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያልተማሩ ካህናት ስላሏት ትችት ያቀርባሉ። ብዙዎቹም ወደ ቤተ ክርስቲያን ላለመሄድ ይህንን ምክንያት አድርገው ይጠቀሙበታል።

በተጨማሪም ትንሽ የእንግሊዝኛ ቋንቋን መማር ፈለጉ። በቋንቋው የተወሰኑ ቃላትን መናገር ትምህርት ቤት እንደ ተማሩ ያስቈጥራል። የጀማሪዎችን ሒሳብና ሳይንስም ሥርዐተ ትምህርቱ ውስጥ አካተትን። ቀላል መመሪያዎችን ማስት «መሬት ክብ ናት» «ፀሓይ አትንቀሳቀስም መሬት ግን በዙሪያዋ ትሽከረከራለች» የሚሉትን እናውቃለን። እነርሱንም ምንም እንኳ ሁልጊዜ ባይገባቸውም ወይም ባያምኑንም፣ ይህን ሲሰሙት ያስደስታቸዋል።

ከቋሚው የእሑድ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በተጨማሪ በሳምንት ሁለት ቀን ሙሉ ቀን ለማስተማር ሐሳብ አቀረብን። ቀኑን ሙሉ ተራ በተራ እናስተምራለን ብዙ ነገርም ሊማሩ ይችላሉ። ሐሳቡን ወደዱት፤ ስለዚህ በቀጣዩ ሳምንት ትምህርቱን መስጠት ጀመርን። ቋሚ ግርማንም ለማስተማር እንዲረዳን ቀጠርነው። መጽሐፍ ቅዱስንና የሁሉንም ተማሪዎች የኦርቶዶክስ ልምድ በሚገባ ያውቅ ነበር። በሕይወቱ ስላለፈባቸው፣ ችግሮች የት የት ላይ እንዳሉ ያውቅ ነበር። ቋሚ ግርማ በየቀኑ በሚያስተምርበት ጊዜ ስናዳምጠው በረከትን እንቀበላለን፤ ዕውቀታችንና መረዳታችንም ያድግ ነበር።

በቀያ በነበረው የድንኳን ክፍላችን ውስጥ ታጠቅ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ነበር። ብዙ ሳይቈይ ዲያቆን የነበሩትን ሁለት ወንድሞቹን ይዞ መምጣት ጀመረ። እርሱ ያገኘውን ለወንድሞቹ ሊያካፍላቸው ፈለገ። አቢ የታጠቅ ታላቅ ወንድም ነበር ነገር ግን ከታጠቅ በበለጠ ያፍር ነበር። የክትትል ትምህርት ኮርሶችን ተማረ። በቤተ ሥራዎችና ፈተናዎችም ላይ የሚችለውን ሁሉ ቢያደርግም ትምህርቱ ለእርሱ አስቸጋሪ ነበር። በየሳምንቱ የጥያቄ መልሶችን ለመጻፍ በጣም ሲቸገር ታይቷል። ብዙ ጊዜ ባጠቃላይ ለመሥራት እንኳ ጊዜ ያጥረዋል። ባልም አባትም እንደመሆኑ በጣም ሥራ ይበዛበት ነበር።

አመቺና ቅርብ የሆነ ቦታ መምረጥ ነበረብን። ትልቁን ድንኳን መሥራት እንችል ነበር ነገር ግን ያን ያህል ቦታ አያስፈልገንም። በተጨማሪም ነፋስ ሲነፍስ ድንኳኑ ይቀዘቅዝ ነበረ ብዙ ጊዜም መሬቱ ጭቃ ነው። አቢ በመኖሪያ ግቢው ውስጥ ከቀድሞው ቤቱ የሚበልጥና የሚያምር ዐዲስ ቤት ሠርቶ ነበር። በርና መስኮት ገና ያልተገጠመበት ቢሆንም፣ ከዚያ ውጪ ዐልቆ ነበር። በቤቱ እንድንጠቀምበት ሐሳብ አቀረበ። በጣም ተስማሚ የመሰብሰቢያ ቦታ ሆነ። እርሱም ለብዙ ወራት በአሮጌው ቤቱ ውስጥ ሲቀመጥ፣ እኛ በዐዲሱ ቤት እንሰበሰብ ነበር።

በቋሚነት የበልግን ወቅት በሙሉና የክረምትን የመጀመሪያ ወራት አስተማርን። ዐልፎ ዐልፎ ዐዲስ ሰው ይመጣና ለጥቂት ጊዜ ይቈያል፤ ነገር ግን ሁልጊዜ እንደሚመጡ የምንተማመንባቸው የመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለት ታማኝ ዲያቆናት ነበሩ። እሑድ እሑድ ክፍሉ ይሞላል። ከጊዜ በኋላ ብዙውን አገልግሎት እነርሱ ሆኑ የሚቈጣጠሩት። ሁለት ሰው በየሳምንቱ ይሰብካል፤ ሌሎች ደግሞ ዝማሬውን ይመራሉ፤ የመዝሙር መጻሕፍትን ያድላሉ፤ እንግዶችንም ይቀበላሉ። ሥራቸው እያንዳንዱን አርፋጅ በግድግዳው ዙሪያ ባሉት አግዳሚ የጭቃ ወንበሮች ላይ ከሞሉ በኋላ የቀሩትን መሬት ላይ ባለው ጭድ እንዲቀመጡ ማበረታታት ነበር። ቄስ ወይም ጉልማሳ ሲመጣ አንድ ሰው ከአግዳሚው ላይ እንደሚነሣ የታወቀ ነበር። የመዝሙር ቍጥርን ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ቍጥርን አይቶ ለማውጣት የሚቸገሩትን ለመርዳት ሁልጊዜ በርካታ ሰዎች ይመደባሉ።

በእነዚህ ወራት በሙሉ ምእመናኑ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በመጠቀም እየተሻሻሉ ሄዱ፤ ትልቅ ዕውቀትንም አገኙ። ዕድገታቸው በጣም ግልጽ ቢሆንም በቍጥር በጣም አልበዙም። በመጠኑ ግራ ተጋባን፤ ምክንያቱ ምን እንደ ሆነ አልገባንም። ቀደም ሲል አንድ አማኝ እንድናገኝ እንዴት እንደ ጸለይንና ጌታም እንደ መለሰልን አስታወስን። ከዚያም አርባ አማኞች እናገኛለን አልን፤ ጌታም በድጋሚ ታማኝነቱን አረጋገጠልን። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደዚያ ዐይነት የተለየ ጥያቄ አንሥተን አናውቅም።

ጥር ላይ የእኛ ሚሲዮናውያን ለዓመታዊ የጸሎት መርሐ ግብር ተሰበሰቡ። በእንድነት ስንጸልይ ጌታ ብዙ ዐዲስ አማኞችን ለማግኘት እጅ ለእጅ ተያይዘን መንቀሳቀስና አጥብቀን መጸለይ እንዳለብን ወቀሠን። በዚህ ጊዜ ምንም ወሰን አላበጀንም። እግዚአብሔር የጸሎት ጥያቄያችንን እንዴት እንደሚመልስ ለማየት ስንጠብቅ ከፍተኛ ጉጉት ዐደረብን።

ከሚያዳምጡትም ሴቶች መካከል ሊዲያ የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም እግዚአብሔርን የምታመልክና ከትያጥሮን ከተማ የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴ ነበረች። ጌታም ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ተሰማ ዘንድ ልቧን ስፈተላት። እርሷና ቤተ ሰዎቿ ከተጠመቁ በኋላ፣ «በጌታ ማመኔን በርግጥ ከተረዳችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥቼአለሁ ጥቂት ተቀመጡ» በማለት አጥብቃ ለመነችን።

የሐዋርያት ሥራ 16÷14-15

ምስክሮች

ከሚሰዮናውያን የጸሎት ፕሮግራም መመለሳችን ከአንድ ሃይማኖታዊ በዓል ጋር ተገጣጠመ። በፀሓይ ሲና የቅድስት ማርያም በዓል ላይ የወልደ ጻድቅን እኅትና ወንድም አየናቸው። ምንም እንኳ ወልደ ጻድቅ በዚያ ባይኖርም፣ የሞቀ ሰላምታ ካቀረቡልን በኋላ ወደ ቤታቸው መጥተን በድጋሚ ቤተ ሰባቸውን እንድንጉበኝ ጠየቁን።

ቤታቸው ከሄድን ከስድስት ወር በላይ እንደ ሆነን አስታወስን። ለማመን ያስቸገር ነበር። በዚያ ጊዜ ውስጥ ብዙ ነገር ተሠርቷል፤ ጊዜ ውም ያለፈው በፍጥነት ነበር። እዚያ ስንደርስ ምን እንደምናገኝ እያሰብን ለመምጣት ቃል ገባን። በእምነታቸው ጠንክረው እንዴት ሊቁዩ ይችላሉ? ወልደ ጻድቅ ሲሄድ፣ ኢየሱስን የሚያውቁና የመጽሐፍ ቅዱስ መጠነኛ ዕውቀት የነበራቸው ሁለት እኅቶቹና እናቱ ነበሩ የቀሩት። ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው የመመለሳቸው ነገር የማይቀር ነበር።

በመኪና ስንመጣ የቤተ ሰቡ አባላት በሙሉ ከግቢያቸው ወጥተው ቆመው ይመለከቱን ነበር። እናትየዋ ደስተኛ ነበረች። ለሰላምታ ከተሳሳምን በኋላ በጉጉት ምን እየሆነ እንደ ነበር ትነግረን ጀመር። ወደ ቤት ገብተን እስክንቀመጥ እንኳ አልጠበቀችም። እምነቷን በኢየሱስ ላይ ብቻ በማድረግ ክታቦቿን በሙሉ እንድናቃጥላቸው ስትጠይቀን የአካባቢው ሰው ሁሉ ሰማ። ሁለት ነገሮች ሊከሠቱባት እንደሚችሉ ዐሰብን።

ከሁሉ አስቀድሞ ሰይጣን ይቄጣታል። ከዚያም የተነሣ አንድ ትልቅ አደጋ ማለት በሽታ፣ የአዝመራ ብልሽት፣ አደጋ፣ ለሸክላ ሥራው መጥፎ ገበያ ወይም ሞት ቤተ ሰቡን ያጋጥመዋል። የትኛ ው እንደሚከሠት ቁጭ ብለው ተመለከቱ። ሁለተኛ በመጥፎ ድርጊቷ ተጸጽታ ዐዲስ ክታቦችን ለማግኘት ወደ ጠንቋዩ ተመልሳ እንደምትሄድ ገመቱ። ብዙም ሳትቈይ ወደ ቀድሞው ስሜቷ ትመለሳለች።

በጥርነቱና በዝናብ ወቅት በሙሉ ሁልጊዜ ምሽት ላይ ቤተ ሰቡ የጸሎት ጊዜ ነበረው። ወልደ ጻድቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ያነብና ምን ማለት እንደ ሆነ ያብራራል። አንድ ላይ ይጸልዩና ይዘምሩ ነበር። በመዝሙሩ ላይ ልጆቹ ሁሉ ይሳተፋሉ። ይሠሩ የነበረውን ነገር ለመደበቅ አልሞከሩም። ጎረቤቶቻቸውም ሁሉ መስማት ይችሉ ነበር። ወልደ ጻድቅ ወደ ሆስፒታል ሄዷል ነገር ግን ያ ሁኔታ የምሽት ልምዳቸውን አላቆመውም። የወልደ ጻድቅ ታላቅ ወንድም አየናቸው እስከ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ተምሮ ነበርና በመጠኑ ያነባል። የተቀሩት ደግሞ መዘመርና መጸለይ ይችላሉ። ስለዚህ እነርሱ ሥራቸውን ቀጠሉ። ጎረቤቶቻቸውም እነርሱን መመልከት ቀጠሉ።

ስድስት ወር ዐለፈ። ሰይጣን እንደማይበቀላቸው ግልጽ እየሆነ መጣ። ከሰይጣን ሁከት ነጻ መሆን ብቻ ሳይሆን፣ በሌላ ጊዜ ከነበሩበት ሁኔታ የበለጠ እየተሻሻሉ ሄዱ። ባለፈው ዓመት እናትዮዋ በርሃ በሽታ ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ወደ መሆን ተቃርባ ነበር። አሁን ያ ሕማም አያስቸግራትም። የሸክላ ዕቃዎች ዋጋ በጣም ስለ ጨመረ የተሻለ ገቢ ማግኘት ችለዋል። አዝመራውም በጣም ጥሩ ነበር። በዝናቡ ወቅት ወይም በቀዝቃዛው የክረምት ወራት አንዳችም ብርድ አልበረዳቸውም። እግዚአብሔር በጥሩ ሁኔታ እየተንከባከባቸው ነበር። ስለሚያገኙት የተሻለ አጋጣሚም ሁሉ ለጎረቤቶቻቸው ይነግሯቸው ነበር።

እናትዮዋ ታሪኳን ተናግራ ስትጨርስ የመጀመሪያ ልጇ ሚስት ስንቄ የምትጠይቀን ነገር ነበራት። በእነዚህ ወራት በሙሉ ሦስቱን ሴቶች ትከታተላቸው እንደ ነበር አመነች። ሴቶቹ ያላቸው ነገር እውነተኛ እንደ ሆነ ድምዳሜ ላይ ደረሰች። ያንን ከወሰነች በኋላ እንደ እነርሱ መጸለይና በሕይወቷ እንደ እነርሱ ሰላምና ደስታ ማግኘት እንደምትፈልግ ጠየቀችን። ስለዚህ በድጋሚ በአንድነት ጭንቅላታችንን ዝቅ አደረግን። ስንቄና ባለቤቷ፣ ከዚያም አየናቸው ልባቸውን ለእግዚአብሔር ሰጡ። በክርስቶስ እኅቶቻችንና ወንድሞቻችን ሲሆኑ፣ ለመግለጽ የሚያስቸግር ጣፋጭ ደስታ በላያችን ዐለፈ።

ለመሄድ ከመነሣታችን በፊት አየናቸው በማመንታት በእግሩ ላይ በሚታየው ቊስል ላይ ማድረግ የሚቻል አንድ ነገር እንዳለ ጠየቀን። ታፋው ላይ መግል የያዘውን አካሉን ከፍቶ አሳየን። እንደዚህ ከታመመ ስንት ጊዜ እንደ ሆነው ስንጠይቀው ገና የአራት ዓመት ልጅ እያለ እንደ ጀመረው ነገረን። በዚያን ጊዜ ሃያ አራት ዓመቱ ነበር። ሕማሙ ሃያ አመት አሠቃይቶታል ማለት ነው። በመሐል ሜዳ ባለው የመንግሥት ጤና ጣቢያ ለመታከም ሞክሮ ነበር። በዚያ ተከታታይ መርፌ በየጊዜው የተወጋ ቢሆንም፣ በእግሩ ላይ ምንም ለውጥ አልታየም። ሕማሙ አልቆመም፤ ዐልፎ ዐልፎም ያብጥ ነበር። ይህ ሲሆን እስከ ሁለት ወር ድረስ የዐልጋ ቊራኛ ሆኖ ይቈይ ነበር።

ከዚያም ወደ ጠንቋይ ሄደ። የተሻለ ነገር ሊያደርግለት ቢያንስ የተወሰነ ዕድል ነበረው። ጠንቋዩ ያለማመንታት ችግሩን

እንደሚያስወግድለት አረጋገጠለት። ነገር ግን መጀመሪያ የክፍያ ነገር ነበር። ለአገልግሎቱ አንድ ዶሮ እንዲያመጣ ጠንቋዩ ጠየቀው። አየናቸውም ተስማምቶ ክፍያውን ተግባራዊ ቢያደርግም፣ አሁንም ምንም አልተሻለውም። ጠንቋዩ ጠንክር ያለ መድኃኒት እንደሚያስፈልገው ተናገረ። በዚህ ጊዜ ለክፍያ የተጠየቀው በግ ነበረ። ያ ውድ ነገር ነበር ነገር ግን የሚያድነው ከሆነ ጠቃሚ ነው። ስለዚህ አየናቸው ተስፋ ሳይቆርጥ የተጠየቀውን አቀረበ። የሆነው ሆኖ በሚያሳዝን ሁኔታ አሁንም ምንም ነገር አልተሰወጠም። ከዚያም ጠንቋዩ ከፍተኛ ዋጋ ያለውን የመለያ ካርዱን በመጣል ተጫወተ። የእኛ ሚሊዮን ከሚያረባቸው ግልገሎች አንዱ እንዲመጣለት ጠየቀ። ግልገሎቹ ብዙ አልነበሩም። በቁጥር ትንሽ ስለ ሆኑ ዋጋቸው ውድ ነው።

ነገር ግን አየናቸው ለመዳን በጣም ጓጓ። ዋጋው ምንም እንኳ ከፍተኛ ቢሆንም መዳኑ ይበልጣል። ከእነዚህ ልዩ በጎች መካከል አንዱን ለመግዛት በቂ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚችለውን ሁሉ አደረገ። በመጨረሻ ላይ አንድ በግ ለመግዛት በቂ ገንዘብ አገኘ። ስለ መዳኑ እያሰላሰለ በጉን ወደ ጠንቋዩ ይዞ ሄደ። ቀናት እያለፉ ሲሄዱና በእግሩ ላይ ምንም ዐይነት መሻሻል ሳያይ ሲቀር በጣም ተናደደ።

ከዚህ በኋላ፣ «እግዚአብሔር በእግሬ ላይ ሊያደርገው የሚችለው ነገር አለ ብላችሁ ታስባላችሁ?» በማለት ጠየቀን። ታሪኩን ስንሰማ መዳኑ ለእግዚአብሔር ክብር ሊያመጣ የሚችልበት ጊዜ ሊሆን እንደሚችል ዐሰብን። ጌታ ያየናቸውን እግር እንዲያድንና በአካባቢው ላሉት ሰዎች ከጠንቋይ እንደሚበልጥ እንዲያሳይ ከእርሱ ጋር አብረን ጸለይን።

ጎመሱ እስት አየናቸው ወደ ፀሓይ ሲናው ክሊኒክ ረጅሙን የእግር ጉዞ አደረገ። ሳም ችግሩ የዐጥንት ችግር እንደ ሆነ በምርመራ ዐወቀው። ዐጥንቶቹ በእግሩ ውስጥ እየበሰበሱና በቁዳው ላይ ባለው ቁስል ወደ ውጪ እየወጣ ነበር። እንደዚህ ዐይነት በሽታዎች በአሜሪካ ሊታዩ በጣም ጥቂት ናቸው። ለሃያ ዓመትም በርግጠኝነት በሕክምና ሳይታዩ አይቁዩም። ሳምና መኮ ጸልየውለት ብዙ ፔኒሲሊን በመርፌ ወጉትና በሚቀጥለው ሳምንት ተመልሶ እንዲመጣ ነገሩት። በአንድ ወር ውስጥ እግሩ ሙሉ በሙሉ ዳነ። እኛ በዚያ በነበርንበት ጊዜ በሙሉ በዚያ ሁኔታ ድጋሚ አላመመውም። በውሽይ የሚኖሩ ሰዎች የሰይጣን ጎይል በተገፈፈበት ቦታ እግዚአብሔር ድል አድራጊ መሆኑን እንደገና አንድ ትልቅ ማረጋገጫ ተመለከቱ።

ከዚያም በቤታቸው ውስጥ ፊልም ማሳየት እንድንጀምር ጠየቁን። በዚህ ጊዜ እኅትማማቾቹ ጎረቤቶቻቸውን በየቤታቸው በመሄድ ጋበዟቸው። ምላሹ አስቀድሞ እንደ አገኘነው ጥሩ ነበር። ከእኛ ጋር ብዙ ጊዜ የሚሄዱት ዳያቆናት ከፊልሙ በኋላ በየተራ

ሰበኩ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ቤተ ሰቦቹ ለመጸለይና ለመዘመር መቼ እንደምንመለስ ጠየቁ። ዐዲስ መዝሙር መዘመር እንዲማሩና የጸሎት ጊዜ እንዲኖራቸው ፊልገው ነበር። ከእሑድ መርሐ ግብራችን ውስጥ አንድ ትርፍ ሰዓት ነበረን። ያ ጊዜ ቤታቸው ፊልም ለማሳየት ከመሄዳችን በፊት ከቀያ የምንመለስበት ጊዜ ነበር። ከእነርሱ ጋር ተጨማሪ አንድ ሰዓት እንዲኖረን ከቀያ ቀጥታ ወደ እነርሱ ቤት ለመሄድ ፈቃደኛ ሆንን። እነርሱም ያንን ውሳኔ በደስታ ተቀበሉት። በየሳምንቱ ቤታቸው የምንደርስው ዐይንን ያዝ ማድረግ ሲጀምር ነበር። የአንድ ደካማ የነጭ ጋዝ ፋኖስ ብርሃን ጨለም እያለ መሄዱን በጥቂቱ ወገግ ያደረገዋል። ከፊል ጨለማ በሆነበት ጊዜ ሰዎች ቀዝቃዛውን አየር ለመከላከል ጋቢ ለብሰው ሲመጡ፣ ማን እንደ ሆኑ ለመለየት ያስቸግር ነበር። ለረጅም ጊዜ በድምፅ ማን እየጸለየ እንደ ሆነ ለማወቅ ስለምንችል እንኰራ ነበር። በዚያ ጊዜ ስንጸልይ ግን የማናውቃቸውን ድምፆች ሰማን። እኛ ጭንቅላታችንን ዝቅ አድርገን ሳለ ሰዎች ወደ ውስጥ ገብተው ነበርና እግዚአብሔር እንደ መራቸው ሲሰማቸው መጸለይ ጀምረው ነበር። ብዙዎች ኢየሱስን በጸሎት በግል ሲያውቁ ሰማን። ነገር ግን በመንግሥተ ሰማያት መንፈሳችን እስኪተዋወቅ ድረስ ማን እንደ ሆኑ አናውቅም ነበር። በዚያ ምንም ጨለማ ስለማይኖር እግዚአብሔርን እመሰገንን።

እሑዶች በዝማሬ የደመቁ ዕለታት ነበሩ። በጣም ወደዱት። በተገናኘንበት ቦታ ሁሉ ይዘምራሉ። በሳር ምድር ያለችዋ ቤተ ክርስቲያን በዚያ መጽሐፍ ቅዱስ እንድናስተምር ጋበዘችን። ሬይ ሰበከ፤ እኔ ደግሞ አስተማርሁ። የዚህም አጸፋ እጅግ በጣም ጥሩ ነበር። ከዚያም የከሰዓት በኋላውን ጊዜ በቀያ ለማሳለፍ ወደዚያ ሄድን። ሁሉም በእግሩ ይመጣ ስለ ነበር፣ ለጥቂት ጊዜ ይጠብቃሉ። የተለመደው አገልግሎት ለሦስት ሰዓት ያህል ይዘልቃል፤ ሁለት ወይም ሦስት ስብከቶችንም ያጠቃልላል። በዚያ ያለውን አገልግሎት ከጨረስን በኋላ ወደ ውሽይ እንሄዳለን። ከቦታ ቦታ ስንዘዋወር ብዙዎቹ ጓደኞቻችን አብረውን ይጓዙ ነበር። ሁሉም አኩል የመሄድ ዕድል እንዲያገኙ ሁልጊዜ መኪናችን እስከሚችለው ድረስ በሰው ይጠቀጠቅ ነበር።

በመኪናችን ውስጥ አንድ ሣጥን መጽሐፍ ቅዱስና አንድ ሣጥን የመዝሙር መጻሕፍት እንይዛለን። ሁልጊዜ አንድ ሰው የመዝሙር መጻሕፍቱን ዐድሎ የመዝሙር ቍጥር እስኪናገር ድረስ በመንገዳችን ላይ ችግር ያጋጥመን ነበር። ከዚያ መዘመር ይጀምራሉ። መኪናው ውስጥ ዐሥራ ዐምስት ሆነን እንኳ ሳንባቸው እስከሚችል ድረስ ይዘምራሉ። ከሞተሩ ድምፅ በላይ እንዲሰሙ ይፈልጋሉ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ለጌታ የደስታ ዝማሬ ማቅረብ ሰዎቹን ያስደስታቸዋል።

የመዝሙር መጻሕፍት ሳይኖሩ ሲቀር ወይም በጨለማ ስንሄድ፣ በቃላቸው የሚያውቋቸውን መዝሙሮች ይዘምራሉ። ጥቂቶቹ መዝሙሮች በቀላል ዜማ የሚዘመሩ ሲሆን ብዙ ግጥም ያላቸው ነበሩ። መዝሙሮቹ ተዘምረው ሲያልቁ በምናባቸው በመጠቀም የራሳቸውን ተጨማሪ መዝሙር ይፈጥራሉ። ጭቃው ውስጥ ካልተቀረቀርን ወይም የመኪና ችግር ካላጋጠመን፣ ሁልጊዜ እሑድ መኝዳ አራት ሰዓት ይፈጅብናል። ነገር ግን ጎብረት ስናደርግና ስንዘምር ጊዜው ቶሎ ያልፋል።

አንዳንድ ጊዜ መንገዱ ቍልቍለት በጣም የበዛበት ወይም አባጣ ጎርባጣ ይሆናል። መንገዱ እስኪስተካከል ድረስ ወጥተን ከመኪና ጎን ለጎን በመሆን እንሮጣለን። ጭቃ ውስጥ ስንቀረቀር ሁሉም ሰው የመኪናው ጎማ በሚፈጥረው ቀዳዳ ውስጥ ድንጋይ ለመሙላት ይንቀሳቀሳል። በቂ ድንጋይ ከሰበሰብን በኋላ ሁላችንም መኪናውን በመግፋት እንረዳዳለን። ሁላችንም በአንድነት ጭቃው ውስጥ ብንገባም እንኳ ደስተኞች ነበርን። ከክርስቲያን ወንድሞች ጋር መሆን ልዩ ደስታ እንደሚያመጣ ሁሉም አስተዋለ። ከዚያ የተነሣ ያደርጉትና ይሆኑት የነበረው ሁሉ ከምንም የሚቈጠር አልሆነም።

ጳውሎስም ወደ ምኵራብ አየገባ፣ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያሳመናቸው ሦስት ወር ሙሉ ምንም ሳይፈራ ፊት ለፊት ይናገር ነበር። አንዳንዶቹ ግን ግትር በመሆን፣ ለማመን ፈቃደኞች አልነበሩም፤ የጌታንም መንገድ በገሃድ ያጥላሉ ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ ትቶአቸው ሄደ፣ ደቀ መዛሙርትንም ለብቻቸው ወስዶ በጢራስ የትምህርት አዳራሽ ውሰጥ በየዕለቱ ያነጋግራቸው ነበር። ይህን ማድረጉንም ሁለት ዓመት ስለ ቀጠለ፣ በእስያ አውራጃ ይኖሩ የነበሩት የአይሁድና የግሪክ ሰዎች ሁሉ የጌታን ቃል ለመስማት ቻሉ።

የሐዋርያት ሥራ 19÷8-10

የእሳቱ መቀጣጠል

ከሚስዮናውያን ጋር ከነበረን የጸሎት መርሐ ግብር በኋላ ውኽይ ወዳሉት ጓደኞቻችን ብቻ ሳይሆን፣ ቀያ ወደሚገኘው ወደ አቢ ቤትም ሄድን። ከጓደኞቻችን ጋር ተመልሶ መገናኘቱ በጣም ደስ ያሰኝ ነበር። እኛ ባልነበርንበት ሦስት ሳምንት ውስጥ እሑድ እሑድ ለመገናኘት ዐቅደው ነበር፤ ነገር ግን ባለፈው እሑድ ማንም አልመጣም። ለብዙ ወራት የቡድኑ ዕድገት የተገታ መስሎ እየታየን በጣም አሳስቦን ነበር። ስለ ችግሩ ምንነት ምን እንደሚያስቡ ጠየቅናቸው።

ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው ግርማ ሁሉንም አናገራቸው። በሁለተኛው እሑድ እኛ ሄደን ነበር፤ የመጡትንም በጥንቃቄ ተመለከቱ። የመጡት ሰዎች በሙሉ ከአቢ ቤት አንድ ሰዓት የእግር መንገድ ከሚርቀው ከአቃፌ ነበር። በግልጽ እንደሚታየው በቤታቸው አቅራቢያ መገናኘት ለእነርሱ ይቀላቸዋል። በተጨማሪም ፍላጎቱ እንዳላቸው የተናገሩ ጓደኞች ነበሯቸው፤ ነገር ግን ለማየት ብቻ ያን ያህል መንገድ በእግራቸው ለመምጣት ፈቃደኛ አልነበሩም።

ግርማ ለጊዜው ድንኳኑን እንድንጠቀምበት ሐሳብ አቀረበ። ከዚያም በአቃፌ መገናኘት እንችላለን። መኖሪያ ቤቱ የሚገኘው ከትልቁ የግጦሽ ስፍራ ከዐመድጉያ ጠርዝ ላይ ነበር። በመኪናችንም እዚያ መድረስ እንደምንችል ዐሰበ። ለመሞከር ከፈለግን ደግሞ በግቢው ውስጥ ድንኳኑን እንድንዘረጋ ፈቀደልን።

ሌሎቹ ተማሪዎች የእርሱን ሐሳብ ደግፈው ተናገሩ፤ ስለዚህ ወደዚያ ተንቀሳቀስን። በዚያ በነበረን የመጀመሪያ ቀን ትምህርት ወደ መቶ የሚጠጉ ሰዎች መጡ። ጥቂቶቹ ከአቃፌ ዐልፎ ከሚገኘው ከድግምሻ ነበር የመጡት። ከእነርሱ ባገኘነው ምላሽ ተደንቀን ነበር።

ነገር ግን በቅርቡ መምጣት እንደሚያቆሙ ገመትን። ተሳስተን ነበር። ሳምንት በሳምንት እየተተካ ሲሄድ መምጣታቸውን ቀጠሉ። ድንኳናችን ሲቀደድና ሲበሰብስ ዐዲስ ድንኳን ገዝተን በግርማ ግቢ ውስጥ ዘረጋነው። የድንኳኑ ትልቅነት ዋና መሰብሰቢያ ለመሆን ያስችል ነበር ነገር ግን ሰብዙ ተማሪዎች በቂ የመማሪያ ክፍል አልነበረንም። ስለዚህ አሮጌውንም ድንኳን ዘረጋነው። በጋ ስለ ነበር ቀዳዳዎቹ ምንም ችግር አላስከተሉም። የተፈለገው እንደ ጥላ እንዲጠቅምና ነፋሱን እንዲከለክል ነበር። ለእነዚህ ዓላማዎች ደግሞ በቂ ሆኖአል።

ግርማ አንድ ቡድን በእርሱ ቤት ውስጥ እንዲሰበሰብ በደስታ ፈቀደ። በተጨማሪም በግቢው ውስጥ አንድ ያረጀ ቤት ስለ ነበረው፣ በከፊል የቆመው ግድግዳ እንደ ጣሪያ እንዲገያለግል ከላዩ ጨርቅ ማንጠልጠል ተቻለ። እንደዚህ መደረጉ አራት የመማሪያ ክፍሎች እንዲኖሩን ረዳን። ከዚያ በኋላ ሰዎቹን ሴቶች፣ እረኛ ልጆች፣ ጀማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችና ነባር የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በማለት በአራት ቡድኖች ከፈልናቸው።

ቀጣዩ ችግር አስተማሪዎችን የማግኘት ችግር ነበር። ወደ አቃፌ ከመጣን በኋላ ረጅም መንገድ መሄድ ቢኖርበትም እንኳ፣ ቄስ ግርማ ሁልጊዜ ጠዋት እየመጣ እያንዳንዱን ቡድን ተራ በተራ ያስተምር ነበር። ሬይና እኔ ሁሉንም ነገር ማድረግ አንችልም። ማድረግ ከምንችለው በላይ ሆኖብናል። ጌታ ግን የሚያስፈልገንን ሁሉ ያውቃልና ግልጽ የሆነ መፍትሔ ሰጠን። አንድ ዓመት ተኩል ሙሉ በጥንቃቄ ያሠለጠንናቸውን ወጣት ወንዶች አስመርቀናቸዋል፤ አስተማሪዎችም ሆነዋል።

በማስተማል ስንመለከታቸው ለእኛ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እነርሱ እንደሚሳካላቸው ተረዳን። ለትምህርቱ መምጣት የጀመሩት ሴቶች ካለባቸው የባህል ተጽዕኖ የተነሣ በውጭ አገር ዜጋ መማሩ አስቸግሮአቸው ነበር። አፈጣጠሬ ትኩረታቸውን ከመሳቡ የተነሣ ለምናገረው ነገር በቂ ትኩረት አይሰጡም ነበር። አንዳንድ ጊዜ ስናገር እንዳያዩኝ ፊቴን በጋቢዬ እሸፍን ነበር። ይህ በተወሰነ ደረጃ ይረዳ ነበር ነገር ግን የመግባባቱ ጉዳይ ቀላል አልነበረም። ከአንድ ቃል ውስጥ አንድ ፊደል አሳስቶ መናገር አንዳንድ ጊዜ አረፍተ ነገሩን በሙሉ ትርጉም ያሳጣባቸዋል። በተጨማሪም ገበሬ ሴቶች እንደ መሆናቸው የነበራቸው ሕይወት ከእኔ ሕይወት በጣም የተለየ ነበር። በትምህርቱ ውስጥ ከሕይወት ጋር ሊያዛምዷቸው የሚችሏቸውን ምሳሌዎች ለማግኘት ለእኔ ከባድ ነበር። ወጣቶቹ እረኞች በጥቂቱ ይሻሉ ነበር።ማንኛውንም ነገር ማስታወስ የሚችሉት በማያቋርጥ ሁኔታ ከተደጋገመላቸው በኋላ እንደ ሆነ ዐወቅን።

ተበላሽተን ነበር። አሳባችንን ለመግለጽ ቃላትን ማግኘት ሲያቅተን እንኳ የሚረዱን ፈጣን ተማሪዎችን ማስተማር ተላምደነው ነበር። ዐዲስ አስተማሪዎች እኛ ከነበሩብን ችግሮች መካከል አንዱም

እንኳ የለባቸውም። የንግግር ዘዬቤአቸውና የቃላት አጠቃቀማቸው ትክክል ነበር። ትክክለኛው የመንዝ የአነጋገር ድምፅ ነበራቸው። አስተማሪዎች መንዜዎች ነበሩ። በመጀመሪያ ላይም እነርሱ ሲማሩ በትምህርቱ ውስጥ ትክክለኛ ምሳሌዎች የትኞቹ እንደሆኑ ያውቋቸዋል። በዐሜሩ ለቦታው ተስማሚ አስተማሪዎች ነበሩ።

ከአንድ ዓመት በላይ የትኛውንም የቀያ ቤተ ክርስቲያን ለመከታተል ለእኛ አስቸጋሪ ሆኖብን ቈይቷል። ሰብዙ ጊዜ በአካባቢው የሚጠራጠሩን ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ስለዚህ ለማስተማር ስንል ከድንኳኑ አጠገብ ነበር የምንኖረው። ነገር ግን ያ ቃሉን ከመስፋፋት አልገታውም። ተማሪዎች በቋሚነት ከተለያዩ ሰባት አብያተ ክርስቲያን አካባቢዎች ወደ ድንኳን ይመጡ ነበር። ተማሪዎች በየሳምንቱ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ በታማኝነት የተማሩትን ለቤተ ሰቦቻቸውና ለጓደኞቻቸው ያካፍላሉ። ብዙዎቹ እንዲያውም በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የመመስከር ዕድሉን አግኝተው ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና የማስታወስ ችሎታን ለመመዘን ይዚጋጁ የነበሩት ፈተናዎች ብዙ ጊዜአችንን መውሰድ ጀመሩ። ፈተናዎቹን ለመውሰድ ሰዎች ከየቦታው ይመጡ ነበር። ሁሉም የኦርቶዶክስ ቀሳውስትና ዲያቆናት ናቸው ማለት ይቻላል። በሰሜን ዐሥር ማይል ከሚርቀውና ከባድ ጦርነት ከነበረበት ከሀና ትልቅ ቡድን መምጣት ጀመረ። ሰዎቹ ወደዚያው ሄደን እንድናስተምራቸው ለመኑን። ለማስተማር እንዴት በወደድን ነበር፤ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ዐዲስ መርሐ ግብር መጀመር አንችልም። በዚያም ላይ የዓመት ፈቃዳችን መውጫ ጊዜ ደርሶ ስለ ነበር፣ ሌላ ሰው እንዲያስተምር ከማድረግ በቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም።

የእኛን የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የራሳቸው ሕዝብ ትክክለኛ መሪዎች እየሆኑ ሲመጡ፣ በዐዲስ ብርሃን ውስጥ እንመለከታቸው ጀመር። ቀድመው የነበሩት ዐይናፋር ተማሪዎች አልነበሩም። በራሳቸው የሚተማመኑ ወጣቶች ሆነዋል። እኛ ለመሄድ ወዳልቻልንባቸው ስፍራዎች ሁሉ መሄድና ማገልገል ይችሉ ነበር።

ድንኳናችንን በግቢው ውስጥ ከጣልን በኋላ ስብሰባዎችን ሁሉ የማስተባበር ኀላፊነት በግርማ ላይ ወደቀ። ምንም እንኳ የሃያ ዐምስት ዓመት ሰውና ገና ያላገባ ቢሆንም ግርማ ብስለት ያለው ልጅ ነበር። መንፈሳዊ እውነታን ለመረዳት ፈጣን ነበር፤ በስብከቱ ላይም መልእክቱን ለአድማጮች ግልጽ የማድረግ ችሎታ ነበረው።

የግርማ መኖሪያ ቤት ከማኅበረ ሰቡ የአድባር ዛፍ አጠገብ ነበር። ሁልጊዜ ከሰዓት በኋላ አመሻሹ ላይ የዛፉ ጥላ ቤቱ ላይ ያርፋል። አንድ ቀን ያ በሕይወቱ ምን ዐይነት ተጽዕኖ እንደ ነበረው ለቡድኑ ተናገረ። ትንሽ ልጅ ሳለ መጀመሪያ የተወለደ በግ ተሰጠው። ከአንድ ወር በኋላ ታመመ። የቻለውን ሁሉ ቢያደርግም እየባሰበት

መጣ። ለሞት እየተቃረበ ስለ ነበረ ፈራ። ተስፋ በመቁረጥ በጉን ወደ አድባሩ ዛፍ ወስዶ ከዳነ ግልገሉን ለአድባር እንደሚሰጥ ስለት ተሳለ።

ጠቦቱ ዳነና አድጎ የራሱን ጠቦት አደረሰ። ግርማ የገባውን ቃል ኪዳን የሚፈጽምበት ጊዜ ደረሰ። ስለቱን ካልፈጸመ የሚደርስበትን ፈራ። ስለዚህ የገባውን ቃል ለመፈጸም እየተዘጋጀ ሳለ እኛ በቀያ ለቀሳውስትና ለዲያቆናት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጀመርን። እኛ ያስተማርነውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በፍጥነት ጨብጦ በመሐል ሜዳ ስብሰባ ላይ ሕይወቱን ለክርስቶስ ሰጠ። አድባሩን ከዚያ በኋላ መፍራት አልነበረበትም።

ታጠቅ እሑድ በተደጋጋሚ የሚሰብክ ሌላ ሰባኪ ነበር። በተፈጥሮ ዝምተኛ ሰው ነበር። ነገር ግን በእጁ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ በሕዝብ ፊት ሲቆም ያ ሁሉ ይለወጣል። መልእክቶቹ ግልጽና ቀላል እንዲሁም በግልጽ ከጌታ በመጣ ሥልጣን ጀሮ ላይ የሚያስተጋቡ ነበሩ። ምንጊዜም ሲናገር ሰዎች ያዳምጡት የነበረው በከፍተኛ ትኩረት ነው።

አባ አሰፋ በቀያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ከመጀመሪያው አንሥቶ ይመጣ ነበር። ከስድስት ዓመት በፊት ባለቤቱ ስትሞት መንኩሷል። ከቀዳሚ ግዴታዎቹ መካከል የተጣሉ ሰዎችንና ቤተ ሰቦችን ማስታረቅ ነበር። በተጨማሪም ነፍስ አባትነትን የመሰለ ትልቅ ኀላፊነት ነበረበት። ኢየሱስን ሊያውቅ እነዚህን ሥራዎች አላቆመም። እንዲያውም ኀላፊነቶቹ ከዚህ በኋላ ትክክለኛ ትርጉም ይሰጡ ጀመር። ይቅርታ እውነተኛ ንስሓ ከተገባ በኋላ ብቻ የሚመጣ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ስጦታ እንደ ሆነ ለሰዎች መንገር ጀመረ። ይቅርታ በገንዘብ ወይም በአገልግሎት አይገዛም። እግዚአብሔር ይቅር እንዳለን እኛም እርስ በርሳችን ይቅር መባባል አለብን። አባ አሰፋ እምነቱን በተግባር ለማዋል ትክክለኛው ቦታ ላይ ያለ አገልጋይ ነበር።

ይሁን እንጂ ከሁሉም በላይ ያስደነቀን አስቻለው ነበር። ከቸኩልነትና ከቀጡነት የጠቅላላ ቡድኑ በጣም ታጋሽና ታማኝ አስተማሪ ወደ መሆን ተለውጦ ነበር። በየትኛውም ሰዓት እኛ ስንደርስ የተገኘውን ሰው ሲያስተምር እንደምናገኘው ርግጠኞች ነበርን። መዝሙሮችንና የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ፈልጎ ማግኘትን በማለማመድ ያስተምራቸው ነበር። ያውቀው የነበረውን መጠነኛ የሒሳብ ዕውቀት ያካፍላቸዋል፤ በ260 የአማርኛ ፊደላት ላይም የንባብ ልምምድ ያሠራቸዋል። አስቻለው ደፋርና የሚሰማውን የሚናገር ሰው ነበር። ነገር ግን ከጊዜ በኋላ እግዚአብሔር እነዚህን ባሕርያት አስቻለውን ጎይለኛ ሰባኪና አስተማሪ ለማድረግ ተጠቀመባቸው።

ከአስቻለው ባሕርይ በጣም የሚያስደስተው ነገር ደግሞ የሽመና ጓደኛውን የሚደበድብ ሰው ከመሆን ወደሚያፈቅርና ራሱን ወደሚሠዋ ሰው መለወጡ ነው። ይህ በእውነቱ ሙሉ ለሙሉ ነበር። ይህንን

ማንም ሳይሆን እግዚአብሔር ብቻ ነው ሊያደርገው የሚችለው። ሁልጊዜ ዐዲስ ኪዳኑን በሸሚዙ ኪስ ውስጥ ነበር የሚያስቀምጠው። ከብቶቹን ለመጠበቅ በቤተ ሰቡ ውስጥ ልጅ ከሌለ አስቻለው ሜዳ ላይ ብዙ ሰዓት ያሳልፋል። ከብቶቹን ሣር እያበላ መጽሐፍ ቅዱሱን በተደጋጋሚ ሲያነብ ይታያል። እግዚአብሔር ቃሉን በአእምሮው ውስጥ ሊፋቅ በማይችል መልኩ ቀርጾ ያስቀምጥ ነበር። ብዙም ሳይቈይ ሕይወት ያለው ጥቅስ ማውጫ ሆነ። አስቻለው ጥቂት ቃላትን ለመናገር ፍንጭ ሲሰጡት የትኛውንም ጥቅስ በአንድ ወይም በሁለት ደቂቃ ውስጥ ያገኛል። እንደዚህ ዐይነት ነገር አይተን አናውቅም።

ከአነርሱ ጋር በምናሳልፈው ጊዜ ሁሉ አንድ የቀረ ነገር እንዳለ ይሰማን ነበር። የእሑድ ሥራ የበዛበት መርሐ ግብራችን ከአንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወደ አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይወስደን ነበር። ልክ እንደ ደረስን ይጀምሩና እስክንሄድ ድረስ ይቀጥላሉ። በአንድነት የምንጸልይበት ጊዜ አልነበረም። በድንኳኑ ውስጥ ከቡድኑ ጋር ረጅም የጸሎት ጊዜ እንዲኖር ማድረግ መልስ ሊሆን እንደማይችል አስተዋልን። ብዙዎች ገና ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አልተቀበሉትም ነበር። በዚህ ሁኔታ የነበሩት ደግሞ በጣም ብዙ ሰዎች ናቸው። ነገር ግን አንድ ጊዜ በአንድ ቦታ ከልባችን ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር በቂ ጊዜ መውሰድ ነበረብን።

አንድ ቀን ምሽት ላይ በግሮስ ቤት ትልቅ ቡድን ሆነን የመሰብሰብ ዕድሉን አገኘን። በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ አጠናን፤ ከዚያም ሌሊቱን ሙሉ ስንጸልይና ስንወያይ ቈየን። በጣም ጥሩ ጊዜ ነበር ነገር ግን በመጠኑ ሰው ሠራሽ ሁኔታ ተከሥቶ ነበር።

እሑድ ቀን ቀያ ድንኳኑ ጋ ስንደርስ፣ ትንሽ ሴቶችንና ሕፃናትን ብቻ አስቻለው እያስተማራቸው አገኘን። ብዙ ጊዜ እኛ ስንደርስ ብዙ ሰው ነበር የሚጠብቀን። ሁሉም የት እንዳሉ ዐሰብን፤ ከዚያም ግርማን ሰላም ለማለት ድንኳኑን ዐልፈን ሄድን። ከድንኳኑ ዐልፈን ግቢው ስንደርስ በጨርቅ ከተከለለው ቤት የሚወጡ ድምፆችን ሰማን። ቀረብ ብለን ሰንመለከት ክፍሉ ሁሉ ዐንገታቸውን ዝቅ አድርገው በሚጸልዩ ስዎች ተሞልቷል። አንድ ሰው በጉባኤው መካከል ቆሞ ይጸልይ ነበር። ሲጨርሱ እኛ ከመምጣታችን በፊት ለሳምንታት በዚያ ቦታ እየተገናኙ በኀብረት እንደሚጸልዩ ነገሩን። እኛን የተሰማን እነርሱንም ተሰምቷቸው ስለ ነበር፤ ተመሳሳይ ነገር አድርገዋል።

ወደ ዋናው ድንኳን ከመመለሳቸው በፊት ወልደ አረጋይ ሊያካፍላቸው የሚፈልገው ነገር እንዳለ ተናገረ። ብዙዎቹ እንደሚያውቁት ታኅሣሥ ላይ ወልደ አረጋይ በጠና ታሞ ነበረ። መኮ ለገና ወደ ወላይታ ስለ ሄደ፣ ወደ መሐል ሜዳ ጤና ጣቢያ መሄድ ነበረበት። አባቱ በዚያ ስለማኖር ወልደ አረጋይ መቄዶት ቻለ። ጤና ጣቢያ ብዙ መርፌ ተወጋ ግን ሕማሙ እየባሰበት ሄደ።

ብዙም ሳይቈይ ጠንቋዩ ወደ ቤት መጣ። ከዓመታት በፊት ጠንቋይ ሥራ እጥቶ አያውቅም ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ችግር እየተፈጠረ መጣ። ጠንቋዩ ቀድሞ እንደ ነበረው አሁን ደንበኛ የለውም። ጠንቋዩ በቁመቱ ልክ ብራና ላይ ተጽፎና ተጠቅልሎ እንደ ክታብ በዐንገቱ ላይ ማድረግ እንደሚያስፈልገው ለወልደ አረጋይ ነገረው። ወልደ አረጋይ ሲያመነታ ጠንቋዩ ተቈጣና፣ «ለርዳታ ወደ እኔ ካልመጣህ፣ ጥቅምት ዐሥራ ስድስት ቀን ትሞታለህ» አለው። ጎይሉን ሁሉ በማሰባሰብ ወልደ አረጋይ በእንቢተኝነት የጠንቋዩን መድኀኒት እንደማያስፈልገው ነገረው። ኢየሱስ ይንከባከበዋል። በሚያሳፍር ሁኔታ ገልመጥ ብሎ ከተመለከተ በኋላ ጠንቋዩ ቀኝ ኋላ ዞሮ ወጣ።

ይህ ውሳኔ በቤተ ሰቦቹ ላይ ወዲያውኑ ውጤት አመጣ። ወልደ አረጋይ የሞተ ያህል በጣም ማዘን ጀመሩ። ሴቶቹ ደረታቸውን ሲመቱና ፀጉራቸውን ሲነጩ ቤቱ በተስፋ መቊረጥ ሐዘን ተሞላ። ወልደ አረጋይ እንዴት ሞኝ ይሆናል!። ጠንቋዩ እኮ ሁልጊዜ ትክክል ነበር። ወልደ አረጋይ ለጠንቋዩ ባለመታዘዙ በራሱ የሞት ማረጋገጫ ሰነድ ላይ እየፈረመ ነበር።

ከጥቅምት ዐሥራ ስድስት በፊት ያሉት ዐሥር ቀናት በወልደ አረጋይ የጤንነት ሁኔታ ላይ ጕልቶ የሚታይ ለውጥ ሳያመጡ በሚያስገርም ሁኔታ ዐለፉ። ነገር ግን ሕማሙ አልባሰበትም፤ በተደጋጋሚም የትኛውም ጠንቋይ ቢሆን ከጌታ እጅ እንደማያወጣው በመጽሐፍ ቅዱስ የተገባለትን ቃል ወልደ አረጋይ ይናገር ነበር። ለዘመዶቹ ኢየሱስ ከጠንቋዩ እንደሚበልጥና እንደሚጠብቀው አስረዳቸው።

ወልደ አረጋይ ጠንቋይን ሲፈታተኑ የሞቱ ሰዎችን ያውቅ ነበር። ምንም እንኳ ጠንቋዩ ከተናገረው ጥቂት ጊዜ ያለፈ ቢሆንም፤ ሰውየው የሚገድል ርግማን ማምጣቱ ያልተለመደ አይደለም። ወልደ አረጋይ ለመቃወም የደፈረውን ሰውየ ጎይለኛነት አልናቀውም። ቢሆንም የኢየሱስን ጎይል ያውቅ ነበር። የኢየሱስ ጎይል እንደሚበልጥ ርግጠኛ ነበርና በሕይወቱ እርሱን ለመወራረድ ፈቃደኛ ሆነ።

መጨረሻ ላይ ጥቅምት ዐሥራ ስድስት ቀን ደረሰ። ወልደ አረጋይ አሁንም ታሞ ነበረ ነገር ግን አልሞተም። ቀኑን ሙሉ ሰዎች በእርሱ ላይ በቅርቡ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማየት በአንክሮ ሲመለከቱት ዋሉ። በጣም የፈሩት ነገር ሳይፈጸም ቀረ። ያ ቀን ለየት ያለ ነገር ሳይፈጠርበት ዐለፈ።

በማግስቱ ወልደ አረጋይ ትንሽ ተሽሎት ከእንቅልፉ ነቃ፤ ብዙም ሳይቈይ ቀያ ወዳለው ቤቱ ተመልሶ ለመሄድ ቻለ። ከዚያም በኋላ ቢሆን ሙሉ በሙሉ አልዳነም። ሕማሙም እየቀጠለ ሲሄድ ሕይወቱን መረመረ። ችላ ባለባቸው ሁኔታዎች ላይ ጌታ በጎጢአተኛነት ወቀሠው። ከጎጢአቱ ይቅር እንዲባልና እንዲነጻ ጸለየ። በሚቀጥለው ቀን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ክፍል መጣና ቡድኑ

እንዲጸልይለት ጠየቀ። በማግስቱ ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ ስድስት ሳምንት ሙሉ ይሰማው ከነበረው የሕማም ስሜት ተሻለው። በሳምንቱም ማለቂያ ላይ ሙሉ በሙሉ ዳነ።

ወልደ አረጋይ ታሪኩን እየተናገረ ሳለ፣ ጌታን ለጥበቃውና እርሱን እንዲመስለ ላደረገበት ሥነ ሥርዐቱ አመሰገነው። ጌታ እምነቱን በማጠንከር ብቻ ሳይወሰን፣ ለዘመዶቹ ምስክር እንዲሆን አደረገው። ከዚያ በፊት ሰዎቹ ማንም ሰው ጠንቋይን በተሳካ ሁኔታ ሲቃወም አይተው አያውቁም ነበር። ይህ ርምጃ ብዙ እንዲያስቡ አደረጋቸው።

በቀያ ከአገልግሎት በፊት የሚደረጉት ጸሎቶች የሁሉንም ፍላጎት የሚያሟሉ ሆነው ሳለ፣ በዚያ ያሉ መሪዎች አሁንም ዐልፎ ዐልፎ ተጨማሪ የጸሎት ጊዜ እንደሚያስፈልግ ዐሳቡ። በእነዚህ ቀናት ብዙ ጎሳፊነትና ልዩ ልዩ ተግባራት ነበሯቸው። ሚያዝያ ወር ላይ ሲሰበሰቡ ወደ እኛ ቤት አልመጡም። ነገር ግን በዲያቆን እርገጤ ቤት ተሰበሰቡ። በተቻለ መጠን ቀላል ለማድረግ ባለቤቱ ምንም ምግብ ማዘጋጀት እንደሌለባት ተስማሙ። ሁሉም ከመምጣታቸው በፊት በየቦታቸው ሊመገቡ ይችላሉ። የቀን ሥራቸው ተሠርቶ ሲያልቅ መሸት ሲል ለመሰብሰብ ዐቀዱ።

በተመረጠው ምሽት በኰረብታው ጕን ላይ ተፈልፍሎ በተሠራው ጠባብና ጠመዝማዛ መንገድ ላይ በቍልቍለት በፍጥነት ተንዘዝን። ፀሐይ ጠልቃ ነበር፤ እየጨለመና ብርድም እየመጣ ነበር። በዚያ ስናልፍ ውሾቹ ጮኹ። ነገር ግን ወደ እነርሱ ክልል ስላልተጠጋን እኛን አላስቸገሩንም። በረጅምና አድካሚ በሆነ የዕርሻ ሥራ ላይ ውለው ወደ ቤታቸው የሚመለሱ ገበሬዎችን መንገድ ላይ አግኝተን ሰላምታ አቀረብንላቸው። በመንገድ ላይ ብዙ ነገር ስላደረግን፣ የአንድ ማይል የእግር ጕዞአችን ሳናውቀው ዐለቀ።

እርገጤ ቤት ስንደርስ ብዙ ጓደኞቻችን ቀድመውን ደርሰው ነበር። በዓሉን በማስመልከት መሬቱ ላይ በሙሉ ሳር ተጐዝጕዞ ነበር። ይህ ለሁሉም ነገር ጣፋጭና ዐዲስ መዐዛ ሰጠው። ሁለት የጋዝ ፋኑሶች ደመቅ ያለ የብርሃን ወገግታ ረጭተውበታል። ወዲያውኑ ሁሉም ሰው መጣ። ትልቁ ክብ ክፍልም ሞላ።

አንድ ወይም ሁለት ሰዓት ያህል በመዘመርና መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት ዐለፈ። ነገር ግን አብዛኛው ጊዜ ጌታ በሕይወታቸው ያደረገውን ለመመስከርና ለመጸለይ ነበር የተመደበው። ተሳታፊዎቹ ለሚመጡት ቀናት ጌታ እንደሚመራቸው ርግጠኛ መሆን ይፈልጉ ነበር። በተጨማሪም ሕያው እግዚአብሔርን ስለማያውቁ አርቶዶክስ ጓደኞቻቸው ሽክም በጣም ይሰማቸው ነበር። ሊያቆሙ ሲሉ እኩለ ሌሊት ነበር።

ጸሎቱን ስንጨርስ እንደምንሄድ ዐስበን ነበር። ነገር ግን ለመሄድ ከመነሣታችን በፊት ጥቂት ምግብ አቀረቡልን። በራሳቸው

ውሳኔ ተሰብስበው ምግብ መቅረብ እንዳለበት ተስማመተው ነበር። ጎላፊነቱን ተከፋፍለው እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ ምግብ ይዘው መጥተዋል። ብዙ ትላልቅ መሶቦች ላይ እንጀራና ወጥ አድርገው አቀረቡና እኛ በመሶቦቹ ዙሪያ ተቀመጥን። ሁላችንም እንጀራውን በቀኝ እጃችን እየቁረስን በወጥ ስናጠቅስ፣ ልዩና እጅግ የጠነከረ ትስስርና ዝምድና በመካከላችን እንዳለ ተሰማን። አንድ ላይ መመገብን የመሰለ መልካም ነገር ምን አለ? በእውነት የአንድ ቤተ ሰብ አባላት ነበርን።

ብዙዎቹ በዚያ ቁይተው ሌሊቱን በመሬት ላይ ተኝተው ዐደሩ። እኛ ግን በድንኳኑ ውስጥ ወዳለው ወደ ራሳችን መኝታ ተመልሰ መሄድን መረጥን። ባትሪአችንን ይዘን በግርማ፣ በአስቻለው በሲደልል ሽኚነት በድንጋያማው መንገድ አደርገን በግርማ ግቢ ወደሚገኘው ድንኳናችን ተመለስን። መንገድ ላይ አንድ ላይ እየተነጋገርን ስንሄድ ደስተኞች ነበርን። እግዚአብሔር በመልካምነቱ እስክንጥለቀለቅ ድረስ ሞልቶን ነበር። ከዚህ ሁሉ የተነሣ ብርዱንም አላስብነውም።

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።

የሐዋርያት ሥራ 1÷8

እስከ ምድር ዳርቻ

ምንም እንኳ ብዙ ጊዜያችንን መጽሐፍ ቅዱስ በማስተማር ብናሳልፍም፣ የማኅበረ ሰቡ ልማት ሥራ አልተረሳም። ከምናከናውነው ሁሉ ዋንኛውን ክፍል የሚይዘው እርሱ ነበር። ሁልጊዜ በጤና ጣቢያ ያሉትን ሰዎች ለመርዳት ቀላል መድኀኒቶችን እንይዝ ነበር። በብዙ ቦታዎች ያሉ ሴቶች የፀጉር መፍቻ ማሽኖችን በመጠቀም ይለማመዱ ነበር። በፀሐይ ሲና የነበረች እንዲት ወጣት ሴት በመፍተያ ማሽን አጠቃቀሟ ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረገች ነበር። በተደጋጋሚ በርካታ የሚሸጡ በጎችንና ዶሮዎችን አዘውትረን በመኪና እንጭን ነበር። በተጨማሪም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በየወሩ የሚካሄድ የምንጣፍ ገበያ ነበረን።

ሊንና ሬይ ክብቶች የሚጠጡበትን ሴቶቹ ውሀ ከሚቀዱበት ምንጭ ለመለየት ምንጮችን በማጽዳትና በመጥረግ ዕገዛ አደረጉ። የአቃፌ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እንደ ጠበል የሚጠቀሙበት ምንጭ እንዳይበከልባቸው ዙሪያውን ግንብ እንዲሠራላቸው ሬይን ጠየቁት። የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንዶች የጠበል ዙሪያ በተገነባ ዕለት ቀኑን ሙሉ ከሬይ ጋር ሲሠሩ ዋሉ።

ከሁሉ በላይ አስደሳች የነበረው ፕሮጀክት ግን በተልባ ፋብሪካው የታየው እድገት ነበር። ብዙ የመንዝ ገበሬዎች ተልባ ያመርቱ ነበር። ሚስቶቻቸው ዘሩን በወጥ ውስጥ መጨመር ይወዱ ነበር። እንዲያውም ከተልባው ዱቄት ያልተለመደ መጠጥ ይሠራሉ። ነገር ግን ከተልባ ዘር ዘይት ተጣርቶ እንደሚወጣ ወይም በአንዱ ውስጥ የተደበቀ ጠንካራ ቃጫ እንዳለ አያውቁም ነበር።

ለብዙ ክፍለ ዘመናት በዓለም ዙሪያ በተለያዩ ክፍሎች ያሉ ሰዎች ቃጫውን ለብዙ ጊዜ የሚያገለግለውን የላይነን ጨርቅ ለመሥራት ይጠቀሙበት ነበር። በመንዝ የሚኖሩት ሰዎች ስለ ግንዱ የሚያውቁት ነገር የጭድን ያህል እንደማይጠቅምና ለከብቶች መኖ እንደማይሆን ብቻ ነው። ተልባ በቀላሉ የማይጐብጥና አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሣ ማገር በመሆን አይጠቅምም፤ ጭቃ ሲቦካበት ቢሞከርም እግር ይወጋል። ለማገዶነት እንኳ አይጠቅምም።

ሊን በተሻሉ የተልባ ዘሮች ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ጀመረ። በመንዝ የሚያድገው ተልባ ቁመትም ከአንድ ጫማ የማይዘል ነው። ለመከራ በትንሽ መሬት ላይ ከሦስት ጫማ በላይ የሚያድጉ ጥቂት የተልባ ዘሮችን ዘራ። በተጨማሪም በመንዝ አማካይ ምርት አራት ለአንድ ያህል ነው ማለት የተዘራው አራት ዕጥፍ ገደማ ነው የሚገኘው። ከዐዲሶቹ ዘሮች መካከል ጥቂቶቹ ሃያ አንድ የሚሆን ምርት አስገኙ።

ምርምሮቹ የተካሄዱት የመንዝ ገበሬዎች ልክ በዐሥር ሺ ጫማ ከፍታ ላይ በሚያጋጥማቸው ተመሳሳይ ሁኔታዎች ላይ በመመሥረት ነው፣ ይኸውም ቀዝቃዛ ሌሊቶች፣ የማያቋርጥ ነፋስና በቂ ያልሆነ ዝናብ ባለበትና እንደዚሁም በቂ ዐፈርና ማዳበሪያ በሌለበት ሁኔታ ማለት ነው። ዘሮቹ ይህንን ሁሉ ካልተቋቋሙ ለመንዝ ምንም ጥቅም አይኖራቸውም። ሊን በከፍተኛ የዐየር ጠባይ ላይ የተሞከሩ የስንዴ፣ የገብስና የተልባ ዘሮችን ተጠቀመ። አዝመራው ሲደርስ የዕርሻ ማሳያ ቀን አዘጋጀን። ሁሉም ሰዎች መጥተው እንዲያዩ ተጋበዙ። የሙከራ የዕርሻ ቦታዎቹን ዙሪያ ሲጐበኙ በጣም ተደነቁ፤ ከዚያ በፊት እንዲህ ዐይነት ሰብል በፍጹም አይተው አያውቁም ነበር።

ከዚያም ሬይ ግንዱን ሳይገዱ የተልባውን ዘር እንዴት መልቀም እንደሚችሉ ለሰዎቹ አሳያቸው። ፈላሽ መርጫ እንዲኖረው በአንደኛው ጫፍ በኩል ቀጠን ብሎ ምስማር የተመታበት አንድ ሣጥን ሥራውን እንዲያፋጥን አደረገው። ከዚያ በኋላ የተልባ ቃጫ አምጥቶ እንደ ገመድ ጠቀለለው። ግንዱን እንዲሰብሩት ጋበዛቸው። በሁለቱም ጫፍ ሰዎች እየጐተቱት እንኳ ፈጽሞ ሊሰበር አልቻለም። ምስጢሩ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ጓጉ። ምስጢራዊው ቃጫ ከየት መጣ?

ሬይ በጥንቃቄ የጥንቱን የተላና እግር ቃጫ አወጣጥ ዘዴ አሳየ። በመጀመሪያ የተልባ እግሮቹ ውሃ ውስጥ ይዘፈዘፋሉ። በመንዝ ቀዝቃዛ የአየር ንብረት ይህ ከአንድ ወር በላይ ይወስዳል። ግንዶቹ መበስበስ ሲጀምሩ እንዲደርቁ ይሰጣሉ። መጨረሻ ላይ ልክ እንደ መንዝ የአሠራር ልማድ በክምር ውስጥ ተደርገው በዱላ ይደበደባሉ። በግንዱ ላይ ያለው ቅርፊት ሲወድቅ ቀጭኑ ጠንካራ ቃጫ ይወጣል። ሬይ እዚያ ድረስ ነበር መሄድ የነበረበት ሰዎቹ በቃጫዎቹ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ። እያንዳንዱ ወንድ ልጅ በልጅነቱ ክርና ገመድ እንዴት እንደሚሠራ ይማራል። ሁሉም ሴቶች ደግሞ ጥጥና ሱፍ የመፍተል ጥበብ ይማራሉ። ጥጥን በሚሸምኑበት በተመሳሳይ መንገድ የተልባው ቃጫ ክር ልብስ ወይም ጀኒያ መሥሪያ መሆን ይችላል።

ለማስተማር በጣም የጓጓንበት ሌላው የልማት ተግባር አካል መስኖ ነበር። በመንዝ ግብርና ሙሉ በሙሉ በዝናብ ላይ የተመረኰዘ

ነበር። በዓመት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ማረስ አይችሉም። በዝናብ ወቅት ከበቂ በላይ ውሃ አለ፤ ነገር ግን በኰረብታዎቹ ወደ ታች ከቊጥጥር ውጪ ሆኖ መሬቱን እየሸረሸረ ይጐርፋል። ውሀው ተገድቦ ወይም ታቊሮ አያውቅም።

ሁልጊዜ ወደ አዲሰ አበባ በመኪና ስንሄድ፣ ከትናንሽ ምንጮች በቀላሉ በመሬት ስበት ፍሰት መሠረት በተሠራ መስኖ የተዘሩ ሁለት አዝመራዎች በሚታዩባቸው ማራኪ ሁለት ሸለቆዎች በኩል እናልፍ ነበር። በጣም ትንሽ ወንዝ ሁሉንም ሸለቆ ዓመቱን ሙሉ አረንጓዴ ማድረግ ይችላል። ነገር ግን መንዜዎች በተፈጥሮ ጎረቤቶቻቸውን የሚጠራጠሩ ናቸው። የመስኖ ቦይ የብዙ ሰዎችን መሬት ማቋረጥ አለበት። እርስ በርስ መተባበርን ይጠይቃል ማለት ነው። ገበሬዎቹ ይህ ሐሳብ ሲቀርብላቸው አንድ ሰው ከሚደርሰው በላይ ውሀ ይወስዳል ብለው ፈሩ። ሰዎቹን በአንዱ በተመረጠ ቦታ እንዲሰማሙ ለማድረግ ሞከርን፤ ነገር ግን አልተሳካልንም። ሰዎቹ ለሥራው አልተዘጋጁም ነበር።

በመንዝ እየቈየን ስንሄድ አንድ አስደሳች ነገር አገኘን። ከጅምሩ የማኅበረ ሰብ ልማት መርሐ ግብራችን ወደ ዐዳዲስ ቦታዎች የመግቢያ ፈቃድ እንደሚያስገኝልን እናውቅ ነበር። የትም ቦታ ብንሄድ ሁልጊዜ በምናስተምረው የትኛውም ነገር ፍላጎት የሚያድርባቸው ጥቂት ሰዎች እናገኝ ነበር። ነገሮችን በተሻለ መንገድ የመሥራትን ጥቅም እንዲያዩትና እንዲያምኑበት ለማድረግ ግን ከፍተኛ ትግል ነበረብን።

ከጊዜ በኋላ ሁሉ እየተለወጠ ሄደ። ክርስቶስን ወደ ሕይወታቸው ጋብዘው የተቀበሉት የአኗኗር ሁኔታቸውን ማሻሻያ መፈለግ ጀምረው ነበር። ቤተ ሰቦቻቸውን በተሻለ መንገድ ለመንከባከብ ሙከራ እያደረጉ ታዩ። የመሻሻል ፍላጎት ነበራቸው፤ ዐዳዲስ ነገሮችን ለመሞከርም ፈቃደኛ ነበሩ። አንድ ነገር እንደሚረዳቸው ከተናገርን፣ ቃላችንን አክብረው መቀበል ጀምረዋል። እስካሁን አታለናቸው አናውቅምና። ስለዚህ የእኛን ምርጥ ዘሮችና የዕርባታ እንስሳት ተቀብለው ማርባት የሞከሩት እነርሱ ነበሩ። ጎረቤቶቻቸው እነርሱን ከተመለከቱ በኋላ የእነርሱን ፈለግ ለመከተል ወሰኑ።

ወጣት ወንዶች በመሪነት እያደጉ የነበረው በቀያ ብቻ አይደለም። በፀሓይ ሲናም ለዚህ ተግባር ተስማሚ የሆነ ጥሩ የተማሪዎች ቡድን ነበር። የሆነው ሆኖ ብዙዎቹ ትልልቅ ሆነው በቤታቸውና በቤተ ክርስቲያናቸው ከባድ ኀላፊነት የነበረባቸው ወይም ልጅ ሆነው ለመሪነት ገና ያላደጉ ነበሩ።

ኀይለ ጊዮርጊስ የማይረሳ ለየት ያለ ባሕርይ ያለው ሰው ነበር። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርሐ ግብሩ በመጀመሪያ መምጣት ሲጀምር፣ የሚያደርገውን ሁሉ በጥንቃቄና በማስተዋል የሚያደርግ ሰው ነበር። በጣም ወግ አጥባቂና ለቤተ ክርስቲያኑም እጅግ በጣም ታማኝ ነበር። ሁሉንም ነገር ሲያደምጥ በተለይ እያንዳንዱን ዐዲስ

ሐሳብ ከሁሉም አቅጣጫ እየመረመረ በአእምሮው የማሰላሰል ልምድ ነበረው።

ጎይለ ጊዮርጊስ እጅግ በጣም ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ነበረ፤ ጌታንም በሰዓቱ ነበር ያወቀው። ከፀሓይ ሲናው ተማሪዎች ቡድን ጉበዝ ሰባኪ እርሱ ስለ ነበር፣ ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያንና ጎሙስ ጎሙስ በጤና ጣቢያው የመስበክ ዕድል ይሰጠው ነበር። ሲሰብክ ሁልጊዜ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ሆነ የሚያመለክተውን ነጭ ጥምጣም ጭንቅላቱ ላይ ይጠመጥም ነበር። የመንዝ ሰው እንዳልሆነ የተረዳነው ካወቅነው ከዓመት በኋላ ነበር። ቤቱ የአራት ቀን የእግር ጉዞ ተሂዶ በሚገኘው ቦረና ውስጥ ነው። ወደ ፀሐይ ሲና ከዐምስት ዓመት በፊት የመጣው፣ ቀሳውስትን በማሠልጠን በሚታወቀው ትምህርት ውስጥ ቤት ለመማር ነው። ጎይለ ጊዮርጊስ የምንጣፍ ሸማኔም ነበር።

በመንዝ ሚሲዮናዊ ሥራችንን ስንጀምር በፀሓይ ሲና መኖር የእኛ ምርጫ አልነበረም። የጌታ እጅ እንደ ነበረበት ግልጽ ነው። ከመንዝ የቀሳውስት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤቶች በሙሉ የሚሻለው ትምህርት ቤት ደጃፋችን ላይ ነበር። በሥልጠናው ላይ የነበሩ ብዙ ዲያቆናት ወደ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ይመጡ ነበር። ከየቦታው ይልቁንም ከመንዝ ውጪ ካሉ ስፍራዎችም ሰዎች እንደሚመጡ ተረዳን። ከዚህ የበለጠ ምቹ ቦታ ላይ ልንሆን አንችልም።

አንድ ቀን ጎይለ ጊዮርጊስ ራእዩን አካፈለን። ከእርሱ ጋር ቦረና ሄደን በዚያ መጽሐፍ ቅዱስ እንድናስተምር መፈለጉን ነገረን። በዚያ እንድንኖርም እንኳ የበለጠ ይወድ ነበር። ያንን ማድረግ ካልቻልን ደግሞ እንድንጉበኘው ፈለገ። ቦረና የአየር ማረፊያ እንዳለና ከአዲስ አበባ በሳምንት አንድ ጊዜ የመንገደኞች አውሮፕላን እንደሚመጣ ነገረን። የእኛ ሚሲዮን አውሮፕላን ከመንዝ ወደ ቦረና ሊወስደን ይችል እንደ ሆነ ዐሰበ።

ጎይለ ጊዮርጊስ የታየው ከጉሂችን ጋር የተያያዘው አንድ ችግር በዚያ የሚጠብቀን ማንም አለመኖሩ ነው። የአየር ማረፊያው ከእርሱ መኖሪያ ቤት የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ያስሄድ ስለ ነበር፣ ያለ ምንም ርዳታ ሁሉንም ጓዛችንን እኛ ራሳችን መሸከም ይኖርብናል። በተጨማሪም እሑድ ትምህርቶችን ላለመሰረዝ በሳምንት ውስጥ ለመሄድ ፈለግን። በሥራ ቀን ሰዎችን መሰብሰብ በጣም አስቸጋሪ እንደሚሆን ዐሰበ። ነገር ግን በሳምነቱ አጋማሽ ላይ ጉብኝት ማድረግ ከምንም ይሻል ነበርና ለዚያ ጊዜያዊ ዝግጅት አደረግን።

የሚቀጥለው የእኛ ሚሲዮን የውሳኔ ሰጪ ኮሚቴ ስብሰባ እኔና ሬይ ወደ ቦረና ሄደን ጥናት እንድናደርግ ወሰነ። ሊወስዱን ይችሉ እንደ ሆነና መቼ ሊወስዱን እንደሚችሉ የሚስዮናችንን የአየር መንገድ አነጋገርን። የአየር ማረፊያውን እንደሚያውቁትና ወደዚያ

ለመሄድ ፍቀደኛ እንደ ሆኑ ነገሩን። በመጀመሪያ ወደዚያ ስፍራ የሚደረገው በረራ ከአራት ቀን በኋላ ሰኞ ቀን ነበር። ከጤና ጣቢያው ጉዞ ጋር በማያያዝ በሚቀጥለው ዐርብ መጥተው ሊወስዱን እንደሚችሉ ተነገረን።

ወደ ወንዝ ተመልሰን ዜናውን ለጎይለ ጊዮርጊስ ለመንገር በጣም ጓጓን። ምን ያህል እንደሚደሰት እናውቅ ነበር። ሚሲዮናችን ጎሙስ ዕለት ዐርብ እንደምንሄድ ስለ ገለጸልን፣ ለሚቀጥለው ቀን ጉዞ ተዘጋጀን። ጎይለ ጊዮርጊስን እሑድ ዕለት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ እንደምናገኘው ርግጠኞች በመሆን ቅዳሜ ዕለት ወደ መንዝ ተመለስን። ጥሩውን ዜና ለጎይለ ጊዮርጊስ ለመንገር በጣም ጓጕተን ነበር ነገር ግን አልመጣም። ከጥናቱ ቀርቶ የሚያውቀው በጣም ጥቂት ለሆኑ ጊዜያት ስለ ነበር፣ ለምን እንዳልመጣ ለሚቀርብለት ጥያቄ ጥሩ ምክንያት እንደሚኖረው አልተጠራጠርንም።

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ላይ በራችንን አንኳኳ። የማናውቀው አንድ ሽማግሌ ዐብሮት ነበር። በደስታ ፈገግ አያለ ጎይለ ጊዮርጊስ አባቱን አስተዋወቀን። ልክ ከአንድ ቀን በፊት ከቦረና መጥቶ ነበር። ጎይለ ጊዮርጊስ በፀሐይ ሲና ዐምስት ዓመት ኖሯል፤ እርሱን ለመጐብኘትም ከቦረና ሰው ሲመጣ ይህ የመጀመሪያው መሆኑ ታወቀ። የአባቱ ጉዞ በጣም አስቸጋሪና አድካሚ ጉዞ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ቦታዎች ላይ መጥፎ ነበር።

በዚያ ጊዜ ለመምጣት ምን እንዳነሣሣቸው አባቱን ጠየቅናቸው። የተለየ ምክንያትም እንደሌላቸው ነገሩን። ጎሙስ ዕለት ልጃቸውን ሄዶ ለማየት ሊገልጹት የማይቻል ከፍተኛ ጕጕት ዐደረባቸው። ስለዚህ ጉዞ የጀመሩት በአጠቃላይ አቅጣጫውን ተከትለው እንጂ ዋና መንገዱን አያውቁትም ነበር። መንገድ ላይ ዕርዳታ እየጠየቁ እሑድ ከሰዓት በኋላ መንዝ ደረሱ። በተጨማሪም ባልተወቀ ምክንያት በዚያ ዕለት ጎይለ ጊዮርጊስ ወደ ቀያ ዐብሮን አልሄደም ነበር። ስለዚህ አባቱ ሲመጡ እርሱ ቤቱ ይገኝ ነበር። የእግዚአብሔር እጅ እየሠራ እንደ ነበረ በግልጽ ታወቀን።

ከአራት ሳምንት በኋላ ቦረናን ለመጐብኘት የነበረንን ዕቅድ ለሁለቱም ነገር ናቸው። ጎይለ ጊዮርጊስ በደስታ ተሞላ። ከደስታው የተነሣ መቁየት አቃተው። እርሱና አባቱ በከፍተኛ ጕጕት ዕቅድ አወጡ። ከዚያም ጎይለ ጊዮርጊስ ለቀሳውስቱና ለማኅበረሰቡ መሪዎች እንደምንመጣ ደብዳቤ ጻፈ። በተጨማሪም ስብሰባዎችን ለማዘጋጀት የሚፈልጉ ከሆነ፣ ፊልሞችንም ለማሳየት ይዘን እንደምንመጣ በደብዳቤው ነገራቸው። ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከመጡ ሃያ አራት ሰዓት ሳይሞላቸው የጎይለ ጊዮርጊስ አባት ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

በለበሱት ሽሚዝ ኪስ ውስጥ የእኛ ልዩ ደብዳቤዎች ነበሩ። የጉዞአችን ሁኔታ ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ሊገለጽ አይችልም ነበር።

የጉዞው ቀን ደረሰና አውሮፕላኑን ለማግኘት ወደ መሐል ሜዳ በመኪና ሄድን። ስለ ጉዞው በጉጉት እያሰብን ስለ ነበር፣ አወሮፕላኑ በአየር ማረፊያው ሲደርስ ተደሰትን። አውሮፕላን አብራሪው አየር ላይ እንዳለ ድንገተኛ ጥሪ እንደ ደረሰን ነገረን። ነገር ግን እኛን ለመውሰድ ጉዞ ጀምሮ ስለ ነበር ወደ ኋላ አልተመለሰም።

ትንሹ አውሮፕላን በመንደርደሪያው ላይ በፍጥነት በኋላው አቧራ እያበነነ ሲሄድ የጎይለ ጊዮርጊስ ዐይኖች ፈጠጡ። ወዲያውኑ አየር ላይ ተንሳፈፈ። ከታች መሬት ላይ የሚታየው ነገር እያነሰ እያነሰ ሄደ፣ ነገር ግን እየቄየ ቀስ በቀስ የሚታዩ ነበሩ። አውሮፕላን አብራሪው ከዚያ በፊት ቦረና ሄዶ አያውቅም። ስለዚህ ከካርታው ላይ በኮ ምፓስ እያነበበ ትክክለኛውን አቅጣጫ ያዘ። በዚያ ሁኔታ ለሃያ ስምንት ደቂቃ በርረን ቦረና ደረሰን።

ጎይለ ጊዮርጊስ ለብዙ ጊዜ ዐይቹን ከመሬት ላይ ሳይነቅል ቈየ። መጀመሪያ ወደ መንዝ ሲመጣና ዘመዶቹን ለመጠየቅ ሁለት ጊዜ ወደ ቤት ሲሄድ በመንገዱ ላይ የነበሩትን የምልክት ድንጋዮች በእጁ እየጠቁመ ያሳየን ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ከተለመደው ትልቅ የአቅጣጫ ለውጥ በማድረግ አውሮፕላኑ ቀጥታ መብረር ቀጠለ። ከዚያ በኋላ ለጎይለ ጊዮርጊስ ሁሉ ነገር ያልተለመደ ሆነበት። ከሃያ ዐምስት ደቂቃ በኋላ አውሮፕላን አብራሪው የሚታየው ነገር እንዳለ ጠየቀው። ሞከረ ነገር ግን አንድ ምልክት እንኳ ለይቶ ማሳየት አልቻለም። ሁለት ደቂቃ ዐለፈ። መጨረሻ ላይ ከሠለሳ ደቂቃ በረራ በኋላ ጎይለ ጊዮርጊስ በኰረብታው ትንሽ ክፍል ላይ ያለውን የቦርናን የአስተዳደር ሕንጻ ለይቶ አመለከተ። ይህ የሆነው ገና ቦታው ላይ ሳይደርስ ነበርና ትክክለኛውን የበረራ አቅጣጫ ለመያዛችን ማረጋገጫ ሆኖአል።

አውሮፕላኑ ሲያርፍ ወንድሞቹና አባቱ እኛን ሰላም ለማለት መጡ። እኛን ላለማጣት ከንጋት ጀምሮ ሲጠብቁን ውለዋል። አውሮፕላን አብራሪው ዕቃዎቻችንን ዐብሮን አያወረደ፣ ብዙ ዝናብ ጫልዘነበና አየር ማረፊው ካልጨቀየ ከአራት ቀን በኋላ ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ገባልን።

ዕቃ ላለማብዛት አንድ አንድ ተቀያሪ ልብስና ቀላል የመኝታ ከረጢቶችን ነበር የያዝነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፣ ፕሮጀክተርና የመኪና ባትሪ እንድናመጣ በጉትጉታ አሳስበውናል። በዚህ ጉዳይ ከመስማማታችን በፊት በቤታችን ጎምሳ ፓውንድ ክብደት ያለውን ባትሪ እንዴት እንደሚይዙት አለማምደናቸው ነበር። ሁለት ወንዶች በችግር በማንጠልጠያው ውስጥ ዱላ አስገብተው ትከሻቸው ላይ በማድረግ ሊሸከሙት እንደሚችሉ አረጋገጡልን።

የቀረውን ዕቃችንንም ለመሸከም ከወተወቱን በኋላ ለመሄድ ተነሣን። በዚያን ጊዜ ረፍዶአል፤ ፀሓይም በሙሉ ጎይሏ በመውጣት ላይ ነበረች። ሰማዩ ላይ ደመና አልነበረም። ቦረና ሰባት ሺ ጫማ ከፍታ ላይ ያለች ስትሆን፣ ከመንዝም ትሞቃለች። መንገዱ በኰረብታው ላይ ሽቅብ የሚያመራ ነበር። በመጨረሻ ጉብታው ጫፍ ላይ ስንደርስ ወዲያውኑ በተቃራኒው አቅጣጫ ወደ ታች መሄድ ቀጠልን። ከዚያ በኋላ ደግሞ ሌላ ተራራ መጣ። እንደርስ ይሆን ብለን ዐሰብን።

በቦረና ያሉት ሰዎች ብዙዎች እንደ መንዝ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ነበሩ። ነገር ግን ብዙ ሙስሊሞችም ነበሩ። በሚኖሩበት አካባቢ ስናልፍም ጓደኞቻችን ወደ እነርሱ እየጠቁሙ አሳዩን። እየሄድን ሳለ ለወደፊት የአየር ማረፊያ ሊሆን የሚችል ቦታ በዐይናችን እንፈልግ ነበር ነገር። ግን አልተሳካልንም። በበቂ ሁኔታ ትልቅ ወይም ሜዳማ የሆነ ቦታ አልነበረም።

ምንም እንኳ ሁሉንም ዕቃ ተሸከመው የነበረ ቢሆንም፣ ጎይለ ጊዮርጊስና ዘመዶቹ ብዙ ጊዜ እስክንደርስባቸው እየቆሙ ይጠብቁን ነበር። መጨረሻ ላይ ቤታቸው ስንደርስ ሰባት ማይል እንደ ሄድን ዐሰብን። በዚያ ርቀት አንድ ሺ ጫማ ወደ ላይ ወጥተናል፤ አንድ ሺ ዐምስት መቶ ጫማ ደግሞ ወደ ታች ወርደናል። ዐምስት መቶ ጫማ ደግሞ በድጋሚ ወደ ላይ ወጥተናል።

በቦረና ያሉ መኖሪያ ቤቶች ትልልቅና አራት ማእዘን ሲሆኑ ከመንዝ ትንንሽና ክብ ቤቶች በጣም ይለዩ ነበር። ጣሪያው ጫፍ ሲኖ ረው የብርድ ችግር ስለ ሌለ በአንዱ ጕን መጨረሻ ላይ ክፍተት ነበ ረው። ምሽት ላይ ሁሉም እንስሳት በቤቱ መግቢያ በር ላይ ይሆናሉ። የእንቅልፍ ጊዜ ሲደርስ ሁሉም ከሚተኙበት ከእሳቱ አጠገብ እንድንተኛ ተደረገ። ክፍሉ ውስጥ ካለው ከፍ ያለ ስፍራ ባሻገር ሁለት በራፎች፣ ፈረስ፣ ላም፣ ሁለት ፍየሎች፣ ስምንት በጎችና ጥቂት ዶሮዎች ነበሩ። ከጨለመ በኋላ ወይም ሌሊት ወደ ውጪ ለመወጣት ቢያስፈልግ፣ በእንስሳቱ መካከል በጥንቃቄ የሚረገጠውን ስፍራ ፈልጎ በማግኘት ነበር የሚታለፈው። በፈረሱና በበሬው ቀንድ መካከል ታከን ለማለፍ ስንገደድ ትልቅ የባህል ግጭት ውስጥ ገባን።

ራሳችንን ችለን ምግብ በሚያዘጋጁበትና በሚያስቀምጡበት በቤቱ ጠርዝ ላይ ለመተኛት እንደምንፈልግ ገለጽንላቸው። ከጥቂት ክርክር በኋላ መጨረሻ ላይ ተስማሙና ለመተኛት ተዘጋጀን። ዝናብ እየዘነበ ነበር። በእኛ አቅጣጫ በኩል በነበረ የጣሪያ ቀዳዳ ሰማዩን አሾልከን ማየት እንችል ነበር። ከዚህ የተነሣ ዝናብ በጣሪያው ቀዳዳ ገብቶ ቤቱ በሙሉ እንደሚበሰብስ ተረዳን። በትልልቁ ከሚያንጠባጥበው የጣሪያ ቀዳዳ ለመሸሽ ስንተረማመስ በአጠገባችን የተኙትን ሰዎችና የእንስሳቱን ሁኔታ ግምት ውስጥ ለማስገባት እንሞክር ነበር። በዚህ

ሁኔታ ዐልፎ ዐልፎ እያሸለብን የማያልቅ የሚመስለውን ሌሊት አሳለፍነው። በእግዚአብሔር ቸርነት ሌሊቱ ነጋ። በቀጣዩ ቀን ሌሊት እኛ እንድንተኛበት በቁሻሻው መሬት ላይ ጭድ ጉዘጉዘበት። ነገር ግን ከመተኛታችን በፊት ዝናቡ አቆመ። ተደላደልንና ሌሊቱን መሉ አንድ ነገር ሳንሰማ ተኝተን ዐደርን።

የጎይለ ጊዮርጊስ ወላጆች ደግ እንግዳ ተቀባዮች ነበሩ። የምንፈልገውን ነገር ሁሉ በግምት ለማወቅ ይሞክራሉ። በሚገባ ይመግቡን ነበር፤ በየሄድንበትም ቤት ሁሉ መስተንግዶው ተመሳሳይ ነበር። ጎይለ ጊዮርጊስ ያገኘው ሰው ሁሉ በደስታ የሚቀበለው በጣም የሚወደድ ሰው ነው። ከረጅም የዲቁና ሥልጠና መመለሱ አስደስቷቸዋል። እኛን ከሁሉም ሰው ጋር አስተዋወቀን፤ ለጓደኞቹም እኛን ማመን እንዳለባቸው ነገራቸው። ልንረዳቸውና ስለ ኢየሱስ ልናስተምራቸው ነበር የሄድነው። ከዚህም የተነሣ ቤሄድንበት ሁሉ የመመስከር ዕድሉ ነበረን። የመጽሐፍ ቅዱስ ፊልሞችን በተለያዩ ቤቶች ውስጥ በምሽቱ አሳየን። በዚህም ምክንያት ሁል ጊዜ ቤቶቻቸው በሰው የተሞሉ ነበሩ።

ረቡዕ ቀን ሃይማኖታዊ በዓል ነበረ፤ ስለዚህ ሁሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዱ። ጎይለ ጊዮርጊስ በእኛ ስለሚተማመን ያለምንም ጥያቄ በሥርዐቱ ላይ እኛም እንድንገኝ ተደረገ። በመንዝ ለሰባት ዓመት ኖረን ያላገኘነውን ተቀባይነት በአንድ ቀን በቦረና አገኘን። በጣም ያስደንቅ ነበር። ከሥርዐቱ ፍጻሜ በኋላ ሬይን እንዲሰብክ ጠየቁት፤ ከዚያም ለጎይለ ጊዮርጊስ ዕድል ተሰጠው።

ጎይለ ጊዮርጊስ መጽሐፍ ቅዱሱን በደንብ እንደሚያውቅና ጥሩ ሰባኪ እንደ ሆነ አረጋገጥንላቸው። የውጭ አገር ዜጎች ስለ ሆነን ያከብሩን ነበር። ምንም እንኳ ወጣት ቢሆንም በእኛ ድጋፍ ጎይለ ጊዮርጊስን ሊሰሙት ፈቃደኛ

ሆኑ። ከእያንዳንዱ ፊልም በኋላ በዚያ ቀን ስብከት ሰብኮአል፤ ዕድሉን ባገኘ ጊዜም ሁልጊዜ ይመሰክር ነበር። ከዲቁና ሥልጠናው በኋላ ብቻ ውን ቢመለስ ለማግኘት ዓመታት የሚወስድበትን ክብርና ተቀባይነት ከእኛ ጋር በመሄዱ በዐጭር ጊዜ አገኘው።

ሥርዐቱ ከተፈጸመ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ለሌሎች ሰዎች በሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሰጠን። ከዚያም ቀሳውስቱ ጥቂት ዳቦ ከእነርሱ ጋር ተቀምጠን እንድንበላ ጋበዙን። በቦረና በቁየንባቸው አራት ቀናት በሙሉ ብዙ ሰዎች እኛን ለመጐብኘትና ከእኛ ጋር ለማጥናት ከሚሠሩበት ጊዜ ቀንሰው ይመጡ ነበር።

ምንም እንኳ በቦረና የሚኖሩት ሰዎች መንዝ ካሉት በጣም የተሻሉ ቢሆንም፤ አሁንም ልንረዳቸው የምንችልባቸው ብዙ መንገዶች እንዳሉ ተመለከትን። የሕክምና አገልግሎት በጣም ያስፈልጋቸው

ነበር። አካባቢው ለመስኖ በጣም አመቺ በመሆኑ፣ ብዙ ሰዎች የመስኖ ዕርሻን ለመሞከር ጓጉ። እንስሶቻቸው ብዙ ጊዜ ስለሚታመሙባቸው ችግር እያጋጠማቸው ታይቶአልና ለእነርሱ የእንስሳት ሐኪም ማግኘት ትልቅ ርዳታ እንደ ሆነ ተገነዘብን።

ብዙም ሳንቈይ የቦረናዎች ክርስትና እንደ መንዝ ሁሉ ከሰይጣን አምልኮ ጋር የተያያዘ እንደ ሆነ ተረዳን። የአድባር ዛፍ ሁሉም ነገር ላይ ጥላውን አጥልቶአል፤ ጠንቋዮቹም ጎይለኞችና ተደማጭነት ያላቸው ነበሩ። ልናደርጋቸው የምንችላቸው ብዙ ነገሮች ነበሩ። በዚህ አካባቢ መሥራት እንችል እንደ ሆነ ማሰብ ጀመርን። ይህንን ከልብ ዐሰብን። ተግባራዊ የምናደርገው ከሆነ፣ ሁሉን ዐይነት ትብብርና ድጋፍ እንደሚያደርጉና በተጨማሪም የምንኖርበትን ቦታ እንደሚሰጡን ቃል ገቡ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተመልሶ የመሄጃ ጊዜያችን ደረሰ። ጎሙስ ዕለት ከሰዓት በኋላ ወደ ከተማ ተመለስን። አውሮፕላኑ በጠዋቱ ይመጣ ስለ ነበር፣ ሌሊቱን ከአየር ማረፊያው አቅራቢ ማሳለፍ ነበረብን። ከቤተ ሰቡ ጋር በነበረ አንድ የድሮ ወዳጃችን ቤት ውስጥ ዐደርን። ያ ሰው ጎይለ ጊዮርጊስንና ሌሎች ዲያቆናትን ከፀሓይ ሲናው የቅስና ትምህርት ቤት ያስተምር ነበር። እኛ ዘንድ ሽመናን ከተማረ በኋላ ወደ ቦረና ለማስተማር ተመለሰ። ባለቤቱ ከማስተ ምራቸው ሴቶች መካከል አንዷ ተወዳጅ ተማሪዬ ነበረች። ጣፋጭ ምግብ አዘጋጅቶልንና ስለ ቀድሞው ጊዜና ስለ ቅርብ ጊዜ ወዳጆች ትዝታ እያወራን አስደሳች የሆነ ምሽት በዚያ ቤተ ሰብ ውስጥ አሳለፍን።

በዚያ ቀን ከሰዓት በኋላ በከተማው ተዘዋውረን ከብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ተዋወቅን። ከእነርሱ ጋር ለመቀራረብ ጥቂት ዕድል አግኝተን ስለ ነበር፣ እነርሱም እኛ ወደዚያ ሄደን እንድናስተምር ፍላጎት እንዳላቸው ገለጹልን።

ጠዋት ወደ አየር ማረፊያው ሄደን አውሮፕላን አብራሪው ባዘዘን መሠረት ጥቂት ድንጋዮችን አጽድተን ጨረስን። ከዚያም ለመጠበቅ ተቀመጥን። ካለፈው ምሽት በስተቀር በየቀኑ ትንሽ ትንሽ ዘንቦአል። በዚያን ጊዜ አየር ማረፊው ደረቅ ነበር፤ ስለዚህ አውሮፕላኑን ለማሳረፍ ምንም ችግር አይገጥመውም። ልክ ወደ ሌላ ዓለም ሄደን የመጣን ነበር የመሰለን። የአውሮፕላኑ መምጣትና ከአብራሪው ጋር ለመነጋገር ዕድሉን ማግኘታችን ወደ ምድር መለሰን። እኛን ሊወስደን በመምጣቱ ደስተኞች ነበርን፤ ሆኖም አንድ ቀን ወደዚያ ቦታ ተመልሶ የመሄድ ዕድሉን ለማግኘት ተመኘን።

«ሰባቱ ቀንም ሊፈጸም ሲቃረብ፣ ከእስያ አውራጃ የመጡት አይሁድ ጳውሎስን በቤተ መቅደስ ባዩት ጊዜ፣ ሕዝቡን ሁሉ አነሣሥተው ያዙት፤ እንዲህም አሉ ጮኹ፤ «የእስራኤል ሰዎች ሆይ፤ ርዱን ሕዝባችንንና ሕጋችንን እንዲሁም ይህን ስፍራ በማጥላላት በደረሰበት ስፍራ የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ የሚያስተምረው ሰው ይህ ነው፤ ከዚህም በላይ ግሪክን ወደ ቤተ መቅደስ አያስገባ ይህን የተቀደሰ ስፍራ የሚያረክሰው እርሱ ነው።»

የሐዋርያት ሥራ 21÷27-23

እስራት

በበልጉ ወራት የክትትል ትምህርት መርሐ ግብራችንን ስንጀምር፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ በጣም ታማኝ የነበሩትን ተማሪዎች ወደ አዲስ አበባ እንደምንወስዳቸው ቃል ገብተን ነበር። ብዙዎች ከመንዝ ወጥተው አያውቁም። የትልቁን ከተማ ድንቅ ነገሮችና ከሁሉም የሚበልጠውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለማየት ጓጉተዋል። ከሁሉ የሚበልጠው ግን በዚያ ካሉት ጥቂት ክርስቲያን ወንድሞች ጋር መተዋወቅ የሚችሉ መሆናቸው ነው። ከእነርሱ ቡድን ውጪ ወደ መንዝ የሄድነውን እኛንና ጥቂት ሰባክያንን ካልሆነ በቀር ሌሎች ክርስቲያኖችን አያውቁም ነበር። እይታቸውን የሚያሰፋበት አንድ ዕድል ይህ ነበር።

የግንቦት የመጀመሪያ ሳምንት ለትልቁ ጉዞ ተመደበ። በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ጉዞ አንድንጀምር ዐሥራ አንድ ዲያቆናት ከቁስ ግርማ ጋር ሌሊቱን በእኛ ቤት ለማሳለፍ መጡ። ወልደ ጻድቅን አዲስ አበባ እናገኘዋለን ብለን ተስፋ አድርገናል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ እርሱ በሥጋ ደዌ ሆስፒታል ውስጥ ቁይቶ መጨረሻ ላይ ሰው ሠራሽ እግር ተገጥሞለት ይገኝ ነበር።

ለጉዟችን ሁለት ላንድ ሮቨር መኪኖችን ይዘን ተንቀሳቀስን። በመንገድ ላይ ለማየት ያጓጓንን ቆም ብለን እያየን ሳለ፣ ጥርሳቸውና ፀጉራቸው ገና ምንም ያልሆነ በመርዝ የደረቁ ሬሳዎች የሞሉብትን ዋሻ ተመለከትን። በመንገዱ በአንድ በኩል ያለው ውሀ ወደ ቀይ ባሕር፣ በሌላው በኩል ያለው ውሀ ደግሞ ወደ ሜዲትራኒያን በሚፈስበትና አህጉሩን በሚከፍለው ዐሥራ ሁለት ሺ ጫማ ላይ ተጓዝን። የደናኪልን በረሓ አብዛኛ ክፍል ከባሕር ጠለል በታች ሆኖ በጨረፍታ ተመለከትነው። በተጨማሪም በትናንሽ ምንጮች መስኖ የተሠራባቸውን ሁለት ለምለም ሸለቆዎች አሳየናቸው።

መጨረሻ ላይ ዋናው ከተማ አዲስ አበባ ደረስን። ተማሪዎች ብዙ ነገሮች መመልከት ሲጀምሩ አመለካከታቸው እየሰፋ ሄደ። በሁሉም አቅጣጫ የሚሄዱ መኪናዎችና ቀኑን ሙሉ የሚበሩ መብራቶች ነበሩ። ተንቀሳቃሽ ማስታወቂያ ምልክቶችና ቴሌቭዥን የተማሪዎችን ትኩረት ተቈጣጠሩት። ረጃጅም ሕንጻዎች በየማእዘኑ ነበሩ። ሊታሰብ በሚችል ነገር ሁሉ በተሞላ የገበያ አዳራሽ ዐሥራ

ሁለት ፎቅ ባለው ሕንጻ አሳንሰር ውስጥ ዐለፉ። የአንበሳን ግቢ ሲጐበኙ የአንበሶቹን ባለ ግርማ ጩኸት መስማት ቻሉ። በሚሊዮኑ ስልክም ተራ በተራ እርስ በራሳቸው ተነጋገሩ። በክተማው ውስጥ የሚታዩ ድንቅ ነገሮች ማለቂያ አልነበራቸውም።

እኔና ሬይም በዚህ አጋጣሚ ጥቂት ዐዳዲስ ልምዶችን ቀሰምን። ትኩስ ምግብ ለአንድ ሰው በሃያ ዐምስት ሰንቲም የሚያቀርብ ምግብ ቤት አገኘን። የምግብ ቤቱ ደንበኞች የእኛን ቡድን ሴት ይልቁንም የውጪ አገር ዜጋ የሆነች እንዳለበት ሲናገሩ ሰማናቸው። ምግቡ ጥሩ ነበር፤ ዋጋውም ትክክለኛ ዋጋ ሆኖ ስላገኘነው፣ በድጋሚ ሄድን። አንድ ቀን በምግብ ሰዓት ከተማ ውስጥ ገበያ ላይ ነበርን። ለተበላው ምግብ ሁሉ ዐሥራ ሁለት ብር ከጎምሳ ሳንቲም ብቻ በሚከፈልበት ምግብ ቤት ሁላችንም ተመገብን። በሽቀጣ ሽቀጥ ሱቆች ውስጥ የምግብ ዋጋዎች ከፍተኛ ስለ ሆኑ፣ ትክክለኛ ዋጋ መሆናቸውን ለማመን ያስቸግር ነበር። የምግቦቹ ጣፋጭ መሆን ግን ከሁሉም ይበልጣል።

ነገር ግን እነዚህ ትኩረት የሚስቡ ነገሮች ሁሉ አዲስ አበባን እንድንጐበኝ ያደረገንን አንደኛ ምክንያት እንድንረሳ አላደረጉንም። ቅዳሜ ጠዋት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራልን ጐበኘን። በክረምት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ያስተምራቸው የነበረው ኢሰይያስ በካቴድራሉ አቅራቢያ ባለ ቢሮ ውስጥ ይሠራ ነበር። እርሱን ድጋሚ ስናገኘው ሁላችንም ልክ ቤተ ሰባዊ የሆነ ግንኙነት እንደገና እንዳደረግን ተሰማን። ወደ ካቴድራል ሄደን አንድ ቁስ ሲያስጐበኘን እርሱም ዐብሮን ነበር።

ቅድስት ሥላሴ ከኢትዮጵያውያን ጥበብ በጣም የሚያስደንቅ ሀብት ነው። በልዩ ልዩ ሕብረ ቀለማት የተዋቡ መስኮቶችና ትልልቅ ሥዕሎች በግድግዳውና በጣሪያው ላይ ተሥለው ይታያሉ። በጌጥ የተንቈጠቈጡ የነገሥታት መቃብሮች ልዩ የክብር ስፍራ ይዘዋል። የቀድሞ ንጉሣውያን ዘውዶችና የንጉሥ ካባዎች ወደሚቀመጡበት ክፍል ገባን። ውብታቸው አስደናቂ ነበር። በዚያ ቀን ጠዋት ሌሎች ብዙ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ጐበኘን። እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተለየና የራሱ የሆነ ማራኪ ገጽታ አለው። ረጅም ካባ የለበሱ አንድ ሽማግሌ መነኩሴ ታሪካዊ የሆነ አንድ ቤተ ክርስቲያንን ከፈቱልን። ሁላችንም ወደ ውስጥ ከገባን በኋላ በሩን ከኋላው ቀረቀሩት። በጐበኘናቸው አብያተ ክርስቲያናት ውበት ላይ ምንም ጥያቄ አልነበረም። ነገር ግን ሕይወት ያለው ነገር አልተገኘም።

ከመንዝ ከመምጣታችን በፊት የፖለቲካ መረጋጋት በሌለበት ጊዜ ወደ አዲስ አበባ እነርሱን ስለ መውሰዳችን ከእኛ ሚሲዮናውንና በመንዝ ከሚገኙ ጓደኞቻችን ጋር ጸሎት አድርገናል። የተቃዋሚዎች መታሰር በመጠኑ እየተለመደ ሄዶአል። በቅርብ ጊዜያት በአዲስ አበባ በተደጋጋሚ ችግሮች ይከሠቱ ነበር። ተማሪዎቻችንን ወደ ከተማ

ወስደን ለችግር ልናጋልጣቸው አልፈለግንም። ነገር ግን ጉዞውን ለማድረግ ቃል ስለ ገባንላቸው በሁኔታው እንደሚደሰቱበት እናውቅ ነበር። መጨረሻ ላይ ኃላፊነቱን ወስደን መሄዳችን እንደሚበልጥ ወሰንን።

ቅዳሜና እሑድ የምንሠራውን እያቀድን ሳለ ልንሳተፍበት የሚገባ ጥሩ የፐሮቴስታንቶች የጸሎት መርሐ ግብር ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ እንዳለ ተነገረን።ስለ ቡድኑ ከዚህ በፊት የሰማን ቢሆንም፣ ወደ ፕሮግራሞቻቸው ሄደን አናውቅም። ስብዙ ዓመታት የስደት ዒላማ ሆነው ኖረዋል፤ ብዙዎቹም ለጥቂት ጊዜ ታስረው ቈይተዋል።

ከመንግሥት ለውጥ በኋላ የሚያጋጥሟቸው መለስተኛ ችግሮች ነበሩ። ዋናው ተቃዋሚ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ድሮው አይቃወማቸውም ነበር። ለራሱ ህልውና በመታገል ሥራ በዝቶበት ታይቶአል። በቅርቡ ጳጳሱ ከሥልጣናቸው ወርደው ስለ ታሰሩ፣ በርሳቸው ምትክ መንግሥት ዐዲስ ጳጳስ ሾሞ ነበር።

አንድ ጓደኛችን የስብሰባውን ቦታና ጊዜ ጠቈመን። በዚያ ስንደርስ አሸክረክረው ከነበረው መኪና ዘልዬ ወጣሁ። ነገር ግን ሁሉም ከመውጣቱ በፊት ትክክለኛው ቦታ ላይ የደረስን ስለ መሆናችን እንዳረጋግጥ ሬይ ሐሳብ አቀረበ። ከውጪ በሚታየው ሰው መካከል ዐልፌ ወደ ግቢው ገባሁ። በርግጠኛነት የተነገረን ትልቅ ድንኳን በዚያ ተተክሎ ነበር። ወደ ድንኳኑ ስጠጋ አንድ ወጣት መጣና እጁን ያዘኝ።

«በቀጥጥር ሥር ውለሻል!» በማለት በንቀት ተናገረ። ግራ መጋባቴን ተመልክቶ ንግግሩን ቀጠለ።«ይህ ቤተ ክርስቲያን ሕገ ወጥ እንደ ሆነ የሚያሳየውን ምልክት ከውጪ አልተመለከትሽም? እዚህ ሁልጊዜ ከሚመጡት ሰዎች መካከል አንዷ ነሽ። ኢትዮጵያን ለማዳከም እንደምትሞክሩ ዐውቃለሁ። ይህ ቤተ ክርስቲያን ለሀገሪቱ መጥፎ ነው። ፖለቲካና ሃይማኖት አይቀላቀልም። እግዚአብሔርንና ኢትዮጵያን መወደድ አትችይም።» በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስላናገረኝ በተ መሳሳይ ቋንቋ መለስሁለት። ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን ከዚያ በፊት መጥቼ እንደማላውቅና ያ የመጀመሪያ ጉብኝታችን እንደ ሆነ አስ ረዳሁት።

በዚያን ጊዜ ሬይ ለምን እንዳልተመለስሁ ለማወቅ መጣ። ወደ በሩ እየተጠጋ ሲመጣ፣ ወደ ግቢው ከተጠጋ እርሱንም እንደሚያስሩት አስጠነቀቁት። በመኪናችን ውስጥ ስላሉት ወጣቶች በማሰብ እንዲመለስ ጮተጉትሁት። ሲሄድ የተቈጡት ሰዎች ተከተሉት። ጠብን በመፈለግ የአሜሪካ የስለላ ድርጅት አባላት እንደ ሆንና በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ሀገር ውስጥ እንደ ገባን ተናገሩ። እንሰቅላችኋለን ብለው አስፈራሩን። በዚያ ጊዜ ሁሉም እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያንን በመቃወም ይናገሩ ነበር። በመኪናዎቻችን ውስጥ ያሉትን ወጣቶች

መጽሐፍ ቅዱስ እንፈልጋለን አሏቸው። መጽሐፍ ቅዱሱን እንደሚያጠፉት ዛቱ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰዎች በዙሪያችን ተሰበሰቡ። በኢትዮጵያውያን በተለይ ደግሞ በመኪናዎቻችን ውስጥ ተቀምጠው በሚመለከቷቸው ደኻ ገበሬዎች እንደምንጠቀም ወነጀሉን። የጊዜው የኢትዮጵያ ችግሮች እኛን በመሰሉ የውጪ አገር ዜጎች የተፈጠሩ እንደ ሆነም ተናገሩ። እኔ ላይ እየጮኹ ሳለ አንድ ወጣት በአማርኛ ለሌላ ሰው፣ «ከዚህ በፊት እዚህ መጥቼ አላውቅም የምትል ከሆነ እውነት ነው። እንደነዚህ ዐይነት ክርስቲያኖች በፍጹም አይዋሹም» ሲል ሰማሁት። ሳያውቅ በሰጠው ምስክርነት ተደነቅሁ።

በዚያ ቆሜ ሁኔታውን እግዚአብሔር እንዲቈጣጠር ዐንጥቴን ዝቅ አድርጌ ጸለይሁ። ከያዙኝ ሰዎች መካከል አንዱ ምን እያደረግሁ እንደ ሆነ ጠየቀኝ። «እየጸለይሽ ነው?» በማለት ጠየቀኝ። «ምንም ጥቅም የለውም። እግዚአብሔር የሚባል ነገር የለም።» ለሠላሳ ደቂቃ ዎች እጁን ይዘው እየተሳደቡና ጸያፍ ነገር እየተናገሩ በዚያ አስቆመኝ። ከዚያም መግለጽ በማይቻል ሁኔታ እንድወጣ አዘዘኝ። ሁለት ጊዜ እስኪነገረኝ ድረስ አልጠበቅሁም። ወዲያውኑ ወደ መኪናው ስሄድ ጸሎቴ እንደ ሠራ ለመናገር ልቤ አመነታ፤ ነገር ግን ጊዜው ጥቂት የገለልታ ጊዜ እንደ ነበረ ተሰማኝ። ሐሳባቸውን ከመቀየራቸው በፊት ለማምለጥ ጓጕቼ ነበር። ከተቈጣው ሕዝብ ፊት ለመራቅ ስንንቀሳቀስ ከዐይናቸው እስክንርቅ እየተሳደቡ የመኪናዎችን በር መዝጊያና ኮፈን ይደበድቡ ነበር።

ከእኛ ጋር የነበሩት ወጣቶች ሁሉንም አዩ፤ ተመለከቱም። የተወነጀልንባቸው ነገሮችም እውነት እንዳልሆኑ ያውቁ ነበር። ከዓመት በፊት በሪቻርድ ወርምብራንድ የተጻፈውን «ለክርስቶስ ተሰቃየሁ» በሚል ርእስ የሚታወቀውን መጽሐፍ በአማርኛ ተተርጕሞ ሰጥተናቸው ነበር። አነበቡት ግን ምንም ትርጕም እንዳልሰ ጣቸው ተናገሩ። በተለይ ደግሞ የኮምዩኒዝም ምንነት አልገባቸውምና እንድናስረዳቸው ጠየቁን፤ እኛም የተቻለውን አደረግን። ነገር ግን ሐሳቡን መጨበጥ አልቻሉም። እንግዳ ሐሳብ ነበርና።

እኛ ለወራት አስተምረን ማድረግ ያቃተንን እግዚአብሔር በግማሽ ሰዓት ፈጸመው። ስለ መስከሩት ጕዳይ በአእምሯቸው ምንም ጥርጥር አልነበረም። የወረዳው ሕዝብ ማኅበር ተሰብስቦ በድንኳኑ የሚሰበስበውን ቤት ክርስቲያንና ሕንጻውን ለመውሰድ በጭፍን እንደ ወሰኑ በኋላ ሰማን። በቤተ ክርስቲያኑ ንብረት ምንም ገንዘብ አላወጡበትም፤ እንዲሁ ዝም ብለው ወሰዱት። እንዲህ ዐይነቱን ነገር ማንም ይግባኝ ብሎ የሚቀርብበት ፍርድ ቤት አልነበረም። በዐዲሱ የፖለቲካ ሥርዐት በቤተ ክርስቲያናቸው ድጋሚ እንዲሰበሰቡ አልተፈቀደላቸውም። የሃይማኖት ነጻነት እየጠፋ መምጣት ጀምሮ ነበር።

እሑድ ማለዳ በጠዋት ተነሥተን በአዲስ አበባ ከሚታወቁት የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ ወደ ሆነው በወቅቱ ትልቅ በዓል ወደሚከበርበት ቤተ ክርስቲያን ሄድን። ቅዳሴ እየተቀደሰ ስለ ነበር፣ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ ሰዎች ተሰብስበዋል። መንገዱ በሽተኛነታቸውንና ዐቅመ ደካማነታቸውን በማሳየት በዕለቱ በዓል በሚከበርለት ቅዱስ ስም ምጽዋት በሚለምኑ የኔ ቢጤዎች ተሞልቷል። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ተጠግተን ስንመለከት፣ ብዛት ያላቸው በልዩ ልዩ ጌጥ ያሸበረቁ ጣጉጥላዎች ተራ በተራ ለቤተ ክርስቲያኑ በስጦታነት ወደ ፊት ሲቀርቡ አየን። ጣጉጥላዎቹ ለአይታ ከበቁ በኋላ ወደ ውስጥ ይወሰዳሉ። አስደሳች ነገር ነበር። ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ወደ ፊት ጠጋ ብሎ ሥርዐቱን ለመመልከት ወይም ለመስማት ስለማይቻል ለመሄድ ወሰንን።

ከዚያም ወደ ባፕቲስት ሚሲዮን የጸሎት ቤት ሄድን። እኛ ቦታው ላይ ስንደርስ አባላቱ ስብሰባ ላይ ነበሩ። በኦርቶዶክስ ጓደኞቻችን ላይ እግዚአብሔር የሠራውን ታላቅ ሥራ ሰምተው ነበርና ሞቅ ባለ በክርስቶስ የወንድማማችነት ስሜት ተቀበሏቸው። በሥርዐቱ ላይ የጉባኤው ልዩ እንግዶች በመሆን ከሁሉም ጋር ተዋወቁ፤ የሚያውቋቸው መዝሙሮች ሲዘመሩም በቤታቸው እንዳሉ ተሰማቸው።

በዚያ የነበረው ፕሮግራም እንዳለቀ በመጀመሪያ በሚሰዮናውን ርዳታ የተጀመረ፣ በኋላ ግን ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያውያን ወደ ሆነ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሄድን። እኛ ስንደርስ ሰባኪው መስበክ ከጀመረ ቁየት ብሎአል፤ ይሁን እንጂ ተጋፍተን ገባንና ስብከቱን ለመስማት ተቀመጥን። ምን ያህል እንዳመለጠን አላውቅም፤ ነገር ግን ለአንድ ሰዓት እያደመጥን ቈየን።

ዐርብ ዕለት ማታ ሠላሳ ክርስቲያን ወንድሞች ተይዘው ወህኒ ቤት መታሰራቸውን ሰባኪው ጨምሮ ተናገረ። ቤተ ክርስቲያኑ ሕገ ወጥ እንደ ሆነ ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ አባላት ውስጥ እያመለከ ነበር። ጓደኞቻችን በጣም ደነገጡ። ስለምን ጉዳይ እየተናገረ እንደ ነበር ተረድተዋልና። በቦታው ሆነው በዐይናቸው ሁኔታውን አይተውት ነበር። ስለ ስደቱ ሲናገር የሚሰሙት ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ለእምነታቸው በጽናት እንደሚቆሙ በማሰብ መንፈሳዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ አሳሰባቸው።

ከቡራኬው በኋላ መጭው ጊዜ ልዩ የጸሎትና የጾም ጊዜ እንደ ሆነ ተናገረ። ከሰዓት በኋላ በሚካሄደው መሰተፍ የሚፈልጉ ሁሉ እንዲቈዩ ተጋበዙ። ጓደኞቻችን ግብዣውን ተቀብለው ለመሰተፍ ጓጉ። ወደ አዲስ አበባ የመጡት ለዚህ ዐላማ ነበር፤ ማለት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ለማድረግ፤ ስለዚህ መቈየት ይችሉ እንደ ሆነ

ጠየቁን። ባገኙት ዕድል እነርሱ የተደሰቱትን ያህል እኛም ተደሰተን ነበር።

ከተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጸሎት በኋላ የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች የጌታ እራት እንደሚወሰድ ተናገሩ። በመጀመሪያ ወደ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ጓደኞቻችን መጡና አናገሯቸው። በክርስቶስ እንደ ወንድሞቻቸው እንደ ተቀባሏቸው አረጋገጡላቸው፤ የጌታን እራትም የሚፈልጉ ከሆነ መውሰድ እንደሚችሉ ገለጹላቸው። ምርጫው ሙሉ በሙሉ የእነርሱ ነበር። ጓደኞቻችን ባገኙት ተቀባይነትና ባዩት ኅብረት ተነክተው ነበር፤ ነገር ግን እስከዚያ ጊዜ ድረስ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ናቸውና እንደዚያ ሆነው መቀጠል ፈለጉ። ለቤተ ክርስቲያን አባላት ጓደኞቻቸው ኀላፊነት እንዳለባቸው ተሰማቸው። አንድ የስሕተት ርምጃ ሁሉንም ነገር እንደሚያበላሽ ያውቃሉ። የአህያ ሥጋ በልታችኋል ተብለው መወንጀላቸው ከአእምሮአቸው ገና አልጠፋም። በጉዳይ ላይ ከተነጋገሩበት በኋላ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባላት እስከ ሆኑ ድረስ ሕግጋቱን ለመጠበቅ ተስማሙ።

እንደዚህ ዐይነቱ ወይይት ሲደረግ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አልነበረም። ከዚህ በፊት ቄስ ግርማ የራሳችን ልጆች ሲጠመቁ ከእኛ ጋር ሄዶ ሲመለከት አንድ ጊዜ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከቀያ ዲያቆናት መጥተው በገላ መታጠቢያችን በምስጢር ስለ መጠመቅ ሊጠይቁ ሲመጡ። ሁለት ጊዜ ስለ ጥምቀት ተወያይተን ነበር። በጉዳዩ ላይ ለረጅም ጊዜ ተወያይተንበታል። አንድን ነገር በምስጢር መሥራት ማለት ማን ምስጢሩን ማወቅ እንዳለበት የመወሰንን ኀላፊነት መውሰድ ማለት ነበር። አንድ ደካማ ሰው ወይም ሰላይ ሁሉንም ነገር ሊያበላሸው ይችላል። የአዲስ አበባ ክርስቲያኖች ያጋጠማቸው ይህ ነበር። በመካከላቸው ባሉ አበላት ብዙ ጊዜ ተታለዋል።

ክርስቲያን ታዛዥ እንዲሆን ጥምቀት አስፈላጊና መሠረታዊ ነገር እንደ ሆነ እናምን ነበር። ሕፃናት ሆነው በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ተጠምቀው ነበር፤ ነገር ግን እምነታቸውን በክርስቶስ ሲያደርጉ በሕይወታቸው ካገኙት ለውጥ በኋላ በድጋሚ አልተጠመቁም።

አንገብጋቢው ጥያቄ ምእመናኑ ተጠምቀውና ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥለው በመንዝ ዐዲስ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ዝግጁ ናቸው? ወይስ ለጊዜውም ቢሆን በቤተ ክርስቲያናቸው ቈይተው ከውስጥ ሆነው ለዐዲስ ሕይወትና ለመነቃቃት መሥራት ይፈልጋሉ? የሚለው ነበር። ጉዳዩን በዚያ መንገድ ሲመለከቱት አሁንም ትክክለኛ ቦታቸው በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ያለ እንደ ሆነ አመኑ። ኢየሱስን በእውነተኛ መንገድ ብዙ ሰዎች እያወቁ ሲመጡ በባህልና በእምነት ላይ መጠነኛ ለውጥ እንደሚመጣ ከወዲሁ ገምተዋል። ከተሳሳቱ ዳግሞ አሁንም ቤተ ክርስቲያንን ለቆ የመውጣት ምርጫ ነበራቸው።

እነዚህም ጌታን እያመለኩና እየጸሙ ሳሉ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ «በርናባስንና ሳውልን እኔ ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ» አለ። እነርሱም ከጸሙና ከጸለዩ በኋላ እጃቸውን ጭነው አሰናበቷቸው።

የሐዋርያት ሥራ 13÷2-3

«ይህን ካለ በኋላ፣ ተንበርክኮ ከሁሉ ጋር ጸለየ። ሁሉም እጅግ አለቀሱ፣ ጳውሎስንም ዐንገቱን ዐቅፈው ሳሙት፣ ከሁሉም በላይ ልባቸውን የነካው፣ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቱን እንደማያዩ የተናገራቸው ቃል ነበር። ከዚያም እስከ መርከቡ ድረስ ሸኙት።»

የሐዋርያት ሥራ 20÷36-38

ለአገልግሎት መለየት

በፀደዩ ወራት በሙሉ የሚፈጸመው መጪው የዓመት ፈቃዳችን መቃረብ ያስጨንቀን ነበር። እኛ ስንሄድ ምን ይፈጠር ይሆን? እኛን የሚተካ ሰው ይኖር ይሆን? ዐዲሶቹ አማኞች ራሳቸውን ችለው መስብሰብ ይቀጥሉ ይሆን? ለሁለት ዓመት ተኩል ያህል ዐዲስ ክርስቲያን አልተጨመረም። ዐጭር ጊዜ ሰለ ሆነ ገና ሊያውቁት የሚያስፈልግ ብዙ ነገር ይቀር ነበር። ሁልጊዜ በተወያየን ቍጥር ምንም ዐይነት መፍትሔ ላይ አንደርስም። በግንቦት ወር በሚካሄደው የመጨረሻ ትልቅ ስብሰባችን ላይ ጌታ በሆነ መንገድ ነገሩን ይፈታዋል በሚል ተስፋ ላይ ተደግፈን ቆምን።

በዚህ ጊዜ ምእመናኑ በቀያ ለመሰብሰብ ፈለጉ። ድንኳኑ የመሰብሰቢያ ክፍል በመሆን እንዲያገለግል ተደረገ፤ እንግዶችንም በቤታቸው እንዲተኙ ፈቀዱላቸው። ከሚወዷቸው ሰባኪዎች መካከል አንዱ የሆነው ተስፋዬ ወርቅነህንና ጆን ኬይን በድጋሚ ጋበዝን። መኮና ሙሽራት ሚስቱ ዐብረው በመሄድ የአስተማሪዎችን ቡድን የተሟላ አደረጉት።

በመጀመሪያ ትንሽ ሰው በመምጣቱ ዐዝነን ነበር። ሰማንያ ሰው ብቻ መጣ። ዐዲስ ተማሪዎችም እንደሚመጡ ተስፋ አድርገን ነበር። ነገር ግን ማን መምጣት እንዳለበት እስክ መምረጥ ድረስ እግዚአብሔር እንደሚወስንና እንደሚቈጣጠር ርግጠኞች ሆንን።

አየናቸው ከውኃይ በረጅሙ መንገድ ለመራመድ ከዚያ በኋላ ባላስቸገረው እግሩ ተጉዞ መጣ። ከግሮስ ቤት በስተጀርባ ካለው ማኅበራዊ መገለል ከደረሰባቸው ሰዎች ግቢ ዘመዱ የሆነውን ምንይሉን ይዞ ነበር የመጣው። ምንይሉ በወልደ ጻድቅ ጕትጕታ ነበር

ስለዚህ በዚያ ቀን በጌታ እራት ላይ አልተሳተፉም። ነገር ግን ሥርዐተ አምልኮውን ተመለከቱ፤ አመለኩም። የሥርዐቱን ውበትና ግልጽነት በአንክሮ ተመለከቱ። ካህናት ብቻ የሚፈጽሙት ምስጢራዊ ሥርዐት በዚያ አልነበረም። ሁሉም እንዲያየው በግልጽ ነበር የተደረገው። በተጨማሪም ሥርዐቱ በመንዝ ጎጢአት እንደሌለባቸው ለሚቈጠሩ ለሕፃናት ወይም ለአዛውንት ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ጸሎት ከተደረገና ልባዊ ንስሓ ከተገባ በኋላ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል በሥርዐቱ ተሳተፈ።

ከዚያ ሥርዐት በኋላ ጓደኞቻችን በዐዲስ ራእይ ወደ መንዝ ተመልሰው ሄዱ። በኢየሱስ ፍቅር የተሳሰረ የዓለም ዐቀፍ ቤተ ሰብ አባል እንደ ሆኑ ተረዱ። አዲስ አበባ እያሉ በሚቻለው መንገድና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወንጌልን የማካፈል ፍላጎትን እግዚአብሔር በውስጣቸው አስቀመጠ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን መማር የጀመረው፤ ብዙም ሳይቈይ ክርስቶስን ተቀበለ። ወዲያውኑም የቤተ ሰብ የጸሎት ፕሮግራምንና በግቢውም ሌሎችን ማስተማር ጀመረ።

አየናቸውንና ምንይሉን በዚያ የተሰበሰቡት አባላት ሞቅ ባለ ሁኔታ ተቀበሏቸው። የምግብ ሰዓት ሲደርስ ያለ ምንም ጥያቄ ከሌሎች ጋር ተቀላቀሉ። ምሽት ላይ ሁሉም ወደ ቤታቸው ላለመሄድ ወሰኑ። ድንኳኑ ውስጥ ሙቀት ለማግኘት መሬት ላይ ተጠጋግተው ተኙ። ማኅበራዊ መገለል ሲደርስባቸው የነበሩት ሰዎች በዚህ ዐይነት ተገቢ ተቀባይነት ያላቸው የቡድን አካል ለመሆን በቁ።

ይህ ስብሰባ ቀድሞ ከተካሄዱት በሌሎች መንገዶች ይለይ ነበር። ስብሰባውን በብዛት የመሩት ተገልለው የነበሩት እነዚህ ሰዎች ነበሩ። መዝሙሩን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን ፈልጎ የማግኘት ውድድሩንና የጸሎቱን ጊዜ ተራ በተራ ይመሩ ነበር። ብዙዎቹ ሰበኩ፤ በእያንዳንዱ ምሽትም በሕይወታቸው ጌታ የሠራውን ሥራና የግል ምስክርነት ተናገሩ። በሁለተኛው ምሽት እስከዚያ ጊዜ ድረስ ጌታን ያልተቀበሉ ብዙዎች እምነታቸውን በክርስቶስ አደረጉ። ብዙዎቹ ከድግምግሚ የመጡ ነበሩ። እናስተምራቸው የነበሩት ተማሪዎች በሙሉ ባይመጡም፤ የመጡት የጌታን ምሪት በተክክል ለመከተል ዝግጁ ነበሩ።

በተጨማሪም ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቶች ወደዚህ ስብሰባ መጡ። እነዚህ ሴቶች በጸደይ ወራት በሙሉ ትምህርት ሲከታተሉ ነበር። ምንም እንኳ ዐይን አፋር ቢሆኑም፣ ብዙዎቹ እግዚአብሔር ለልባቸው እየተናገረ እንደ ሆነ ቆመው ለመናገር ድፍረት አገኙ። ጥቂቶቹ እንዲያውም ፈተና ዐልፈው መጽሐፍ ቅዱስ ለመሸለም በቁ። በተጨማሪም እግዚአብሔር እኛ ባስተማርናቸው ወጣት ወንዶች በመጠቀም ለሴቶች በር እየከፈተ ነበር።

በጦርነት ላይ እንዳለንና ጠላታችንም ሰዎች ወይም ተቋሞች ላይሆኑ ሰይጣን እንደ ሆነ ዘንግተነው እናወቅም። ዐሥራ አራት ዓመት ገደማ የሚሆነው አንድ ትንሽ ልጅ ወደ ስብሰባው መጣ። ከዚህ በፊት እርሱን አይተነው እናውቅም። ወደፊት ቀጥታ ሄደና ከተናጋሪው አጠገብ ቆመ። ከዚያም ወደሚያዳምጡት ሰዎች ፊቱን አዞረ። የሚርገበገቡ በሚመስሉ ዐይኖቹ በጥርጣሬና በፍርሀት ወዲያና ወዲህ ይማትር ነበር። ዐይናቹን ከተቀመጡት ሰዎች ላይ ላይነቅል ያለ ዕረፍት ተንጐራደደ።

ስንጸልይ ማጒረምረም ጀመረ፤ እንዲያውም በጩኸት መናገር ቀጠለ። የሚናገራቸው ነገሮች ያልተለመዱና የማይገናኙ ነበሩ። በስብሰባው የነበሩ ጥቂቶች ማንነቱን ያውቁ ነበር። ምንም ቤት እንደ ሌለውና ያለ ምንም መጠለያ ባዶ ሜዳ ላይ እንደሚተኛ ነገሩን። ጋኔን

እንዳለበት ይናገር ነበር። ስናናግረው ያልተለመደ ባሕርይ እንዳለው ተረጋገጠ፤ ይሁን እንጂ ምንም ማድረግ እንደማይችል ተናገረ። የሚቈጣጠረው ጎይል እንዳለ ይታይ ነበር። ስለ ኢየሱስ ወይም ስለ ሰይጣን ባወራን ቊጥር ርእሱን ይቀይራል።

ሰኞ ዕለት የስብሰባው የመጨረሻ ቀን ነበር። ለጉብኝትን ዝግጅት ጌታ በተለየ መልክ አንድ ነገር እንደሚያደርግ አሁንም ይሰማን ነበር። በመጨረሻው ምሽት የጸሎቱንና የምስክርነቱን ጊዜ በጉጉት ጠበቅን። ባለፈው ምሽት ለነበረን ፕሮግራም ጥሩ ምላሽ ነበር። ሲጨልም አንድ ዲያቆን የመናገር ዕድል ይሰጠው ዘንድ ጠየቀ። በረባሽነቱና በቤተ ክርስቲያኑ ለታላላቆቹና ለወላጆቹ ባለመታዘዝ ጎጢአተኛ እንደ ሆነ ጌታ እንደ ተናገረው በመግለጽ ጀመረ። እየተናገረ ሳለ የብዙዎችን ልብ እየነካ እንደ ነበር ግልጽ ሆነ።

ልክ በዚያን ጊዜ ከውጪ አንድ የሚሰቀጥጥ ድምፅ ተሰማ። የአደጋ ጩኸት ነው የተጮኸው። ድንኳኑ ካሉት አብዛኞቹ በድንኳኑ መጨረሻ ላይ ባለው ጠባብ መውጫ እንደ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ ዘለው ወጡ። ሮጠው ሲወጡ ክፍሉ በአቧራ ተሞላ።

ልባችን በፍርሀት ተሞላ። ችግሩ ምን ይሆን? ጥቂት ሰዎች ነበሩ ድንኳኑ ውስጥ የቀሩትና ጥያቄያችንን ለመመለስ አልቻሉም። ሁልጊዜ ይንጐራደድ የነበረው ልጅ በብርድ ልብስ ተሸፍኖ ተኝቶ በአጠገባችን አልነበረም። ሥርዐቱ ከመጀመሩ በፊት ተጠቅልሎ ተኝቶ ነበርና እንደዚያ እንዳለ ትተነዋል። በዚያ ጊዜ እያስቸገረን አልነበረም። ነገር ግን ብዙ ሳይቈይ በእንቅልፍ ልቡ ማውራት ጀመረ። ሁሉም በእንደዚያ ዐይነት ጥድፊያ ሲወጣ እርሱን መቀስቀስ እንዳለብን ዐሰብን።

ለረጅም ጊዜ ጠበቅን። መጨረሻ ላይም ሰዎች እየተንጠባጠቡ መጡ። ከመካከላቸው አንዱ አንድ ሴትዬ በሬዋ እንደ ጠፋባትና ከመምሸቱ በፊት ፈልጋ ለማግኘት ባለመቻሏ እንደ ተጨነቀች ነገረን። በሬው ተሰርቆ ወይም በትልቁ የግጦሽ ስፍራ እንደ ተሰማራ ጠፍቶ ይሆናል። ሁለት ወንድ ልጆቿ በስብሰባው ላይ ስለ ነበሩ በጭንቀት ለርዳታ ጩኸት ማሰማቷ ነበር። የቀሩት ሰዎችም ምን እየተካሄደ እንደ ሆነ ለማየት ሄዱ። በሬውን ገና አላገኙትም ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በፊት ይሰማን የነበረው የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ሙሉ በሙሉ ጠፋ። በዚያ ያልተረጋጋ ስሜት ሰዎቹ የጌታን ድምፅ እንዲሰሙ አልጠበቅንም። መጸለይ አስፈለገን። ጭንቅላታችንን ዝቅ አድርገን በጌታ በኢየሱስ ደም የተሸፈንን እንደ መሆናችን፣ ጠላት ሰይጣንን በመቃወም በዚያ ድንኳን የመገኘት መብት እንደሌለው በድፍረት ነገርነው። በልባችን የእግዚአብሔርን ሰላም እንድናገኝ አጥብቀን ጸለይን።

ወድያውኑ በብርድ ልብስ ተሸፍኖ የነበረው ልጅ የጉርምርምታ ድምፁን እየጨመረ ሄደ። ከሚናገራቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ፀረ ሃይማኖትና ከሥነ ሥርዐት ውጭ የሆኑ ነበሩ። የሚናገረው በጣም በዛ። መቀስቀስ እንደሚኖርብን ወሰንን። ብርድ ልቡሱን ከጭንቅላቱ ላይ ስናነሣው ያገኘነው የተኛ ሰው ሳይሆን ዐይኑን እያፈጠጠ ያለ ንቁ ሰው ነበር። ወዲያውኑ ጸለይንለትና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸጥ ብሎ ቁጭ አለ።

እየጸለይን ሳለ አንድ በአንድ ተማሪዎቹ ተመልሰው መጡ። ከአንድ ሰዓት በኃላ ሁሉም ተጠቃለው ተመለሱ። እንደገናም የእግዚአብሔር መገኘት ተሰማን። የሚገርመው በሬው ከሴትዮዋ ግቢ አልወጣም ነበር፤ ነገር ግን እንዲሁ ዐጥሩን ዘሎ በግቢው ሌላ ክፍል ተገኘ። የዚህን ዝርዝር ጉዳይ መጥቀስ ምንም አያደርግም። ይህ ከሰይጣን ስልቶች ውስጥ አንዱ እንደ ሆነ አስተዋልን፤ ይሁን እንጂ ተንኰሉን ስለምናውቅና በኢየሱስ ስም ስለ ተቃወምነው አልተሳካለትም ነበር።

ሌሊቱን በሙሉ ብዙ ሰዎች በሕይወታቸው ጌታ የሠራውን ሥራ መሰከሩ ወይም ኀጢአታቸውን ተናዘው የኢየሱስን አዳኝነት አምነው ተቀበሉት። ከዚያም እኩለ ሌሊት አካባቢ አስቻለው መናገር የሚፈልገው ነገር እንዳለ ነገረን። ሰዎች ሁሉ በደንብ የሚያውቁትን ማለት ምን ያህል አስቸጋሪና ጨካኝ እንደ ነበር አንድም ሳይቀር ዘክዝከ ገለጸ። ነገር ግን ያ ሁሉ ኢየሱስን ገና ከማወቁ በፊት የሆነ ነበር።

«አሁን በእግዚአብሔር ርዳታ ተለውጫለሁ» በማለት ተናገረ። «ስካር ለእኔ ከዐቅሜ በላይ የሆነ ችግር ነበር። አሁን ግን በአጠቃላይ መጠጣት በማቆም ችግሬን አስወግጀዋለሁ። ከሽመና ሥራ የማገኘውን ትርፍ እንዴት አጠፋ እንደ ነበር አይታችኋል። ሕይወቴን ለኢየሱስ ከማስረከቤ በፊት ለዓለማዊ ነገሮች እንደምጨነቀው አሁን አያሳስበኝም። ሴትና ዝሙትም ብዙ ችግሮች አስከትለውብኛል። ነገር ግን እግዚአብሔር ከዚያ ችግር ውስጥ አውጥቶኛል። ለወንጌል የእኔ ባሕርይ ዕንቅፋት ሲሆን በጣም ዐዝናለሁ፤ ምክንያቱም በሕይወቴ በጣም እፈልገው የነበረ ጉዳይ ሰዎች ኢየሱስን እንዳያውቁት ማድረግ ስለ ሆነ ነው።»

«እንደሚመስለኝ እግዚአብሔር እንደ ጳውሎስ አስተማሪ እንድሆንና ትዳር እንዳልይዝ ይፈልጋል» በማለት ምስክርነቱን ቀጠለ። «ያ ደግሞ ለእኔ ችግር የለውም። ልጆች በጣም እወዳለሁ፤ የራሴ ልጆች ቢኖሩኝም አልጠላም ነገር ግን ከሁሉ በበለጠ የእርሱን ፈቃድ መፈጸም እፈልጋለሁ። ያንን ካደረግሁ ደስተኛ እንደሚያደርገኝ ዐውቃለሁ። ከእናንተ ጋር ልካፈለው የምፈልገው ዕቅድ አለኝ። ከመንዝ የሁለት ቀን የእግር መንገድ በሚርቀው በጀማ የዲቁና ትምህርት ለዐምስት ዓመት ተምሬ ነበር። ከልምዴ እንደ ተረዳሁት

በዚያ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቅ ሰው የለም። እነዚያን ሰዎች ከአእምሮዬ ማውጣት አልቻልሁም። ከሽመና በማገኘው ትርፍ አህያ ገዝቼ መጽሐፍ ቅዱስ እየወሰድኩላቸው ስለ ኢየሱስ ላስተምራቸው ወሰኛለሁ። አንድ ጥያቄ ብቻ አለኝ። ስለዚህ ምን ታስባላችሁ? ትክክለኛውን ነገር እያደረግሁ እንደ ሆነ ትስማማላችሁ ወይስ ይህ የግሌ ሐሳብ ብቻ ነው? ወደዚያ ቦታ ስሔድ በራሴ ነው የምሄደው ወይስ እናንተን ወክዬ?»

ለጥያቄዎቹ መልስ ከመሰጠቱ በፊት ጎይለ ጊዩርጊስ ዘሎ ቆመ። ወደያውኑም፣ «ለዐምስት ዓመት በመንዝ የዲቁና ትምህርት ስማር ወደ ቦረና የምመለስበትን ቀን በተስፋ ስጠብቅ ነበር። መጨረሻ ላይ የምሄድበት ጊዜ ሲደርስ፣ ያለተለመደ ነገርን አስተዋልሁ። መሄድ አልፈልግም። ይህንን ቦታ ወድጀዋለሁ። በዚህ ቦታ ክርስቲያን ወንድሞችን አግኝቻለሁ፤ ልቤም ያለው እዚህ ነው» በማለት ተናገረ።

በመቀጠልም፣ «መጀመሪያ ላይ የሚሰዮናውያን የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ስሆን፣ በውድድሩ አሸናፊ ሆኜ በተሸለምሁት መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ኮርቼ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሱን ሁሉም ሰው እንዲያየው በትከሻዬ ይዤ እንዞራደድ ነበር። አሁን በውስጡ ያለውን ማወቅ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ማግኘትና መሸከም ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ። እዚህ መቄዶኒያ እፈልጋለሁ። ነገር ግን የተማርሁትን በሙሉ ተመልሼ ለቤተ ሰቤና ለጓደኞቼ ማካፈል እንዳለብኝ እግዚአብሔር እየጠራኝ እንደ ሆነ ይሰማኛል። ካልሄድሁ እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ? እዚህ ካገኘነው ጥቂቱን ወስጀ በዚያ ባካፍላቸው ትጸልዩኛላችሁ?» አለ።

ከዚያ ደግሞ ግርማ እጁን አወጣና፣ «እግዚአብሔር እዚህ የሚፈልገኝ ይመስለኛል። ለረጅም ጊዜ ሰባኪ እንድሆን የሚፈልግ እንደ ሆነ ይሰማኛል። ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ነገር ለእናንተም ገልጾላችሁ እንደ ሆነ ማወቅ እፈልጋለሁ። ትስማማላችሁ? ደግሞም ሚስዮናውያኑ ከመሄዳቸው በፊት እንዲጸልዩልኝ እፈልጋለሁ» በማለት ተናገረ።

መጨረሻ ላይ ለረጅም ጊዜ እንዲያደርገው የምንፈልገውን ነገር ጌታ እያደረገው ነበር። እንዴት ሊያደርገው እንደሚችል ግን አናውቅም። ለአገልግሎት የመረጣቸውን እየለያቸው ነበር። በዚህ ረገድ ጌታ የተናገረው ሌላ ሰው እንዳለ ጠየቅን።

ቀጥሎ ታጠቅ ለመናገር ተነሣ። ለብዙ ወራት ስለ ወደፊቱ ያስብ ነበር። «ከረጅም ጊዜ በፊት ጌታ ብርሃኑን ለአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሰጠ አምናለሁ። ብርሃኑንም እንዲወጣ አድርገውታል። እንደማስበው ያንን ብርሃን እንደገና ማቀጣጠል የእኛ ሥራ ነው። ጌታ እኔንም ሰባኪ እንድሆን የሚፈልግ ይመስለኛል አለ።»

እግዚአብሔር ቸር ነው። አራት ሰዎችን ለአገልግሎት ጠርቶ ነበር፤ ሁለት ተወላጅ ሚስዮናውያንን ሁለት መጋብያንን። ስለዚህ በዚያ ጉዳይ ላይ ሙሉ የመሆን ስሜት ተሰማን። ሀላችንም ተነጋገርንበት፤ ጸለይንበትም። ሁሉም ደግሞ በጉዳዩ ላይ ተስማምተው ነበር። እግዚአብሔር እነዚህን አራት ሰዎች ለልዩ ዐላማ እንደ መረጣቸው አስተዋሉ።

ቀጥሎ የተጠየቀው ጥያቄ ሊያከናውኑት ስላለው ተግባር ሥልጣኑን ከየት ያገኛሉ? የሚለው ነበር። እስከዚያ ጊዜ ድረስ የሚያውቁት የሥልጣን ምንጭ ጳጳስ ብቻ ነበር። በድጋሚ መመሪያችን የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን ተመለከትን። በርናባስና ጳውሎስ ለአገልግሎት ሲመረጡ፤ የቡድናቸው አባላት ጸልየውና ጾመው፤ እጃቸውንም ጭነውባቸው ባርከዋቸው ነበር። ስለሆነም ያ ቡድን የጎበረት ጳጳስ በመሆን ያንን ተግባር እንደ ፈጸመ ሁሉም ድምዳሜ ላይ ደረሱ።

በቀጣዩ ቀን ጠዋት ላይ በድንኳኑ የመጨረሻውን አገልግሎት ፈጸምን። አራቱም ሰዎች የግል ምስክርነታቸውን ከሰጡ በኋላ ጆን ካይን የምናደርገውን እውነትነት የሚያረጋግጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማንበብ እያንዳንዳቸውን በዘይት ቀባቸው። እነርሱም ልክ በቆረኑ መሬት ላይ ብርድ ልብሳቸውን ተሸፍነው ተንበረከኩ። ይህንን ግልጽ ጎላፊነት መቀበል ይችላሉ ብለው ያመኑ አማኞች ወደ እነርሱ ተጠግተው እጃቸውን እየጫኑ አለዩላቸው። በዚያ ጠዋት ከዚያ የተሻለ ቀላል ሥርዐት ሊኖር አይችልም ነበር ነገር ግን ያን የመሰለ የሚያምር ሥርዐት ድጋሚ ማየታችን አጠራጥሮኛል።

ድንኳኑን ከማፍረሳችን በፊት እያንዳንዳቸውን ለመሰናበት ጊዜ ወሰድን። ከነበረው አሳሳቢ የፖለቲካ ሁኔታ የተነሣ ከዓመት ፈቃዳችን በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ልንመለስ እንደማንችል አስተዋልን። ምናልባትም ለመጨረሻ ጊዜ ይሆናል የምንሰነባበታቸው። ያ ሁኔታ ዕጥፍ ከባድ አደረገው። በኢትዮጵያውያን ባህላዊ ስንብት ማለት ጉንጭ ሰጉንጭ በመሳሳም አንድ በአንድ ተሰነባበትናቸው። ካደረግናቸው ነገሮች መካከል አንዱና እጅግ ከባዱ ይህ ነበር፤ ልባችን እንደ ትልቅ ዳቦ እንደ ሆነና አንድ በአንድ እየቈረስነው እንደ ሆነ ተሰማን።

ከመሄዳችን በፊት ከመካከላቸው አንዱ፤ «ወደ አሜሪካ ስትሄዱ ልክ ለእኛ እንደ ነገራችሁን ስለ ኢየሱስ ንገሯቸው» በማለት በአንክሮ አሳሰበን። በእነዚህ ጥቂት አማኞች በአገራችን ሚስዮናውያን እንድንሆን እንደ ታዘዝን ተሰማን። መጨረሻ ላይ ዕቃችንን ጭነን ወደ ቤት ለመሄድ ቻልን። በመንገዝ ለመቈየት የቀረን ሁለት ቀን ብቻ ነበርና ጓዛችን ሁሉ መጫን ነበረበት።

በዚያ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ወልደ ጻድቅ መኖሪያ ቤት ለመጨረሻ ጊዜ ሄድን። ከሆስፒታል በሁለት እግሮች በደኅና ወደ ቤቱ ተመልሶ ነበር። በዐዲሱ እግሩ ተደስቶአል። ከመሰነባበታችን በፊት

ቁጭ ብለን አንድ ላይ ጸለይን። ባለፉት ጥቂት ወራት እንደ ነበሩት ሁሉ ያን ጊዜም አባቱ ነበሩ። መሐል ሜዳ አቅራቢያ የዘበኝነት ሥራቸውን ለመሥራት ከሄዱ ዓመታት ዐልፈዋል። ስንመጣ ለወልደ ጻድቅና በእጅ ሥራ ትምህርት ባደረግነው ሁሉ ተደስተው ነበር። ነገር ግን ፊልም ስናሳይና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች እርሳቸው ተገኝተው አያውቁም ነበር ስለዚህ የትኛውንም ዐይነት መንፈሳዊ ነገር በትክክል ይረዳሉ ብለን አልጠበቅንም።

ከጥቂት ጸሎት በኋላ የሽማግሌ ድምፅ በመካከል ገብቶ ሲሰማ ተገረምን። እርሳቸው መሆን ነበረባቸው። ወንድሞቹ እንደዚያ ዐይነት ድምፅ አልነበራቸውም። እግዚአብሔርን ሲያነጋግሩ አዳመጥናቸው። እንደዚህ እያሉ «ጌታ ሆይ ይህ ቤት ምን ዐይነት እንደ ነበር ታውቃለች። ሁልጊዜ ጥል የነገሠበት መጥፎ ስፍራ ነበር። ሁሉም ሰው ጠንቋዩን በመፍራት በሥጋት የሚኖርበት በጨለማ የተሞላ ስፍራ ነበር። ነገር ግን አሁን ነገሮች እንደ ተሰወጡ እመለከታለሁ። ከዚህ በፊት የማላውቀው ደስታና ሐሤት አለ። አዚህ ስሆን ጥሩ ስሜት ይሰማኛል። እነርሱ እንደ ሆኑት እንድሆን ኢየሱስን ከልቤ እፈልገዋለሁ።» ይህን ስንሰማ፤ የምንፈነዳ እስኪመስለን ድረስ ጌታ ሙሉ አደረገን። ጽዋዎቻችን በርግጥ ተትረፍርፈው ሞልተው ነበር።

ረቡዕ ዕለት ዕቃችንን ጭነን ጨረስን። ጨለም ሲል ኮኖ ዐሥራ ዐምስት ጓደኞቻችን እኛ ዘንድ ሊያድሩ ሲመጡ ሥራችንን አልጨረስንም ነበር። ድጋሚ ከእኛ ጋር መሰነባበት አንዳሰባቸው ተሰማቸው። ከአንድ ቀን በፊት ከስብሰባው በኋላ የነበረን ጥቂት ጊዜ በቂ አልነበረም። ስለዚህ በመንዝ የመጨረሻውን ምሽት አንድ ላይ በጎበረት በማምሸክ አሳለፍን። ከእነዚህ ወጣት ወንዶች ጋር እንደ ራሳችን ቤተ ሰብ ያህል ተቀራርበን ነበርና ስንለያይ በጣም እንደሚናፍቁን እናውቅ ነበር።

ኀሙስ ቀን በጤና ጣቢያ ሥራና የገበያ ቀን ነበር። በዚያ ቀን የተለመደው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነበረን። መጨረሻ ላይም ከሰዓት በኋላ ቄየት ብለን መንዝን ለቀን ሄድን። በዚያ ቀን በሕይወታችን አንድ ምዕራፍ ተዘጋ፤ ነገር ግን ፈጽሞ እንደማንረሳው እናውቅ ነበር። እግዚአብሔር ልክ በዚያን ጊዜ በዚያ ቦታ እንድንገኝ ስለ ፈቀደልን በጣም አመሰገንነው። እግዚአብሔር በአስደናቂ መንገድ ሲሠራ ከሥረ መሠረቱ በመመልከታችን፣ ራሳችንን ዕድለኞች አድርገን ቈጠርን። ያንን ሁሉ በመመልከትም ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ እንደዚያ እንደማንሆን ተረዳን።

እዚያም በደረሱ ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያንን በአንድነት ሰብስበው፣ እግዘአብሔር በእነርሱ አማካይነት ያደረገውን ሁሉ፣ ደግሞም ለአሕዛብ እንዴት የእምነትን በር እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ። በዚያም ከደቀ መዛሙርት ጋር ብዙ ጊዜ ተ ቀመጡ።

የሐዋርያት ሥራ 14÷27-28

መደምደሚያ

እ.ኤ.አ.ሰኔ 1976 ላይ ኢትዮጵያን ተሰናበትናት። ምንም እንኳ ለመሄድ ፈቃደኞች ባንሆንም፣ የዓመት ፈቃድ ያስፈልገን ነበር። ከልጆቻችን ጋር እንደገና እንደ ቤተ ሰብ የመኖር ዕደል ተሰጠን። በተጨማሪም በእምነት ሲደግፉንና ሲጸልዩልን ለነበሩት በአሜሪካ ለሚገኙት በኢትዮጵያ ጌታ የሠራውን ድንቅ ሥራ ለማካፈልም ጓጉተናል።

ጊዜው ሲደርስ ለመመለስ እየተመኘን ዓመት ሙሉ ስለ ኢትዮጵያ የሚወራውን ዜና በጥንቃቄ እንከታተል ነበር። የአውሮፕላን ቲኬት እስከ መቁረጥ ደረስን። ከዚያም ከአሜሪካ ለመውጣት ሁለት ሳምንት ሲቀረን እንድንቄይ ተጠየቅን። ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ማለት በሰኔ 1969 የእኛ ሚስዮናውያን በሙሉ ከኢትዮጵያ ወጡ።

ከዛያ ዐምስት ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ. እስከ የካቲት ወር 2003 ድረስ ወደ መንዝ አልተመለስንም። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር በሠራው ነገር ስንበረታታና ስንደነቅ ነበር። መጠነኛ ቊጥር ያላቸውን ዐዲስ አማኞች ነበር ትተን የሄድነው። ስንመለስ ብዙ የዐዲስ ኪዳን ምእመናንን በሸዋ ክፈለ ሀገር በአማራ ከፍተኛ ስፍራዎች ላይ አገኘን። በሄድንበት ሁሉ ከብዙ ዓመት በፊት ዘር በመዝራታችን የሚያመሰግኑን ሰዎችን እናገኝ ነበር። በእውነቱ አዝመራው ለመገመት ካሰብነው በላይ ነበር።

ከሄድን በኋላ ለስድስት ዓመት ዐዲሶቹ አማኞች በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሆነው ስለ ዐዲሱ እምነታቸው ይመሰክሩ ነበር።

የማርክሲስት ኮምዩኒስት መንግሥት ሥልጣን ላይ የነበረበት ጊዜ ስለ ሆነ ብዙ መከራ ደረሰባቸው። በተጨማሪም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ትልቅ ስደት አጋጥሟቸዋል። ከብዙ ጸሎትና ንስሓ በኋላ መጨረሻ ላይ የራሳቸውን የዐዲስ ምእመናን ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ። የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በዚህ ሁኔታ ጥለው ከወጡ ሌሎች አማኞች ጋር በመሆን ለቤተ ክርስቲያናቸው «አዲስ ኪዳን» የሚል ስያሜ ሰጥተው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ። ይህ ስያሜ ጌታ ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ሕገጋት ይልቅ የአዲስ ኪዳን አዳኝ እንደ ሆነ ያላቸውን እምነት በጥሩ ሁኔታ እንደሚገልጸው ተሰማቸው።

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ1984 በድርቅ በተመታች ጊዜ፣ የባፕቲስት ሚስዮን በአማራ ተራራማ የገጠር ቦታዎች ምግብ እንዲሰጡ የድርቅ ርዳታ ቡድኖችን ላከ። ከዚያም በቀጠናዎቹ የልማት ቡድኖችን አከታትሎ አሰማራ። ክርስቲያን ሠራተኞች እምነታቸውን ከእነርሱ ጋር አንድ አደረጉ። ከዚህም የተነሣ የዐዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት በየሜዳቡበት ሁሉ ተመሠረቱ። ዛሬ በቡልጋ፣ በመርሐ ቤቴ፣ በግሼ ራቤል፣ በመራኛ፣ በደንሴ፣ በሸል አፋፍ፣ በጉንዶ መስቀል፣ በሞላሌ፣ በዘመሮ፣ በጊና ገር፣ በዓለም ከተማ፣ በሾላ ገበያ፣ በምንጃር አራርቲና በሌሎችም ቦታዎች አማኞች ይገኛሉ።

ሰዎች ከዚህ በፊት በኋላ ቀር መንዜዎች ይሥቁ ነበር። ዛሬ የመንዝ አማኞች የልማትን ተግባር በመንግሥትና በወርልድ ቪዥን ድጋፍ ተያይዘውት ይታያሉ። የቀያ አካባቢ ሰዎች ወደ አድባርና ወደ ጠንቋይ መሄድ ስላቆሙ ያ ስፍራ የወንጌል ስፍራ ተብሏል። ሴቶች ዛር የለባቸውም፤ ቦረንቲቻንም መሥዋዕት አያቀርቡም። አሁን በመንዝ ብዙ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ብዙ አማኝ ልጆችም በዘመናዊ ትምህርት ቤት ብል ኖችና ውጤታማ ከመሆናቸው የተነሣ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ገብተው በመማር ለኢትዮጵያ አገራቸው በብዙ መንገዶች አስፈላጊውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። የተወሰኑት እንዲያውም እምነታቸውን በአውሮፓና በአሜሪካ ለማካፈል ከኢትዮጵያ ውጭ ሄደዋል። የመንዝ ሰዎች በርግጥ ከጨለማ ወደ ብርሃን መጥተዋል።

ደብዳቤዎች

የካቲት 10 ቀን 1969

ለሳማችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ይድረሳችሁ። በክርስቶስ አስተማሪዎቻችን፣ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የሆናችሁ ሊንድሆልም፣ ጆን፣ ጆሲና ስቴፈን።

ከተለያየንበት ቀን ጀምሮ እንደምን ናችሁ? ከእናንተ ሐሳብና ናፍቆት በስተቀር አምላካችን፣ አዳኛችንና ጌታችን ይክበር ይመስገን እኛ ደኅና ነን። ነገር ግን የእናንተ ናፍቆት ከልክ በላይ ጨምሯል። የእግዚአብሔር መንፈስ ከእናንተ ጋር እንደ ሆነ እናምናለን። ከእኛም ጋር ነው። እኛም እንደምንናፍቃችሁ እናውቃለን። መልካም ነው ይሁን። የእግዚአብሔር መልካምነት እያልቅምና ተመልሳችሁ መጥታችሁ በዐይነ ሥጋ የምንተያይበት ቀን እንዲመጣ እንጸልያለን፤ እንናፍቃለንም። ለዚያ እንዲያበቃንም እየጸለይን ነው። ይህና ከዚያም በላይ እንደሚሆን ተስፋ አለን።

አሁን በእኛ አገር የአዝመራው ስብሰባ ተጠናቋል። ዝናብ በጥቂቱ መዝነብ ጀምሯል እኛም እያረስን ነው። አገራችሁ ክረምት፣ ቅዝቃዜና ዝናብ እንደሚበዛበት ሰማን። ከእናንተ ሰረጀም ጊዜ ደብዳቤ አላገኘንም ነበር፣ ከወር በፊት ግን ሁለት ደብዳቤዎችን አግኝተናል። በቅርቡ እንደምትጽፉልን ተስፋ እናደርጋለን።

በዙሪያችን ብዙ መንፈሳዊ መነቃቃት አለ። ብዙ ተማሪዎችም አሉ። ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው በግርማ ቤት እስካሁን እየተማርን ነው። በቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ እሑድ ግርማና ታጠቅ እንዲሰብክ ተፈቅዶላቸዋል። ሰዎቹ በትዕግሥት ስብከቱን እየሰሙ ነው። ነገር ግን ሕይወታችንንም በጥንቃቄ እየተመለከቱ ነው። ዕንቅፋት እንዳንሆንባቸው እንሠጋለን። እናንተም ከዚህ አንጻር እየጸለያችሁልን እንደ ሆነ እናስባለን።

አባ አሰፋ የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኗል። ጓደኞችን ስለ ሆነና ስለምንረዳው በዚያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌል እሑድ እሑድ እንዲሰበክ አዟል። ስለዚህ በፍቅር እየሰበክን ነው። አባ አሰፋ አናንተን በጣም ናፍቋችኋል። እንድትጽፉለትና እንድትጸልዩለት ጥያቄ አቅርቦአል።

ዶክተር ጆሪ፣ ግሮስና ዶክተር መኮ እኛን ለማስተማር አንዳንድ ጊዜ በተራ ይመጣሉ። በጣም ጠንካራ የሆኑ ጥቂት ተማሪዎች አሉ። አናንተ የት እንደምትገኙ ብዙ ሰዎች እየጠየቁ ነው። እናም፣ «አገራቸው ናቸው፣ ተመልሰው ይመጣሉ» እንላቸዋለን።

ከኅይሉ ጊዮርጊስ ደብዳቤ ወይም ወሬ አላገኘንም። ምንም አልደረሰንም። ለእናንተ ደብዳቤ ከላክላችሁ ለእኛ ላኩልን። ምንም እንኳ ስለ እርሱ የምናውቀው ነገር ባይኖርም፣ እየጸለይንለት ነው።

አስቻለው ሰኔ ወር ላይ አልሄደም። አንድ ጊዜ ሄዶ ተመልሷል። ከዚያ ወዲህ ግን ሄዶ አያውቅም፣ ለምን እንደ ሆነም

አልገባንም። ትንሽ ፈርቷል። ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸም። የእግዚአብሔር ፈቃድ ገና እንዳልተሟላ ይሰማናል።

ከእኛ አካባቢ ወጥተን ወደ ሌላ ቦታ ገና አልሄድንም። በሌላ አባባል በራሳችን አካባቢ ነው እያስተማርን ያለው። ነገር ግን ወደፊት እግዚአብሔር ወዴት እንደሚወስደን እናውቅም። ፈቃዱን ብቻ እንከተል ዘንድ እየጸለይን ነው።

እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን። (ሮሜ8÷28)

ነገርን ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋና ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ለለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ። ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።(ፊል4÷6-7)

ጌታ ኢየሱስ ልባችንንና ሐሳባችንን በፈቃዱ መሠረት ብቻ እንዲመራና ከጥበቃው እንዳንወጣ እየጸለይን ነው።

የጭንቀት ጊዜ ሳይመጣ፣ «ደስ አያሰኙኝም» የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ፣ በወጣጥነትህ ጊዜ ፈጣሪህን ዐስብ። ብሎ ለሎሞን በመክ12÷1 ላይ ጽፏል። ይህንን ለሕይወታችን መመሪያ አድርገን እንቀጥላለን።

እኛ እንደምንረዳችሁ እናንተም በጸሎታችሁ ርዱን።

ጎይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ። (ፊል. 14÷13) አሜን!

ለአስተማሪዎቻችን ለሊንድሆልም፣ ለወንድሞቻችንና ለእኅቶቻችን ጆን፣ ጆሊና ስቴፈን የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!

ከቀያ ተማሪዎች ሁሉ የተላከ

በታጠቅ ከበደና በግርማ ብሩ

ሰኔ 27 ቀን 1969

ስለ አራቱ አማኞች ደብዳቤ ከጻፍሁላችሁ በኋላ ተጨማሪ ሠላሳ ሰባት ሙስሊሞች ወደ ክርስቲያናዊ እምነት መጥተዋል። ይህ ሁሉ የሆነው ከእናንተ ጸሎት የተነሣ ነው። በወልቾ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መስፋፋት በጣም አስደስቶኛል፣ እናንተንም እንደሚያስደስታችሁ ዐውቃለሁ። እኔ በእግዚአብሔር ጎይል ደኅና ነኝ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች መስፋፋታቸውን ቀጥለዋል።

በክርስቶስ ወንድማችሁ

ኅይሉ ጊዮርጊስ

የቃላት ፍቺ

አቡነ - ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዋና መሪ

አድባር - በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚሠራ ክፉ መንፈስ

አመድጉያ- በመንዝ ማኅበረ ሰቡ የሚጠቀምበት ትልቅ የግጦሽ ስፍራ

አረቄ - በቤት ውስጥ የሚጠመቅ ጎይለኛ የአልኮል መጠጥ

አቶ - ከወጣትነት ዕድሜ ወጣ ላሉ ሰዎች ከስማቸው በፊት ቀድሞ የሚጠሩበት

ቤተ ክህነት- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር

ቦረንቲቾ- ሰይጣንን ለማስደሰት የሚቀርብ የጥቁር በግ መሥዋዕት

ቡዳ- ክፉ ዐይን (የሰው ወይም የፀሓይ)

ጨሌ - ክፉ ነገር ለመከላከል የሚደረግ ክታብ

ደርግ - በኮሙኒዝም ጊዜ ኢትዮጵያን የመራ የመንግሥት ቡድን

ዱላ- ሰዎች ለምርኩዝነት፣ ራስንም ለመከላከል የሚጠቀሙበት ዕንጨት

ደብተራ- በመንፈሳዊ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ሥልጣን ያለው አብዛኛውን ጊዜም ጎይለኛ ጠንቋይ የሆነ

ፈላሻ - የአይሁድ ዘር እንዳላቸው የሚያምኑ ማኅበራዊ መገለል የደረሰባቸው
(በተጨማሪም ዛሬ ቤተ እስራኤል ይባላሉ)

ጋቢ- ከጥጥ የሚሠራ ነጭ ወፍራም ልብስ

ገረድ - አገልጋይ የቤት ሠራተኛ

ግእዝ - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የሥርዐተ አምልኮ ቋንቋ

ጉዝጓዝ- ቤትን ለማሳመር መሬት ላይ የሚበተን ረጃጅም አረንጓዴ ሣር።

እንጀራ- ከቦካ ሊጥ የሚጋገር የኢትዮጵያውያን ዋና ምግብ

መሶብ - ሰፋ ብሎ በልዩ የሣር ዐይነት በእጅ የሚሠፋ እንጀራና ወጥ የሚሰላበት

ተዝካር - ለሞተ ሰው መታሰቢያነት በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚደረግ ድግስ

ጠንቋይ - ልዩ ልዩ ድግምትን በመድገም፣ በመመተትና ርኩሳን መናፍስትን በመጥራት ከተፈጥሮ ውጭ በሆነ መንገድ የሚሠራ (አብዛኛውን ጊዜ ቄሶች በዚህ ተግባር ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።)

ጠላ- ከብቅልና ከጌሾ ቅጠል የሚሠራና የፈላ አገር በቀል መጠጥ

ጥምቀት- የኢየሱስ ጥምቀት የሚከበርበት የኦርቶዶክስ በዓል

ዛር - በጠንቋይ ትእዛዝ ለአንድ ሰው የሚሰጥ ርኩስ መንፈስ

ውፋ - ቄስ ያልሆነ ጠንቋይ

ወጥ - ብዙ ጊዜ ቅመም የበዛበትና ከእንጀራ ጋር ለምግብነት የሚቀርብ

ታቦት - የቃል ኪዳን ታቦት